# የተቀናጁ የስነ-ህዝብ፣ የጤናና አካባቢ ፕሮጀክቶች ማዘጋጀትና መተግበር

## ለዕቅድ አውጪዎችና ሥራ አስኪያጆች የተዘጋጀ አውደጥናት የተሳታፊዎች ማኑዋል

ይህ ሕትመት የተዘጋጀው በUSAID
Environmental Health IQC
በCDM International የተተረጎመውም
በፒ.ኤች.ኢ ኢትዮጵያ ኮንሶረቲየም ነው።

# የተቀናጁ የስነ-ህዝብ፣ የጤናና አካባቢ ፕሮጄክቶች ማዘጋጀትና ማከናወን

# ለዕቅድ አውጪዎችና ሥራ አስኪያጆች የተዘጋጀ አውደጥናት

## የተሳታፊዎች ማኑዋል

ግንቦት 2002

# መግቢያ

ህይወት ሊኖርበት የሚችልው የመሬት ክፍል ወይም አካባቢ ተብሎ የሚጠራው በውስጡ ከያዘው የተፈጥሮ ሀብቶች ጋር ለሰው ልጅ ህልውናና ልማት መሰረት ነው፡፡ ከዚህ የተፈጥሮ ሀብት ውስጥ አብዛኛው በተወሰነ መጠን ስለሚገኝ በአጠቃቀምና አያያዝ ጉድለት ሊያልቅ ወይም ሊበላሽ ይችላል፡፡ ታዳሽ የሆኑ ወይም ያልቃሉ ተብለው የማይገመቱ የተፈጥሮ ሀብቶች ለምሳሌ አየር ሰው ሰራሽ በሆኑ ችግሮች እየተበከሉና ለጤና አስጊ ወደ ሆነ ደረጃ እየደረሱ እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች ወይም የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ለጤናማ ህይወት ጠንቅ ከመሆን አልፎ ለወደፊት ትውልዶች ችግሮችን ጥሎ ያልፋል፡፡

የአካባቢ መጎዳት እና ተዛማጅ ችግሮች እየጨመሩ የመጡት በዓለም ላይ ከሚታየው የህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ የተከሰተውን ፍላጎት ለማርካት አገሮች በሚያደርጉት ገደብ ያጣ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ምክንያት ነው፡፡ በሁብት የበለጸጉ አገሮች መሃከል የሚደረገው ሃብት የማጋበስ ውድድርና ተረፈ ምርቶችን ያለጥንቃቄ መልቀቅ ዋናው የአካባቢ ችግር ነው፡፡ ድሃ አገሮች በበኩላቸው የዕለት ጉርስ ለማግኘት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለአካባቢ መጎዳት የበኩላቸውን ያደርጋሉ፡፡ በድህነት ውስጥ ያሉ ማህበረሰቦች የተጎዱ አካባቢዎችን ለማስተካከል አቅም ስለሚያንሳቸው አካባቢው እየተጎዳ በሄደ ቁጥር የበለጠ ለችግሩ ተጠቂ ይሆናሉ፡፡ በድሃ አገሮች የሚከሰተው የህዝብ ቁጥር መጨመር አካባቢያቸውን የበለጠ ያጎሳቁለዋል፡፡ ምክንያቱም አማራጭ የገቢ ምንጭ ስለሌላቸው ለገንዘብ ማግኛ ፣ለቤት መስሪያ፣ለምግብ፣ ወዘተ የሚጠቀሙት መሬትና መሬት ላይ የበቀሉ ዕጽዋትን ነው፡፡ ችግሩ የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠቀሙ ላይ ሳይሆን የአጠቃቀም ጉድለቶችን ለማስተካከልና የተጎዱ አካባቢዎችን አስተካክሎ በዘላቂነት ለመጠቀም ባለመቻል ከጊዜ ወደ ጊዜ ተጎጂነታቸው መጨመሩ ነው፡፡

በዓለም የተከሰተው የህዝብ ቁጥር መጨመር ለአካባቢ መጎሳቆል ወይም ለተፈጥሮ ሀብቶች ዕጥረት ወይም መበላሸት ምክንያት ሆነው ከሚነሱት ዋነኛው ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች በቅድሚያ የሚያጠቁት በኤኮኖሚ ያላደጉ አካባቢዎችን ነው፡፡ ለአሁኑና ለወደፊቱ ትውልዶች መሬት ተስማሚ መኖሪያ ሆና እንድትቀጥል ለማድረግና እየጨመረ የመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመግታትና ችግሩንም ለመቋቋም እንዲቻል ብዙ ዓይነት የአሠራር መንገዶችና ዘዴዎች በተግባር እየተፈተሹ ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ ከነዚህ የአሰራር መንገዶች አንዱና እየተከሰቱ ላሉ ችግሮች ( የአካባቢ መጎዳት፣ የተፈጥሮ ሃብት ዕጥረት፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የጤና መጓደል፣ድህነት፣የምግብና ውኃ በቂ አለመሆን፣ወዘተ) ጥሩ መፍትሔ ሆኖ የመጣው ስነ-ሕዝብ (የህዝብ ቁጥር ሁኔታ)፣ጤና እና አካባቢ ጥበቃን ማቀናጀትና መተግበር ነው፡፡ አቀናጅቶ የመተግበሩ ሁኔታ ከከፍተኛ ደረጃ ማለትም የመንግስት ፖሊሲ፣ዓለም አቀፍ የልማት ዕቅድና ገንዘብ እንቅስቃሴ ማዕቀፍ ጀምሮ እስከ በማህበረሰብ ደረጃ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ድረስ ወጥ ሆኖ መቀጠል እንዳለበትና ይህም ሲሆን የሚፈለገው ዘላቂ ልማት፣ከድህነት መውጣት፣የእናቶችና የህጻናት ጤና መጠበቅ፣የአካባቢ ጥበቃ እና በአጠቃላይ የሰው ልጅ ደህንነት በዘላቂነት ሊረጋገጥ እንደሚችል ተመስክሯል፡፡ በዚህ ረገድ በአገር ውስጥና በውጪ አገራት የተሞከሩ አቀናጅቶ የመተግበር ውጤቶች እንደሚያሳዩት አሰራሩ ወጪ ቆጣቢ፣ ውጤታማ፣ የተጠቃሚ ማህበረሰቦችን ፍላጎት የሚያሟላና የሴቶችን እና የህፃናትን ተጠቃሚነት የሚያጎላ ነው፡፡

# የዚህ ትርጉም ሥራ ዓላማ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የስነ-ህዝብ፣ጤናና አካባቢ ጉዳዮችን አቀናጅቶ መተግበሩ በእንግሊዝኛው አጠራር (Population, Health and Environment ወይም PHE Integration) በመባል ይታወቃል፡፡ የአሜሪካን ዓለምአቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) ፊሊፒንስ አገር የባህር ዳርቻ ነዋሪ ከሆኑ ማህበረሰቦች ጋር ይህንን የተቀናጀ አሰራር በመተግበር አመርቂ ልምድና ውጤት አግኝቷል፡፡ ይህንን በማህበረሰብ ደረጃ የተገኘውን ውጤት እና ለውጤቱ መገኘት መሰረት የሆነውን አሰራር ለሌሎቹም ለማስተዋወቅና ጠቃሚ አሰራሩን ለማስፋፋት ባለው እቅድ መሰረት ይህንን የማሰልጠኛ ማኑዋል አዘጋጅተዋል፡፡ ይህንን ማኑዋል ለአገር ውሰጥ ተጠቃሚዎች ቀለል ባለ መልኩ በማቅረብ ሥራ ላይ ለማዋል ስለታሰበ ከ BALANCED ፕሮጄክት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በ PHE Ethiopia አስተባባሪነት ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡ በማንዋሉ ውስጥ የአንዳንድ ቃላት ፍች አስቸጋሪ በመሆኑ የእንግሊዝኛውን ቃል እንዳለ ለመጠቀም ተገደናል፡፡ ዋናው ዓላማ አሰራሩንና እውቀቱን ማስፋፋት ስለሆነ ተጠቃሚዎች በዚህ ዙሪያ የተዘጋጁ ተጨማሪ የእንግሊዝኛ ሰነዶችን በማንበብ እወቀታቸውን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በማንዋሉ ውስጥ ያሉት ምሳሌዎች በሙሉ በፊሊፒንስ የባህር አካባቢ ነዋሪዎችና የ Philpines PATH Foundation ጥረት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ከየአካባቢያችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ብንጠቀም ማኑዋሉ ግልጽ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ የባህር ለሚለው የደን ወይም የሐይቅ አካባቢ ወዘተ በማለት ከራሳችን አካባቢያዊ ሁኔታ ጋር ልናዘምደውና ልንጠቀም እንችላለን፡፡

# የስነ-ህዝብ፣ ጤናና አካባቢ (ፒ.ኤች.ኢ) ፕሮጀክቶች በተቀናጀ መልኩ ለማዘጋጀትና ለመተግበር እንዲችሉ ለዕቅድ አዉጪዎችና ሥራ አስኪያጆች አውደ ጥናት የተዘጋጀ ማኑዋል

***ማሳሰቢያ:*** *ይህ ማኑዋል የፒ.ኤች.ኢ ስልጠና አውደ ጥናት ተሳታፊዎች የተዘጋጀ ስለሆነ ለተመሳሳይ ተግባር ጥቅም ላይ ሊውል ወይም በግል ሊነበብ ይቸላል፡፡*

# ማዉጫ

***ገጽ***


ክፍለጊዜ 1፡ የዓዉደጥናቱ መክፈቻ 6

ክፍለጊዜ 2፡ የፒ.ኤች.ኢ POPULATION HEALTH ENVIRONMENT -PHE) አጠቃላይ ቅኝት 11

ክፍለጊዜ 3፡ ግንዛቤያዊ ሞዴል (CONCEPTUAL MODEL) 21

ክፍለጊዜ 4፡ የፕሮጀክት ግቦች ዓላማዎችና ስትራቴጅዎችን ማስቀመጥ 36

ክፍለጊዜ 5፡ የፒ.ኤች.ኢ ክንውን (INTERVENTION) መምረጥ 53

ክፍለጊዜ 6፡ አመላካቾችን መለየት 72

ክፍለጊዜ 7: የፒ.ኤች.ኢ አፈፃፀም ሞዴሎችና ዘዴዎች 85

ክፍለጊዜ 8፡ የክትትልና ግምገማ እቅድ 102

ክፍለ ጊዜ 9፡ ግብረ-መልስ (BACK-HOME APPLICATION) 121

የአውደጥናቱ ግምገማ 126

# ምስጋና

እ.ኤ.አ በ 2007 በተደረገዉ የዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ የስነህዝበ፣ ጤናና አካባቢ ዘርፎች ግምገማ በነዚህ ዘርፎች ስር የሚከናወኑ የመስክ ስራዎችን ለማስፋፋት የአመራራርና የቴክኒክ ብቃት ማሳደግ አስፈላጊ እንደሆነ አረጋግጧል። ይህን ተከትሎ " የተቀናጀ የስነህዝበ፣ ጤናና አካባቢ (ፒ.ኤች.ኢ) ፕሮግራም ዝግጅት ማኑዋል" እ.ኤ.አ በ 2008 ተዘጋጅቶ ተሰራጭቷል። ማኑዋሉን በአግባቡ ለመጠቀም የፒ.ኤች.ኢ. ፕሮጀክቶችንና የዘርፎቹን ልዩ ባህሪ ያገናዘበ ዕዉቀት የግድ ስለሚል እነዚህን ክህሎቶች በማስጨበጥ ላይ ያተከረ አዉደጥናት አስፈልጎአል። በዚህ ላይ በመመስረት የተለያዩ ዘርፎችን ያካተቱ የተቀናጁ የስነህዝበ፣ ጤናና አካባቢ ፕሮጀክቶችን ለማቀድና ለማከናወን የሚያስችል አካባቢያዊ አቅም ለመፍጠር ይህ ሞዴል አዉደጥናት ተዘጋጅቶአል።

ይህ ሞዴል የአዘጋጆቹና በሂደቱ ከፍተኛ ቴክኒካዊ ድጋፍ በመስጠት ለተባበሩት የፍሬድ ሮዘንስዊግ (Fred Rosensweig ) ከTRG እንዲሁም የሄዘር ዲአግነስ (Heather D'Agnes) (የ ዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ የስነህዝብና አካባቢ ቴክኒክ አማካሪ) የጋራ ጥረት ዉጤት ነዉ። በተጨማሪም በስልጠናዉ አዉደጥናት ሙከራ ጊዜ ስለፒ.ኤች.ኢ ይዘትና ስለ ስልጠናዉ ዘዴ ጠቃሚ ምክርና አስተያየት በመስጠት ለተባበሩን ኢትዮጵያዉያን ባልደረቦቻችን ምስጋና እናቀርባለን። በተለይ አዉደጥናቱን በማስፈጸም የ PHE Ethiopia ዳይሬክተር አቶ ነጋሽ ተክሉ ፤ እንዲሁም ለአዉደጥናቱ ተባባሪ አመቻቾች ለዶ/ር ደስታ ወልደዮሃንስና ለፕሮፌሰር ዘሪሁን ወልዱ ምስጋናችን የላቀ ነዉ።

በተጨማሪም ለሽሪስ ሊንደሰይ (Sherise Lindsay) ከ TRG እና ለጆን ጋቪን (John Gavin) ከCDM አዉደጥናቱን በማስፈጸምና ላበረከቱት የሎጀስቲክስ ድጋፍ ምስጋናችንን እናቀርባለን። በመጨረሻም በአርትኦትና በገጽ ዲዛይን ማኑዋሉ የተሻለ እንዲሆን ላደረገዉ ጆን ሊፕሲ (John Lipsey) ማመስገን እንወዳለን።

### ስለ አዘጋጆቹ

**ሊኦና ዲአግነስ (Leona D'Agnes)** በኔፓል ስነህዝብንና ጤናን ከደን ክብካቤ ጋር ለማቀናጀት በመከናወን ላይ ባለ ፕሮጀክት የፒ.ኤች.ኢ አማካሪ ሆና በማገልገል ላይ ትገኛለች። በፍሊፒንስ የተቀናጀ የስነህዘብና የባርጠረፍ ሀብት ክብካቤ (IPOPCORM) ፕሮጀክትን በማዘጋጀት አስተዋጽኦ አድርጋለች። ተጨማሪም በፍሊፒንስ የፓዝ ፋዉንዴሽን ትኩረት በሆኑ የብዝሃሕየወት አካባቢዎች የIPOPCORMን አሰራር ለማስፋፋት በሚደረገዉ ጥረት የቴክኒክ አማካሪ ሆና በማገልገል ላይ ትገኛለች።

**ማርሻ ስሌተር** (**Marsha Slater)** ለ "ተሬይኒግ ሪሶርስ ግሩፕ" (TRG) አመቻች እንዲሁም የስልጠና የድርጅት ግንባታ አማካሪ ናት። አሳታፊ ዘዴዎችን በመጠቀም በዛ ያሉ አዉደጥናቶችን በዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ ለሚደገፉ የቴክኒክ ፕሮግራሞች ሰጥታለች። ከዚህ በተጨማሪ በፕሮጀክት ዝግጅትና አስተዳደር አቅም ግንባታ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ፕሮጀክት ፈጻሚ ድርጅቶች ጋር ትሰራለች።

*ማሳሰቢያ :በዚህ ማኑዋል ዉስጥ የቀረበዉ የአዘጋጆቹ አመለካከት የግድ የዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲን ወይም የአሜሪካንን መንግስት አመለካከት ያንጸባርቃል ማለት አይቻልም።*

# ክፍለጊዜ 1፡ የዓዉደጥናቱ መክፈቻ

**የክፍለጊዜዉ ዓላማ፡**

- የዓዉደጥናቱን ግብና ዓላማዎች ማሳወቅ

## የዓዉደጥናቱ አጠቃላይ ግብ

ዘላቂ፣ ዉጤታማና ሊስፋፉ የሚችሉ የተቀናጁ የስነህዝብ፣ ጤናና አካባቢ (የፒ.ኤች.ኢ) ፕሮጀክቶችን ለማቀድ፣ ለመተግበርና ለመከታተል የሚያስችል አቅም መገንባት።

## የዓዉደጥናቱ ዓላማዎች

1. የተለያዩ ዓይነት የፒ.ኤች.ኢ ቅንጅት ዘዴዎችን መተንተን፤ የእያንዳንዱን የቅንጅት ዘዴ ጠቃሚና ጎጂ ጎን መተንተን።
2. በአንድ አካባቢ ያሉ የስነሕዝብ፣ ማህበራዊ እና የአካባቢ ትስስሮች በስዕላዊ መንገድ የሚገልጽ ግንዛቤያዊ ሞዴል (Conceptual Model) ማዘጋጀት።
3. ከግንዛቤያዊ ሞዴል በመነሳት ለችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ እድሎችን መለየትና ዓላማዎችን (የአጭር ጊዜ ውጤቶች) ማዘጋጀት።
4. የውጤት ሰንሰለቶችን (Result Chains) በማዘጋጀትና መጠቀም ተስማሚ ስትራቴጂዎን መምረጥ።
5. የተለያዩ ዓይነት ሞዴሎችና የፒ.ኤች.ኢ ትስስር ዘዴዎችን መተንተን።
6. ነባር የፒ.ኤች.ኢ መሳሪያዎችን በመጠቀም ተስማሚ የክትትልና ግምገማ አመላካቾች መምረጥ እንዲሁም የክትትል ዕቅድ ማዘጋጀት።
7. መነሻ የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት ማዘጋጀት እንዲሁም ለቀጣይ ክትትል ስራዎች እቀድ ማዘጋጀት።

## የስነህዝብ፣ ጤናና አካባቢ (ፒ.ኤች.ኢ) ፕሮጀክቶች ዝግጅት
## ዐዉደጥናት መርሃግብር

| አንደኛ ቀን | ሁለተኛ ቀን | ሦስተኛ ቀን | አራተኛ ቀን |
|---|---|---|---|
| 03:00<br>ክፍለ ጊዜ 1፡<br>የዐውደ ጥናቱ መክፈቻ<br>• አቀባበል<br>• ትውውቅ<br>• የመክፈቻ ስነስርዓት<br>• ግብ/አጀንዳ<br><br>04፡45<br>ክፍለ ጊዜ 2፡<br>የፒ.ኤች.ኢ ቅኝት<br>• አሳታፊ ገለፃ<br>• የድርጅታዊ ዝግጁነት ለመፈተሽ የሚከናወን የቡድን ተግባር<br>• ውይይትና ማጠቃለያ | 03:00<br>ክፍለ ጊዜ 4፡<br>የፕሮጀክት ግቦች፣ ዓላማዎችና ስትራቴጂዎችን መወሰን<br>• አሳታፊ ገለጻ<br>• የቡድን ተግባር<br>• የጋራ ውይይት<br>• የውጤት ሰንሰለቶች ገለጻ<br>• የቡድን ተግባር | 03:00<br>ክፍለ ጊዜ 5፡<br>ስትራቴጂካዊ ክንውን (ከሁለተኛው ቀን የቀጠለ)<br>• ውይይትና ማጠቃለያ<br><br>4፡30<br>ክፍለ ጊዜ 6፡<br>አመላካቾችን መለየት<br>• የወጤት ሰንሰለቶችን በመጠቀም ማሳየት<br>• መደበኛ የፒ.ኤች.ኢ አመላካቾች (MEASURE መምሪያ የተወሰደ)<br>• የቡደን ተግባር<br>• የጋራ ውይይት | 03:00<br>ክፍለ ጊዜ 7፡<br>የፒ.ኤች.ኢ አተገባበር ሞዴሎችና ዘዴዎች (ከሦስተኛው ቀን የቀጠለ)<br>• የተመረጡ የአተገባበር ካርታዎችን ማየት<br>• ውይይትና ማጠቃለያ<br>4፡00<br>ክፍለ ጊዜ 8፡<br>የክትትልና ግምገማ ዕቅድ<br>• አሳታፊ ገለፃ<br>• የክትትል ዕቅድ ዝግጅት (የቡደን ተግባር)<br>• ውይይትና ማጠቃለያ |
| ምሳ | ምሳ | ምሳ | ምሳ |
| 7:30<br>ክፍል ጊዜ 3<br>ግንዛቤያዊ ሞዴል<br>• አሳታፊ ገለፃ<br>• የቡደን ተግባር<br>• መርዕይ ጉዞ<br>• ውይይትና ማጠቃለያ | 7:30<br>ክፍል ጊዜ 4<br>(ከጠዋቱ የቀጠለ)<br>• መርዕ ይ ጉዞ (የውጤት ሰንሰለቶች)<br>• ውይይትና ማጠቃለያ<br><br>8፡30<br>ክፍለ ጊዜ 5፡<br>ስትራቴጂካዊ ክንውን<br>• ስለመረጃ ደገፍ ክንውኖች መግለጫና ውይይት<br>• የቡድን ተግባር | 7:30<br>ክፍል ጊዜ 7<br>የፒ.ኤች.ኢ አተገባበር ሞዴሎችና ዘዴዎች<br>• አሳታፊ ገለጻ<br>• ክፍተትን መተንተን (የቡደን ተግባር)<br>• የአቻ ውይይት | 7:30<br>ክፍል ጊዜ 9<br>ተሣታፊዎች ወደየአካባቢአቸው ሲመለሱ …<br>• የዐውደጥናቱ ውጤት ማጠቃለያ/የቡድ ን ውጤት<br>• የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት<br>• የስልጠናና ቴክኒካዊ ድጋፍ ፍላጎቶች መለየት |
| 11፡30<br>የዕለቱ ውሎ ማጠቃለያ | 11፡30<br>የዕለቱ ውሎ ማጠቃለያ | 11፡30<br>የዕለቱ ውሎ ማጠቃለያ | 11፡30<br>የዕለቱ ውሎ ማጠቃለያ |

# ከስነ ህዝብ ፣ ጤና ፣አካባቢ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ቃላት ትርጉም

**ተግባር** (Activity) ፡- ፕሮጄክቶች/ፕሮግራሞች ውጤት ለማግኘት የሚጠቀሙባቸው ግብዓቶች፤ ዓላማቸው ላይ ለመድረስ የሚያከናውኗ ቸው ተግባሮች፡፡ የፒ.ኤች.ኢ ተግባሮች የተሳሰሩ፣ አቅምን ያገናዘቡ እና አግባብነት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡ አንድ ተግባር ተደጋግሞ ሲከናወን ስትራቴጂ ይሆናል፡፡

**የጋራ ግብ** (Common Goal)፡- የተለያዩ የፒ.ኤች.ኢ ውጤቶች በጋራ የሚያስገኙት ልማት/መሻሻል፡፡ ለምሳሌ የፒ.ኤች.ኢ ተግባሮች በተቀናጀ መልኩ በማከናወን የሚገኝ የመጨረሻ ውጤት፡፡

**ግንዛቤያዊ ሞዴል** (Conceptual Model,)፡- በአንድ ፕሮጀክት ጣቢያ በአካባቢና ጤና ጉዳዮች መሃከል ያለዉን ትስስርና እመንታዎች (assumptions) በስዕላዊ መንገድ መግለጽ፡፡ በአግባቡ የተዘጋጀ ግንዛቤያዊ ሞዴል ፕሮጀክቱ ሊቀርፋቸዉ ያሰባቸዉን በፕሮጀክት ጣቢያ ያሉ ችግሮችን መንስኤዎች፤ እንዲሁም ምቹ ሁኔታዎችን ለይቶ ለማወቅ ጠቃሚ መሳሪያ ነዉ፡፡ ተያያዥ የፒ.ኤች.ኢ ዘርፍ ክንዉኖች ወደ ፕሮግራሙ የረዥም ጊዜ ግብ እንዴት እንደሚያመሩ ስለሚያመለክቱ ግንዛቤያዊ ሞዴሎች በተለይ በፒ.ኤች.ኢ ፕሮግራሞች ዉስጥ አስፈላጊ ናቸዉ፡፡

**መረጃ-ደገፍ ክንውን** (Evidence-Based Intervention) ፡- በሙከራ ጥናቶች ወይም ጥልቅ የግምገማ ዘዴዎች ውጤታማነቱ የተረጋገጠ ተግባር፡፡ ለምሳሌ ስለውጤታማነታቸው ሳይንሳዊ መረጃ ሊቀርብላቸው የሚችሉ ክንውኖች፡፡

**ግብ** (Goal ) ፡- በአንድ ፕሮጀክት/ፕሮገራም አማካኝነት ሊገኝ የታሰበ አጠቃላይ የረዥም ጊዜ ለውጥ/መሻሻል፡፡ ግብ በአንድ ዓላማ እንዲታይ የሚፈለግ የረዥም ጊዜ ዉጤት (Impact) ነው፡፡ ከዓላማ ጋር ሲነጻፀር ሰፋ ያለ ይዘት አለው፡፡ ዓላማ፣ ግልፅ ፣ ራዕይ ያለው፣ በጥቅሉ የሚቀመጥ እንዲሁም የሚለካ መሆን አለበት፡፡

**የረዥም ጊዜ ዉጤት** (Impact) ፡- አንድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ሊያስገኝ ያሰበው የመጨረሻ ውጤት (በረዥም ጊዜ የሚታይ ለውጥ)፡፡

**አመላካች** (Indicator) ፡- የልኬት መግለጫ፡፡ የአንድን ፕሮጀክት፣ ፕሮግራም፣ የስነህዝብ፣ ጤናና አካባቢ ዉጤቶች አንድ ልዩ ባህሪይ/ውጤት ለመለካት የሚያገለግል መለኪያ፡፡ አመላካቾች አንድን ውስን ባህርይ ፣ ጽንሰ ሃሳብ ፣ ክስተት መግለጽ አለባቸው፡፡ አመላካቾች የተቡ ፣ ተለኪ ፣ ስምም ፣ ትክክል መሆን አለባቸው፡፡

**ግብዓት** (Input) ፡- ላንድ ፕሮጀክት ማከናወኛ የሚውሉ የገንዘብ እንዲሁም የቁሳቁስ ሃብቶች (ጥሪቶች)፡፡ የሰራተኞች የስራ ጊዜ፣ ገንዘብ እና ምቹ የስራ አካባቢን ያካትታል፡፡

**የተቀናጀ አመላካች** (Integrated Indicator)፡- የፒ.ኤች.ኢን ዘዴዎች ቅንጅታዊ ባህሪይ ለመለካት የሚያገለግል መስፈርት፡፡

**አሸጋጋሪ ውጤት** (Intermidiate Result) ፡- ወደመጨረሻው ግብ የሚያደርስ ነገር ግን በአጭር ጊዜ የሚታይ ለውጥ።

**ክንውን** (Intervention) ፡- ለአንድ ችግር መፍትሄ ለማስገኘት ወይም ችግሩ እንዳይደርስ ለመከላከል የሚተገበሩ ስራዎች/ ለዚሁ ተግባር የሚውሉ ቁሳቁሶች።

**ተያዥ ክንውን** (Linked Intervention)፡- በጽንስ ሃሳብም ሆነ በተግባር የተቀናጁ ፤ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዘርፎች ውስጥ የሚተገበሩ ክንውኖች። እነዚህ ክንውኖች ከአንድ ውሱን ዘርፍ ያለፈ ውጤት ያስገኛሉ።

**ክትትል** (Monitoring)፡- አንደ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት በታሰበው/በታቀደው መሠረት እየተከናወነ ስለመሆኑ የምናረጋግጥበት ሂደት።

**ዓላማ** (Objective)፡- ግብ ላይ ለመድረስ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ከአንድ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት የሚጠበቁ ውጤቶች።

**ለውጥ** (Outcome)፡- አንድ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት በስነ-ህዝብ ፣ በአካባቢ ወይም በጤና ጉዳዮች ላይ የሚያስከትለው ለውጥ። ለውጥ በማህበረሰቡ ደረጃ ወይም በመካነህይወት (Habitat) ደረጃ በሚስተዋል ሁኔታ ይለካል።

**ውጤት** (Output) ፡- አንድ ተግባር በማከናወን እንዲገኝ የሚፈለግ ምርት/ውጤት።

**ፒ.ኤች.ኢ** (P.H.E.-Population, Health, Environment) የሚለዉን የሚያመለክት የእንግሊዝኛ ምህጻረቃል ነዉ። የአማርኛዉም ምህጻረ ቃል ከእንግሊዝኛዉ በቀጥታ የተወሰደ ነዉ።- የስነ-ህዝብ ፣ ጤናና አካባቢ ዘርፎችን የሚያስተሳስር ፤ የነዚህ ዘርፎችን ቅንጅትና መደጋገፍ የሚያመቻች የማሕበረሰብ ልማት ሞዴል ወይም ዘዴ።

**ሂደት** (Process)፡- ፕሮጀክቶች ዓላማቸውን ለማሳካት/ውጤት ለማግኘት የሚያከናውኗቸው ተግባሮች።

**ፕሮጀክት**፡- አንድን የተወሰነ ዓላማ ለማሳካት የሚደረግ በዕቅድ የሚመራ ስራ/ተግባር። ፕሮጀክት ብዙውን ጊዜ በተወሰነ ቡድን እንዲሁም ቦታ ላይ ያተኮረ ሲሆን በጊዜ የተገደበ ነው። ከዲዛይን ፣ ከአስተዳደርና እና ከማስፈጸሚያ ገንዘብ ፍሰት አንጻር ሲታይ የአንድ ፕሮግራም አካል ቢሆኑም ፕሮጀክቶች የልማት መሰረታዊ ወይም መነሻ ክፍሎች ናቸው።

**መርሃ-ግብር/ፕሮገራም** (Program)፡- የጋራ ግብ ላይ ለመድረስ የሚከናወኑ ተያያዥነት ያላቸው ፕሮጀክቶች ስብስብ።

**ውጤት** (Result)፡- ወደፊት እንዲኖር የሚፈለግ ሁኔታን የሚያመለክት አጠቃላይ ስያሜ።

**የውጤት ሰንሰለት** (Result Chain)፡- ተያያዥነት ያላቸዉ መንስዔዎችን በ "ምክንያት-ዉጤት" ሰንሰለት በማስተሳሰር የነገሮች መንስዔና የሚያስከትሉትን ዉጤት ለመተንተን የሚያገለግል ስእላዊ ዘዴ ነዉ። የዉጤት ሰንሰለቶች ከምናባዊ ሞዴሎች ጋር የሚመሳሰሉ ቢሆንም በአንድ

ምናባዊ ሞዴል ዉስጥ በተካተተ አንድ ውሱን 'ሰንሰለት' ላይ ቢቻ ያተኮረ ነዉ፡፡ እነዚህ 'ሰንሰለቶች' የምናከናዉነዉ ተግባር የምንፈልገዉን ለዉጥ እንዴት እንደሚያመጡ ያለንን ግንዛቤ በስዕል መልክ ይገልጻሉ፡፡ የዉጤት ሰንሰለቶች ዉጤት-ተኮር፣ የምክንያት ትስስር ያላቸዉ፣ ለዉጥ አመላካች፣ የተሟሉና ግልጽ መሆን አለበቸዉ፡፡

**ስልት** (Strategy)፡- አንድ ችግር/ፈተና እንዳይደርስ ለመከላከል ከደረሰም ለመቅረፍ የሚረዱንን ዜዴዎች ለመግለጽ የሚያገለግል ጽንሰ ሃሳብ፡፡ ስትራቴጂ የተወሰነ ክንዉንን/ተግባርን ከማመልከት ይልቅ ጥቅል ወይም ግንዛቤያዊ መሆኑ ልዩ መገለጫዉ ነዉ፡፡ ብዙዉን ጊዜ ድርጅቶች በመጀመሪያ ስትራቴጂ ካስቀመጡ በኋላ ይህ ስትራቴጂ በሂደት ወደ ክንዉን/ተግነባርነት ይቀየራል፡፡ ለምሳሌ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችንና መረጃ ማቅረብ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ዕድገትን ለመቆጣጠር አንዱ ስትራቴጂ ነዉ፡፡

***ተደጋጋፊ ዘዴዎች/አሰራር*** (Synergic Approach) ፡- ከነጠላ የስነ-ህዝብ፣ ጤናና አካባቢ ፕሮግራሞች ከሚጠበቀዉ ዉጤት ባሻገር ተጨማሪ ዉጤት የሚያስገኝ ዘዴ/አሰራር፡፡ የ 'ተደጋጋፊ ዘዴዎች/አሰራር' ጽንሰሃሳብ ከ 'የወል ግብ' ጽንሰሃሳብ ጋር አብሮ የሚሄድ ነዉ፡፡

***ዕሴት-ጨማሪ አመላካች*** Value-added Indicator) ፡- በአንድ ዘርፍ ዉስጥ በሚከናወን ተግባር ከዚሁ ዉሱን ዘርፍ ባሻገር በሌላ ዘርፍ ላይ የሚጨመር ዕሴት (የሚገኝ ዉጤት) ፡፡ ለምሳሌ አንድ የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት እየመነመነ ያለ የአሳ ብዝሃ ህይወት ሀብትን ለመታደግ የተሻሻሉ የአሳ ሃብት አያያዝ ተግባሮችን ሊያከናዉን ይችላል፡፡ ይህ ክንዉን የማህበረሰቡን የስነ-ምግብ ሁኔታ በማሻሻል ተጨማሪ 'የማይጠበቅ' ዉጤት ሊያስገኝ ይችላል፡፡ ፕሮጀክቱ በሌሎች ዘርፎች ለሚከናወኑ ተግባሮች የተለየ በጀት ያየዘበት ሁኔታ ካለ እነኚህን 'ያልተጠበቁ' ዉጤቶች መለካት የፒ.ኤች.ኢን አሰራሮች በይነ-ሴክተራዊ ዉጤታማነት ለማሳየት ያገለግላሉ፡፡

***ራዕይ*** (vision)፡-በፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት አማካኝነት ሊደረስበት የሚፈለግ ሁኔታ፡፡ ራዕይ ከ 'የጋራ ግብ' ጽንሰሃሳብ ጋር አብሮ የሚሄድ ነዉ፡፡

# ክፍለጊዜ 2፡ የፒ.ኤች.ኢ አጠቃላይ ቅኝት

- የተቀናጁ የፕሮግራም ዘዴዎች ወይም አሰራሮችን ተያያዥነት ፤ አንፃራዊ ጥቅማችውንና ጉዳqቸውን ማብራራት፤

- ነጠላ-ዘርፍ ፕሮጀክቶችን ከዘርፈ-ብዙ ፕሮጀክቶች ጋር በማነፃፀር የተቀናጁ ፕሮጀክቶች የሚከናወኑበትን መሰረqዊ ምክንያት ማሳወቅ፡፡

## ከክፍል ጊዜው በፊት የሚነበቡ ጽሁፎች

- የፊሊፒንስ #የተቀናጀ የስነህዝብና የባርጠረፍ ሃብቶች ክብካቤ# ፕሮጀክት - በእንግሊዝኛው አጠራር IPOPCORM በመባል የሚqወቅ፡፡ ይህ ዘዴ ከአሁን በሁዋላ «የአይፖፕኮርም» በመባል ይጠራል፡፡
- #የስነህዝብ፤ጤናና አከባቢ ፕሮጀክቶች ማቀናጃ የፕሮግራም ዝግጅት ማኑዋል# ፡፡ ከዚህ በሁዋላ #የፒ.ኤች.ኢ. ፕሮግራም ዝግጅት ማኑዋል# በመባል ይጠራል፤ ምዕራፍ 1 ና 2፡፡

# የፒ.ኤች.ኢ. መግለጫ

- ፒ.ኤች.ኢ. (P.H.E ከሚለዉ የእንግሊዝኛዉ ምህጻረ ቃል በቀጥታ የተወሰደ ነዉ) የስነህዝብ፣ ጤናና የአካባቢ ጉዳዮችን የሚያስተሳስር የማህበረሰብ ልማት ሞዴል ነው፡፡ ይህ ሞዴል በተለይ በብዝሃህይወት ሃብq ቸው በበለጸጉ አከባቢዎች በተለያዩ ሴክተሮች መሃከል የሚኖረውን መደጋገፍና ቅንጅት ያመቻቻል፡፡ (BALANCED)

- በአንድ ማሕበረሰብ ወይም በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ በሚከወኑ የተፈጥሮ ሃብት ወይም ተመሣሣይ የአከባቢ ጥበቃ ስራዎች፤ እንዲሁም የስተነዋልዶ ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል በሚከናወኑ ሥራዎች መሃከል ያለ ትስስር (ኤንግልማን) ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ፒ (P) | = | የሥነተዋልዶ ጤና እና የቤተሰብ ምጣኔ |
| ኤች (H) | = | ውሃ፣ ንጽህና፣ ወባ፣ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ፣የእናቶችና ሕጻናት ጤና |
| ኢ (E) | = | የተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ የብዝሃ ህይወት ክብከቤ፣ የአሣ ሃብት አያያዝ፣ ኤኮ-ግብርና (Eco-Agriculture) |

ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ሊኖር የሚችል ግንኙነት

| | | |
|---|---|---|
| ኢ (E) | = | ትምህርት (መደበኛና መደበኛ ያልሆነ) |
| | = | ኢነርጂ (ማገዶ ቆጣቢ ጭስ አልባ ምድጃዎች፣ ባዮ ጋዝ) |
| | = | ኢኮ-ቱሪዝም፣ ዘላቂ የቱሪዝም ልማት፣ |
| | = | ኢንተርፕራይዝ/ምጣኔ ኑሮ ( Livelihood ) ልማት |

## የማቀናጀት አስፈላጊነት

- በብዝሃ-ህይወት ሃብq ቸው በበለጸጉ የዓለማችን አካባቢዎች የሚኖሩ ቁጥራቸው ከ1.1 ቢሊዮን የሚልቅ ሰዎችን የተቀናጁ ፍላጎቶች ማሟላት ስለሚያስችል፡፡
- በነዚህ አከባቢዎች ያለውን (ሊከሠቱ የሚችሉትን) የሃብትና ማህበራዊ ግጭቶች ለማስወገድ ስለሚያስችል፡፡ በተጠቀሱት አከባቢዎች የህዝብ ቁጥር ዕድገት መጠን በሌላው የዓለማችን ክፍል ካለው አማካይ የህዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ሲነፃፀር በ40 ከመቶ ይበልጣል፡፡
- የተቀናጀ አኗኗር= የተቀናጀ የፕሮግራም ዘዴ፡፡
- ለችግሮች መሰረq ዊ መንስኤዎች መፍትሄዎችን ለማግኘት ያስችላል፡፡
- በቡድኖችና ግለሰቦች መሃከል ያለው ግንኙነት የተሻለ እንዲሆን ያግዛል፡፡
- የተለያዩ ማህበረሰቦችን ፍላጎቶች በአንድ ጊዜ ለማዳረስ ያስችላል፡፡
- ያለው ኢኮኖሚያዊ ስርዓት/ግንኙነት ውጤq ማ ^ንዲሆን፡፡
- በነባር መዋቅሮች ላይ ይገነባል፡፡
- የአብዛኛውን ማህበረሰብ ተሳትፎ ያበረq q ል፡፡
- ቀጥሎ ከተዘረዘሩት እሳቤዎች መነሻነት ቅንጅት ለማምጣት፡፡
    - ማህበራዊ ስርዓቶችና ስነምህዳር ትስስር/ግኑኝነት አላቸው፡፡
    - አንዱን ስርዓት የሚነካ/የሚያቃውስ ክስተት ሌላውን ስርዓት መንካቱ/ማቃወሱ የማይቀር ነው፡፡
    - ባንደኛው ስርዓት የሚኖር መሻሻል (ለወጥ) በሌላኛው ሥርዓት ላይ በጎ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡
    - ሁለቱን ሥርዓቶች ከዉድምት ወደ ጤናማነት ለመመለስ፡፡

## የቅንጅት አይነቶች

- ተጓዳኝ (Paralel)
- የተያያዘ (coordinated)
- ሴክተር-አቀፍ (Bridge)
- የተቀናጀ/ተደጋጋፊ (Symbiotic)

← →

ተጓዳኝ | የተሳሰረ | ሴክተር-አቀፍ | የተቀናጀ/ተደጋጋፊ

1. **ተጓዳኝ፡-** በአንድ አከባቢ ባሉ የተለያዩ ድርጅቶች መሃከል ቅንጅት ሳይኖር የሚከናወኑ ፕሮጅክቶች፡፡

2. **የተሳሰረ፡-** በተወሰነ ደረጃ የቅንጅት ሥራ የሚሰተዋልበት የፕሮጀክቶች አተገባበር፡፡

3. **ሴክተር-አቀፍ፡-** የተለያዩ ሴክቶሮችን ያካተቱ ፕሮጄክቶችን የሚመለከት ሲሆን በነዚህ ፕሮጅክቶች በጽንስሃሳብ ደረጃ ቅንጅት ቢኖርም በአፈፃጸማቸው ግን ተግባራዊ የሆነ ቅንጅት ላይኖር ይችላል፡፡ ለምሳሌ በዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ የሚደገፈው የማዳጋስካር "የተፈጥሮ፣ ጤና፣ ብልፅግና፣ ስልጣን" ማእቀፍ ድርጅቱ የአካባቢ፣ ጤና፣ ምጣኔ-ኑሮንና አስተዳደርን የሚመለከቱ

ፕሮግራሞችንና ሴክተርችን የሚያገናኙ "ድልድዮችን ለመገንባት" (ቅንጅት ለመፍጠር) እየተጠቀመበት ያለ መዋቅር ነው፡፡

4. **የተቀናጀ/ተደጋጋፊ፡-** በጽንሰሃሳብ እንዲሁም በአፈጻጸም የተቀናጁና የሚደጋገፉ (*conceptually and operationally linked*) የተለያዩ ሴክተሮችን ያካተቱ ፕሮጀክቶች፡፡ ለምሳሌ የፊሊፒንስ IPOPCORM ይጠቀሳል፡፡

## የ.ፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት ጣቢያዎችን ለመምረጥ የሚqዩ መመዘኛዎች

### 1. የሥራው አስፈላጊነት (ፍላጎት)

ፒ.ኤች.ኢ የተጎዱትን ከማቋቋም ይልቅ በመከላካል ላይ ያተኩራል፡፡ በአንድ አካባቢ የህዝብ ቁጥር ጫና መንስኤ ምንድን ነው? (የወሊድ መጠን ወይስ ፍልሰት)፡፡ የሰዎች ፍልሰት ከሆነ በዚህ አካባቢ የስነተዋልዶ ጤና ፕሮጀክት ውጤqማ ላይሆን ይችላል፡፡

### 2. ማሕበረሰቡ በፕሮጀክቱ ስራዎች ዉስጥ ለመሳተፍ ያለዉ ፍላጎት

የማሕበረሰቡ አባላት በፕሮጀክቱ ለመሳተፍና አስፈላጊዉን ድጋፍ ለመስጠት ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በዚህ ሂደት የተፈጥሮ ሃብት ክብካቤንና ጤናን በተመለከተ የነባር ማህበረሰብ ዕውቀትና ልማዶች ለመጠቀም ˆድሉ ሊኖር ይገባል፡፡

### 3. ስነ-ህይወqዊ (Biological) ፋይዳ

ስነ-ምህድራዊ ፋይዳቸው የጎላና በህዝብ ቁጥር ጫና ምክኒያት ለሰው ልጆች የሚኖረው የስርዓተ ምህድር አገልግሎቶችና/ቁሳቁሶች (Ecosystem Services/goods) ፍስት አደጋ ውስጥ የሆኑባቸው አካባቢዎች፡፡

<u>የዝርያ አይነት/ብዛት</u>፡- የተለያዩ ዝርያዎች (ዓየነቴዎች) በብዛት የሚገኙባቸውን፣ የስረዓተ-ምህድር ብዙህነትና አገርበቀል ዝርያዎች (Endemicity) የሚገኙባቸውን አካባቢዎች መመረጥ አለባቸው፡፡

ጠቀሜ ｑ፡- በአካባቢው የሚገኙ የጄኔቲክ፣ የዝርያና ስርዓተ ምህድር ሃብቶች ለሰዎችና ለአካባቢዉ የተፈጥሮ ስርዓተ-ምህድር አሁን ያላቸዉ ˆንዲሁም ወደፊት የሚኖራቸው ጠቀሜ ｑ ታመ ｑ የት ይኖርበ ｑ ል፡፡

ስጋት፡- ሌሎች የሃብት ፋይዳዎች ለምሳሌ የውሃ እጥረት፣ የተረጋጋ ዓሣ ሃብት ወዘተ.

ˆላይ የተቀመጡት ሶስት መመዘኛዎች ጠቃሚ ሁነው ካገኘናቸው የሚመረጡት አካባቢዎች ከጥብቅ አካባቢዎች ጋር ካላቸው ቅርበት በተጨማሪም ከሚከተሉት መመዘኛዎች አንፃር መ ｑ የት አለባቸው፡፡

## 4. ሶሺዮ ኢኮኖሚያዊ መመዘኛዎች

**የማሕበረሰቡ አደረጃጀት ሁኔq/ደረጃ:-** *መሠረqዊ ኮሚቴዎች ሊኖሩ ያስፈልጋል::  ካልሆነ አቅም መገንባት::*

**የድህነት መጠን:-** ድህነት በ^ጅጉ የተንሰራፋበት አካባቢ ከሆነ ማሕበረሰቡ በመሰረqዊ የጤና ጉዳዮች ላይ ብቻ ፍላጎት ሊያሳይ ይችላል:: ^ንዲህ ባለ ሁኔq አማራጭ ዘዴዎችን መሞከሩ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል::

**የትምህርት ደረጃ:-** የማህበረሰቡ አባላት መሠረqዊ የማንበብና የመጻፍ ^ንዲሁም የንግድ ሥራ ክህሎት ቢኖራቸው ይመረጣል:: ነገር ግን ይህ የግድ አስፈላጊ አይደለም::

**የመረጃ ተደራሽነት:-** ይህ የማህበረሰቡ አባላት ፕሮጀክቱን በተመለከተ በሚኖራቸው ግንዛቤ ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል:: ለምሳሌ በፊሊፒንስ IPOPCORM እና የ PESCODEV ፕሮግራሞች በተንቀሳቀሱባቸው የባርጠረፍ ማሕበረሰቦች አካባቢ፣ ጤና፣ የቤተሰብ ምጣኔ፣ ፖሊሲዎችንና ህጎችን በተመለከተ መሠረqዊ መረጃ አልነበራቸውም:: የነዚህ ማሕበረሰቦች ህገ-ግንዛቤ አናሳ መሆን የፍትህ ስርዓቱን ለመጠቀም ያላቸውን አቅም ውሱን ^ንዲሆን አድርጎqል::

## 5. ቁሳዊ መመዘኛዎች

**የማሕበረሰቡ ስብጥርና የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት ተደራሽነት:-**

የተፈጥሮ ክብካቤ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች (ለምሳሌ በብዝሃ-ሕይወት የበለጸጉና ብርቅዬ ዝርያዎች በብዛት ያሉአቸዉ አካባቢዎች) ብዙውን ጊዜ ሩቅ፣ በቀላሉ የማይደረስባቸው፣ መሠረqዊ የመንገድና የመገናኛ ዘዴዎች የሉአቸዉም:: በመሆኑም የፕሮጀክት ሠራተኞች ወደነዚህ አካባቢዎች በመመላለስ ቴክኒካዊ ድጋፍ የመስጠት አቅማቸዉ ውሱን ይሆናል::

> ***አስተውሉ:-*** *ፒ.ኤች.ኢን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያከናውኑ ፕሮጀክቶች በእጅጉ የተራቆቱ የስርዓተ ምህድር አካባቢዎችን ወይም "የመጨረሻ ደሃ" ማሕበረሰቦችን በፕሮጀክት ተደራሽነት/ተጠቃሚነት መምረጥ የለባቸውም::*

# የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት ዝግጅት ሂደት ቅደም ተከተል



የፕሮጀክት ማከናወኛ ሃብት ማሰባሰብ

ለፕሮጀክት ማከናወኛ ሀብት ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ እንደ ማዕከላዊ መንግሥት፣ ክልላዊ መንግሥት፣ አጋር ድርጅቶችንና የማህበረሰብ ምንጮችን መፈተሽ

ከሌሎች ጋር ስለሚኖረዉ ድርጅታዊ ግኑኝነት መዋቅር ማዘጋጀት

በአካባቢው ከሚገኙ ድርጅቶች፣ የመንግሥት አካላት፣ የግል ሴክተርና ከዩኒቨርስቲዎች ጋር እንዴት አብሮ መስራትእንደሚቻል መታየት አለበት

ቴክኒካዊ ክህሎቶች የሚገኙበትን መንገድ መወሰን

ድርጅቱ ሙያተኞች የሚቀጥር ከሆነ የቴክኒክ ቡድኖችን እንዴት ማደራጀት እንደሚቻል መወሰን

ቴክኒካዊ ክህሎቶችን ከሌሎች ጋር ትብብር በመፍጠር ለማግኘ ት የሚታሰብ ከሆነ አወቃቀሩ ምን መምሰል እንዳለበት መወሰን

የግለሰቦችንና የድርጅቶችን አቅም ማሳደግ

የአመራር አቅም ለማጎልበት፣ ለሞያ ድጋፍና አቅም ግንባታ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር

ስለ ፕሮጀክቱ ዘላቂነት ማሰብ

- ስልጣን/ውሳኔ ሰጭነት በተዋረድ ማህበረሰባዊ ድርጅቶች ማከፋፈል
- አማራጭ የምጣኔ-ኑሮ መስኮችን መፍጠር

አማራጭ የምጣኔ-ኑሮ መስኮች የሚፈጠሩ ከሆነ ሊኖሩ ስለሚችሉ የኢንተርፕራይዞች አይነት፣ ስለሚያስገኙአቸው ጥቅሞች፣ ስለሚካተቱ ባለድርሻ አካላትና ሌሎች ውጫዊ ጉዳዮች ማስተዋል አስፈላጊ ነው።

ለማስፋፋት መጣር

- ቀጣይነት ያለው የገንዘብ ምንጭ ማፈላለግ።
- ትኩረትን ፕሮጀክት ከማከናወን ባሻገር ብዙሃኑን ባለድርሻ አካላት ወደማነቃቃት ማድረግ።
- የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን መደገፍ።
- የፒ.ኤች.ኢ. እቅድ ዝግጅት አቅምን መገንባት።
- በህግ ተፈፃሚነት ላይ መሥራት።
- በየደረጃዉ አመራር መፍጠር።

## የቡድን ተግባር:- ድርጅqዊ አቅማችሁን መፈተሽ

1. በቡድን በመሆን ቀደም ብሎ በቀረበዉን «የፒ.ኤች.ኢ. ፕሮጀክት ዝግጅት ሂደት ቅደም ተከተል» ቻርት ስር የቀረቡትን ሂደቶች አንደገና በማየት የድርጅቶቻችሁን ፒ.ኤች.ኢ. ፕሮጀክት የማቀድና የማከናወን አቅም ፈትሹ::

   - ድርጅqችሁ የትኞቹን ተግባሮች በአግባቡ ማከናወን ይችላል? (3 ተግባሮች ምረጡ)
   - የትኞቹ ተግባሮች አስቸጋሪ ሆነዉ አገኛችሁዋቸዉ? (3 ተግባሮች ምረጡ)
   - ድርጅqችሁ የትኞቹን ተግባሮች በተመለከተ ጥቂት ተሞክሮ አለው ወይም ምንም ተሞክሮ የለዉም? (3 ተግባሮች ምረጡ)

2. ፍተሻዉን ካከናዎናችሁ በኋላ አሰልጣኙ የሚሠጣችሁን ተጣባቂ የወረቀት ምልክቶች በመጠቀም ውጤቱን አመልክቱ:: ቀጥሎ የቀረበውን የቀለም ኮድ በመጠቀም ዘጠኙን ተጣባቂ ባለቀለም ክብ ወረቀቶች በቻርቱ ላይ ከተዘረዘሩት ተግባሮች ትይዩ ለጥፉአቸው:: ከጎን የድርጅqችሁን ስም ፃፉ::

**የቀለም ኮድ**

ድርጅqችሁ ውጤqማ የሆነባችው ተግባሮች = አረንጓዴ ምልክቶች (3)

አስቸጋሪ የሆኑ እተግባሮች = ቀይ ምልክቶች (3)

ጥቂት ተሞክሮ አለው/ምንም ተሞክሮ የለዉም = ቢጫ ምልክቶች (3)

**የተሰጠ ጊዜ: 20 ደቂቃ**

# ክፍለጊዜ 3፡ ግንዛቤያዊ ሞዴል (Conceptual Model)

## የክፍለጊዜው ዓላማ

- o በአንድ የፕሮጄክት አካባቢ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ (ህዝበ-ነክ፣ ማሕበራዊ፣ አካባቢያዊ) ሃይሎች፤
- o በነኚህ ምክንያቶች ማሃከል ያለውን የመንስኤ ትስስር (casual linkage)

  ዕመን q ዎችን (assumptions) የሚያመለክት ግንዛቤያዊ ሞዴል ማዘጋጀት፡፡

## ከክፍለ ጊዜው በፊት የሚነበቡ ፅሁፎች

- የፒ.ኤች.ኢ ፕሮግራም ዝግጅት ማኑዋል ገጽ 21-24

*ከዚህ በታች ያለው ካርታ በፊሊፒንስ የባህር ዳርቻ ከምግብ ዋስትና እጦት ጋር ግኑኙነት ያላቸዉን ማህበራዊና አካባቢያዊ ነገሮች ያሳያል፡፡ ይህ ካርታ ይህንን ማኑዋል የሚጠቀሙ ሁሉ በአካባቢያቸው ያሉትን ችግሮች በዚህ ዓይነት ካርታ ላይ በማስፈርና በመተንተን የተቀናጁ ፕሮጄክቶችን አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲነድፉ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡*

*በፊሊፒንስ የባህር ዳርቻ ከምግብ ዋስትና እጦት ጋር ግኑኝነት ያላቸዉ ማህበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች*



# የግንዛቤያዊ ሞዴል መሳሪያ ምንነት

አንድ አከባቢ ስላሉ ወሳኝ ሁኔqዎች (Factors) ለማወቅ ጠቃሚ ከሆኑ ዘዴዎች ዉስጥ አንዱ ስለነዚህ ሃይሎች ግንዛቤያዊ ሞዴል (Conceptual Model) ማዘጋጀት ነዉ::ይህ ተግባር በተለይ ˆንደ ፒ.ኤች.ኢ. ላሉ ዘርፈ-ብዙ ፕሮጀክቶች ጠቃሚ ዘዴ ነዉ:: የአ‹ባቢና ጤና ዘርፎችን ትስስር መገንዘብ፤ይህንንም ትስስር ˆንዴት ለማህበረሰቡ አባላት ማሳወቅ ˆንደሚቻል መረዳት አስፈላጊ ነዉ:: ለምሳሌ የደን አያያዝ በዉሃ አቅርቦት ብዛትና ጥራት ላይ ˆንዴት ተጽˆኖ ሊኖረዉ ˆንደሚችል፤ ይህ ደግሞ በተራዉ በአካባቢዉ ህጻናት ጤንነት ላይ ሊኖረዉ ስለሚችለዉ አንድምq መረዳት ሊያስፈልጋችሁ ይችላል::




ግንዛቤያዊ ወይም የሎጂክ ሞዴል ምክንያቶች/ወሳኝ ሁኔqዎች መሃከል ያለውን መሥተጋብር ስዕላዊ በሆነ መንገድ ይገልጻል:: አንድ ግንዛቤያዊ ሞዴል ሶስት ምልክቶችን ያካተqል::

- **ተደራሽ ሁኔq** (Target Condition)፡- በፕሮጄክት ሥራ አማካኝነት ^ንዲለወጥ የምትፈልጉት ሁኔqን ያመለክqል፡፡ ለምሳሌ በአንድ ዉሃከል (watershed) ስር ላሉ የተለያዩ ማሕበረሰቦች የውሃ ንፅህናን በተመለከተ የሚከናወን ተግባር፡፡ ተደራሽ ሁኔqዎች ለአጠቃላዩ የፕሮጄክት ግብ/ራዕይ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ (ላይ በቀረበው ስዕላዊ መግለጫ በቀኝ በኩል ክብ ውስጥ የተመለከቱት ናቸው)

- **ምክንያቶች/ ወሳኝ ሁኔqዎች** (Factors)፡- ተደራሽ ሁኔqዎች ላይ ተፅ^ኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ፖሊሲዎች፣ ባህሪዎች፣ ልማዶች ^ንዲሁም ሌሎች ሁኔqዎች፡፡ ለምሳሌ የአንድ አካባቢ በደን አያያዝና በግብርና ሥራ ጥቅም ላይ የሚውሉ ጸረ-ተባይ ኬሚካሎች የደን ሽፋንን ለመጠበቅ የሚሠራባቸው ብሔራዊ ፖሊሲዎች ሁሉም በውሃ ጥራት ላይ ተፅ^ኖ ሊኖራቸው የሚችሉ ምክኒያቶች ናቸው፡፡

- **ተዛምዶ (Relationship)** ፡- በተደራሽ ሁኔqዎችና በምክንያቶች/ ወሳኝ ሁኔqዎች መሃከል የሚኖር ትስስር፡፡ (ላይ በቀረበው ስዕላዊ መግለጫ በቀስት አማካኝነት የተገናኙ)

አንድ ጥሩ ግንዛቤያዊ ሞዴል፡

- በፕሮጄክት ጣቢያዉ ስላለ ሁኔq በግልጽ ያመለክqል፤
- በተደራሽ ሁኔqው ላይ ተፅዕኖ የሚኖራቸውን ስዉር ግኑኝነቶችን (implicit linkages) ያሳያል፤
- በተደራሽ ሁኔqላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና ግልፅ ስጋቶችንና ቀጥተኛ ያልሆኑ ስጋቶችን ይገልፃል፤
- አስፈላጊ የሆኑ ወሳኝ ሁኔታዎችን ብቻ ያሳያል፤
- ትክክለኛ በሆነ ጭብጥና መረጃ ላይ የተመሠረተ ነው፤
- የቡድን ስራ ውጤት ነው፡፡

*(ማርጎሊስ እና ሳላፍሲኪ 1998፡28)*

# የIPOPCORM ፕሮጄክት ግንዛቤዊ ሞዴል



# የሰበብ/የምክንያት ሰንሰለት ማዘጋጀት



ይህ በፊሊፒንስ ባርጠረፎች አሳ በማስገር ከሚተዳደሩ ማህበረሰቦች ጋር የሚተገበር የ IPOPCORM ፕሮጀክት ግንዛቤያዊ ሞዴል በግቡ ላይ ግልፅ ስጋትና ቀጥተኛ ያልሆነ ስጋት ያላቸው በዛ ያሉ የምክንያት ሰንሰለቶችን ያካተተ ነው፡፡ በዚህ ሞዴል ወስጥ ከቀረቡት በባርጠረፍ አካባቢዎች ለምግብ ዋስትና ችግር ሰበብ ከሆኑት መሰረqዊ ምክኒያቶች አንዱን የምክንያት ሰንሰለት ለይቶ በማውጣት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ አንድአንዶቹ ቀጥተኛ ያልሆኑ ምክንያቶች ማስተካከያ/የማሻሻያ ^ርምጃ ለመውሰድ የተመቹ ናቸዉ፡፡

የቤተሰብ ቁጥር መብዛት በራሱ ለምግብ ዋስትና ችግር መንስኤ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በአንድ ቤተሰብ ዉስጥ በአማካይ ከ5-6 አባላት በሚገኙባቸዉ የፍሊፐንስ ባርጠረፍ ማህበረሰቦች ውስጥ ይህ ሁኔq በቤተሰብ ደረጃ ላለዉ የምግብ ዋስትና አለመኖር ችግር ከሚጠቀሱ ዋነኛ ምክንያች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

በተገኘዉ መረጃ መሰረት አሳ አስጋሪ በሆኑ ገጠራማ ማህበረሰቦች ውስጥ የሴቶች የውልደት መጠን ከመደበኛው የፍሊፒንስ አማካይ የውልደት መጠን የላቀ ነዉ፡፡ በነዚህ አካባቢዎች የቤተሰብ አባላት ቁጥር ከሌላው የፍሊፒንስ ገጠር አካባቢዎች ጋር ሲነፃፀር ለምን ከፍተኛ ^ንደሆነ ያመለክqል፡፡ በገጠራማ አካባቢዎች በህፃናት ትርፈት መጠን (survival rate) ዙሪያ ስላለው መሻሻል የሚያመለክቱ መረጃዎች በአንፃሩ ከመደበኛው ከፍ ለሚለው የቤተሰብ ቁጥር ብዛት ሌላ ምክንያት ያስቀምጣሉ፡፡ አንድአንድ ባለትዳሮች ሕፃናትን «የ^ግዚአብሔር ስጦq» አድርገው ስለሚቆጥሩ በዛ ያለ የቤተሰብ አባላት ቁጥር አላቸዉ፡፡ ^ንዲህ ያለው ምርጫ/አመለካከት ከፍተኛ ለሆነ የውልደት መጠን ምክንያት ይሆናል፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት አለመኖር ለከፍተኛ የውልደት መጠንና የቤተሰብ አባላት ቁጥር መብዛት ሌላኛዉ ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡ የIPOPCORM ፕሮጀክት ሠራተኞች ^ነዚህን ሁለት ምክንያቶች አግባብነት ባለው የመረጃ፣ የትምህርትና ተግባቦት (IEC) ^ንዲሁም የተሻለ የቤተሰብ ምጣኔ ስትራተጂዎችና ተግባሮችን በማከናወን እለመለወጥ የተመቹ ሁኔqዎች አድርገዉ ወስደዋቸዋል፡፡

## የመንስዔ ሰንሰለት ማዘጋጅት




ከላይ የቀረበው የመንስኤ ሰንሰለት ከIPOPCORM የተወሰደ ሲሆን በፊሊፒንስ ባርጠርፍ አካባቢዎች በስርአተ-ምህዳር ጤናና በአሳ አቅርቦት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ግልፅና ቀጥተኛ ያልሆኑ ምክንያቶችን ^ንዲሁም በነዚህ ምክንያቶች/ወሳኝ ሁኔqዎች መሃከል ያለወን ተዛምዶሽ ያመለክqል::

የአካባቢው ማህበረሰብ ኑሮ አሳ በማስገር ላይ መመሥረቱና አሳ አስጋሪዎች ለኑሮአቸው አስፈላጊ የሆነውን ገቢ የማግኘት ፍላጎት ተያያዥ/ተቀራራቢ ወሳኝ ሁኔqዎችን (Proximate Determinants) ያመለክqሉ:: ^ነዚህ ሁኔqዎች በአገሪቱ ባርጠረፍ አካባቢዎች ለሚስተዋለው ገደብየለሽ አሳ የማስገር ተግባር ዋነኞቹ ምክንያቶች ናቸው:: የአሳ ሀብቱ ^የተመናመነ በሄደ ቁጥር ሰዎች ^ንደ ደማሚት፣ ሳይናይድና ጥቅጥቅ ያሉ መረቦችን በመጠቀም አሳ የማስገር ስራቸዉን ለማቀላጠፍ ይሞክራሉ:: ^ንዲህ አይነት የማስገር ዘዴዎች ደግሞ የአሳ ሃብቱን የባሰ

ከማመናመናቸውም በላይ የዛጎል ተሬ (coral reef) ሃብት በማውደም ስርአተ-ምህዳሮቹ ለሰዎች የሚሰጡትን አገልግሎቶችና ቁሳቁሶች ፍሰት ያሳንሱqል፡፡ ውጤቱ በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ የሚኖረው የአሳ አቅርቦት ማነስና የምግብ ዋስትና ችግር መባባስ ይሆናል፡፡ ˆነዚህ ሁኔqዎች ደግሞ ገደብ ያጣዉን የሃብት መመናመንንና የአካባቢ ብክለት አዙሪት ያባብሱqል፡፡

# የኔፓል ፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት ግንዛቤያዊ ሞዴል




የፕሮጀክቱ ራዕይ "ጤናማ ደን - ጤናማ ማሕበረሰብ" የሚል ነው፡፡ ይህ ራዕይ ቀጥሎ በተዘረዘሩት በሶስቱም የፕሮጀክት አላማዎች ላይ ተንፀባርቋል፡፡

1) የቤተሰብ የገቢ ዋስትና
2) የሰዎች ጤና

3) የተረጋጋ የደን ስርዓተ-ምህድር

ፕሮጀክቱ በተጨማሪም "ያለጤንነት ሃብት የለም" የሚል መፈክር አለው

በደንና ሰዎች ጤንንት ላይ ከተጋረጡት ግልጽ ሰጋቶች መሃከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸዉ፡-

- የቤተሰብ ቁጥር መብዛት
- ለኢች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭነት
- የመተንፈሻ አካላት በሽq ዎች መንሰራፋት
- የደን ስርዓተ-ምህድር መራቆትና ከነዚህ ስርዓተ-ምህድሮች የሚገኙ ጥቅሞች መመናመን፡፡

ቀጥተኛ ያልሆኑ ስጋቶች

- በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች አለመኖር፣ በልማድና በዝንባሌ ምክንያት የሚከሰት ከፍተኛ የውልደት መጠን፡፡
- ለቤተሰብ መተዳደሪያ የሚሆን ገቢ ለማግኘት አባወራው ወደ ህንድ በመሄድ የወቅት ሥራ ይሰራል፡፡ አባወራው የኤድስ መከላከያ ዘዴዎች ዕውቀት ስለሌለው ለኤች/አይ/ቪ -ኤድስና ለሌሎች የአባላዘር በሽqዎች ተጋላጭነቱ የከፋ ነው፡፡
- በጭስ መልክ ዕኑስ ቁስ-አካሎችን በማመንጨት የቤት ውስጥ አየር የሚበክሉና የሳንባ ምችና ሌሎች የመተንፈሻ አካላት በሽqዎችን የሚያስከትሉ ባሕላዊ የማብሰያ ምድጃዎች፡፡ ሴቶችና ሕፃናት ከወንዶች ጋር ሲነፃጸር በዛ ያለ ጊዜ ማዕድቤት ውስጥ ስለሚያጠፉ ለዚህ ችግር በተለይ ተጋላጭ ናቸው፡፡
- ገደብ የለሽ የደን ጭፍጨፋና ግጦሽ አጠቃቀም የሚከሰት የደንና የዝርያዎች ውድመት፡፡ የደን ሽፋን በተመናመነ ቁጥር ሰዎች ከደን ስርዐተ-ምህድር የሚያገኙአቸው አገልግሎቶች ^ያነሱ ይመጣሉ፡፡ (ለምሳሌ ለባሕላዊ ህክምና የሚያገለግሉ ዕፅዋት፣ የከብቶች መኖ፣ ያፈር የዝናብ ውሃ የማቆር/የመያዝ አቅም መቀነስ፣ የማገዶ ^ንጨት ችግሮች ይከሰqሉ፡፡ ሰዎች ከስርዐተ-ምህድራቸዉ የሚያገኙት ጥቅም ^ያነሰ በመጣ ቁጥር የበለጠ ጎጂ ዘዴዎችን በመጠቀም ቀሪዉን የደን ሃብት ጥሪqቸውን ለማሟጠጥ ይገደዳሉ፡፡ ይህ ደግሞ ስርዐተ-ምህድሩን የከፋ ጉዳት ጥፋት አዙሪት ውስጥ ይከተዋል፡፡

ይህን ችግር ለመቀየር ምቹ ሁኔqዎችን የሚፈጥሩ አጋጣሚዎች

- የቤተሰብ ምጣኔ ዕውቀትና አገልግሎቶች ^ጥረት/ችግር
- የቤተሰብ ቁጥር መብዛትን የሚያበረqቱ ልማዶችና ዝንባሌዎች (ፍላጎቶች)፤ ባሕላዊ ምድጃዎች
- የኤች.አይ.ቪ. መከላከያ ዘዴዎች ዕውቀት አለመኖር
- ልቅ የደን ጭፍጨፋ

በኔፓል የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት የተከተለዉ ስትራቴጂ

- በስርዓተ-ምህድር አገልግሎቶች ላይ ያተኮረ የአካባቢ ጥበቃ
- የተጠቃሚ ቡድኖችን አቅም መገንባት (በአስተዳደርና ደን አያያዝ ላይ በማተኮር)
- ሕብረተሰብ አቀፍ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት

- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያ ዘዴዎች ትምህርት መስጠት
- ጭስ አልባና ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን ማስፋፋት
- ለሴቶችና ልጃገረዶች መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መስጠት

# ከኔፓል ግንዛቤያዊ መዋቅር (Conceptual Framework)

## የተወሰደ የመንስኤ ሰንሰለት(Casual Chain)




ˆነኚህ ከኔፓል ግንዛቢያዊ ሞዴል የተወሰዱ የመንስኤ ሰንሰለቶች ኑሮአቸው በደን ላይ በተመሰረተ ማሕበረሰቦች ዉስጥ በሰዎችና በስነምህዳር ጤና ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶችን/ወሳኝ ሁኔqዎችን ያመለክqሉ፡፡ በተጨማሪም ለሰዎች የማገዶ፣ የምግብ፣ የመድሃኒት፣ የመኖሪያና የምጣኔ ኑሮ መሠረት ከሆኑ የደን ስርዓተ-ምህድሮች ስለሚገኙ ጥቅሞችና ቁሳቁሶች ዘላቂ አቅርቦት ያወሳል፡፡

## የቡድን ተግባር

## ግንዛቤያዊ ሞዴል ማዘጋጀት

1. ፕሮጀክቶቻችሁ በምን ጉዳዮች ላይ በማተኮር ˆየሰሩ ˆንደሆነ የሚያመለክት ግንዛቤያዊ ሞዴል አዘጋጁ:: በምqዘጋጁት ሞዴል ፕሮጀክቶቻችሁ በተጨማሪ ሊያተኩሩባቸዉ/ሊሰሩባቸው ይገባል ብላችሁ የምqስቡትን ችግሮች/ጉዳች አካቱ::

    - በመጀመሪያ ለአዲሱ ፕሮጀክት ራዕይና አጠቃላይ ግብ አስቀምጡ::
    - ያሉ ምቹ ሁኔqዎችንና ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን አስቀምጡ:: በነዚህ ምቹ ሁኔqዎች/ስጋቶች ላይ በመመስረት የመንስኤ ሰንሰለት አዘጋጁ:: ያሉአቸውን ትስስር ለማመልከት ቀስቶች ተጠቀሙ::
    - ካርዶችንና የወረቀት ነጥቦችን በመጠቀም ሞዴሎቻችሁን ፍሊፐቻርት ላይ አስፍሩ::

2. ፕሮጀክቶቻችሁን የተሻለ ግልጽ ለማድረግ መሟላት ስላለባቸው የመረጃ ክፍተቶች ዝርዝር ነጥቦች አዘጋጁ::

3. ባዘጋጃችሁት ግንዛቤያዊ ሞዴል ላይ በመርዕይ ጉዞ (Gallery walk) ጊዜ ከቡድን አባሎቻችሁ ጋር በመሆን ማብራሪያ ለመስጠት ዝግጁ ሁኑ::

**የተሰጠ ጊዜ: 60 ደቂቃ**

**አስተወሉ፤ በ15 ደቂቃ ውስጥ አሰልጣኙ ያዘጋጃችሁትን ራዕይና ግብ ይመለከqል::**

# ክፍለጊዜ 4፡

# የፕሮጀክት ግቦች ዓላማዎችና ስትራቴጅዎችን ማስቀመጥ

**የክፍላ ጊዜው ዓላማ፡-**

- ከግንዛቤያዊ ሞዴል በመነሳት ቀጥሎ የተዘረዘሩን መለየት፡-
  - ሊስተካከሉ /ሊሻሻሉ የሚችሉ ሁኔqዎችን (ምቹ ሁኔqዎችን)
  - ለqስበው የፒ.ኤች.ኢ. ተግባር የጋራ ግብ
  - ውሱን ዓላማዎች (የአጭር ጊዜ ውጤቶች)
  - የስነህዝብ፣ ጤናና አካባቢ ስራዎችን ለማከናወን የሚያግዙ ስትራቴጂዎች (በተመረጠው የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት ጣቢያ)
  - በፒ.ኤች.ኢ ዘርፎች መሃከል ስላለው ትስስር ዕመንq (assumption) ስዕላዊ መግለጫ (የውጤት ሰንሰለት)

**ከክፍለጊዜዉ በፊት የሚነቡ ጽሁፎች፡-**

- የፒ.ኤች.ኢ ፕሮግራም ዝግጅት ማኑዋል ገፅ 24-27

# የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት ግቦችን ማስቀመጥ

## ግብን በማስቀመጥ ፒ.ኤች.ኢ የሚከተለዉ ፍልስፍና

- ሶስቱ ዘርፎች (ማለትም ስነህዝብ፣ ጤናና አካባቢ) ተደጋጋፊዎች ናቸው።
- በመሆኑም ይህንን ተደጋጋፊነት ያገናዘበ የተቀናጀ ሥራ ማከናወን ያስፈልጋል።
- ግቦቹ
    - ለያንድ አንዱ ዘርፍ
    - ሶስቱንም ዘርፎች የሚያገናኙ (የጋራ ግብ)
    - ለማሕበረሰቡ/ለተጠቃሚዉ ህዝብ
- የተሻለ የልማት ውጤት የሚያመለክቱ ሊሆኑ ይገባል።

## ግብ ሲቀመጥ

- ሶስቱም ዘርፎች አስተዋፅኦ የሚያደርጉለት "የጋራ ግብ" ማመላከት አለበት
- ራዕይ ያለው-አነቃቂና ሩቅ አላሚ ነው
- በጥቅሉ ይቀመጣል
- አጭር (ግልፅ)ና የተመጠነ
- ከሚፈለገው ለውጥ አንፃር መለካት የሚችል መሆን አለበት።

## የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክቶች የጋራ ግብ ምሳሌዎች

- የምግብ ዋስትና
- ድህነት ቅነሳ (የገቢ ዋስትና ማረጋገጥ)
- የተመጣጠነና ዘላቂ ልማት
- የአካባቢ ደህንነትን ያገናዘበ ዘላቂ ልማት
- የሥነምህዳርን ደህንነት ያለዉ ማሕበረሰብ
- ዘላቂ የምጣኔ-ኑሮ ልማት

## ምጡቅ (Gold Standard) የፒ.ኤች.ኢ. ፕሮጀክቶች የተጠቀሙባቸዉ የግብ ምሳሌዎች

**IPOPCORM**

"የባህርማ ስርዓተ-ምህድሮችን (Marine Ecosystem) ብዝሃህይወትና ምርqማነት በመጠበቅ የባርጠረፍ ማህበረሰቦችን (Coastal Communities) የምግብ ዋስትናና የኑሮ ደረጃ ማሻሻል።"

**ኔፓል የፒ.ኤች.ኢ. ፕሮጀክት**

"የኔፓልን የተፈጥሮ ሃብት በዘላቂነት በመንከባከብ በደን ^ንዲሁም በደናማ ስርዓተ-ምህድሮች ዉስጥ የሚኖሩ ማሕበረሰቦችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል።"

## የፒ.ኤች.ኢ. ፕሮጀክቶች ዓላማዎች:-

- ከያንድአንዱ ዘርፍ ስለሚጠበቀው ውጤት ያብራራሉ፤
- አንድን ዓላማ ለማሣካት የምንጠቀምበትን ዘዴ ከማመልከት ይልቅ ምን ማከናወን ^ንደምንፈልግ ይገልፃሉ፤
- በሌላ አጠራር የመሃከለኛ ጊዜ/አማካይ ውጤት (Intermediate Result) በመባል ይqወቃሉ፤
- ወደ አጠቃላዩ ግብ የሚያዳርሱ ውሱን ዓላማዎችን ማስቀመጥ ስራችንን በትጋት ^ንድናቀላጥፍ የሚያግዙ ዓላማዎችን/ግቦችን በግልጽ ከማቅረባቸውም በላይ ውጤqማነqችንን ለመመልከትም ያግዙናል።
- ዓላማዎች "SMART" መሆን አለባቸው። (SMART ከ #Specific, Measurable, Appropriate, Realistic, Time Limited; ከተሰኙ የአንግሊዝኛ ቃላቶች ስብስብ የተፈጠረ ምህጻረ ቃል ነዉ።)

| | | |
|---|---|---|
| Specific | = | ግልጽ (በአንድ ጉዳይ ላይ ያተኮረ) |
| Measurable | = | ሊለካ የሚችል (በቁጥር፤ በመቶኛ) |
| Appropriate | = | አግባብነት ያለው (ግንዛቤያዊ ሞዴሉ ውስጥ ከተቀመጡት ምክንያቶች አንፃር)። |
| Realistic | = | ተግባራዊ ሊሆን የሚችል |
| Time Limited | = | በጊዜ የተወሰነ (በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሊከናወን የሚችል) |

# IPOPCORM ፕሮጀክት፡ 2001 - 2007

***ግብ*** *(የረጅም ጊዜ ውጤት)*

ˆ.ኤ.አ በ 2010

- የባህርማ ስርዓተ-ምህድሮችን ብዝሃ ህይወትና ምርq ማነት በመጠበቅ የባርጠረፍ ማሕበረሰቦችን የምግብ ዋስትናና የኑሮ ደረጃ ማሻሻል:: እ

***ዓላማዎች*** *(የአጭር ጊዜ ውጤቶች)*

- ˆ.ኤ.አ በ2004 በባርጠረፍ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን የስነተዋልዶ ጤና ውጤት ማሻሻል::
- ˆ.ኤ.አ በ2006 የማሕበረሰቡን የባርጠረፍ ተፈጥሮ ሃብት አያያዝ (የምጣኔ-ኑሮ አማራጮችን ያካተተ) አቅም መገንባት::
- በ2007 ሕዝቡና ፖሊሲ አውጪዎች ስለ ፒ.ኤች.ኢ ያላቸውን ግንዛቤና ድጋፍ

ˆነዚህ ዓላማዎች "SMART" ናቸዉ?

# የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክቶች ስትራቴጂ ማዘጋጀት

- የተቀመጠውን ዓላማ ለማሳካት የምንጠቀምበትን ዘዴ ያብራራል::
- ግባችን ላይ ለመድረስ ጥረqችንን/አቅማችንን ˆንዴት መጠቀም ˆንዳለብን ይገልፃል::
- ˆሚፈለገዉ ውጤት ላይ ለመድረስ መውሰድ ስላለብን ˆርምጃዎችና qክቲኮች ለመወሰን ይረዱናል:: ˆነዚህ ˆርምጃዎች/ qክቲኮች የፕሮጀክቱ ክንውኖችና ሁነቶች (events) ይሆናሉ::



የመንስኤ ሰንሰለቶች ዓላማ ላይ ለመድረስ ˆንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ስጋቶችን ለማስወገድ የሚያግዙ ስትራቴጂዎችን በመለየትና ማዘጋጀት ሂደት በጣም ጠቃሚ መሣሪያዎች ናቸው:: በተጨማሪም ቀጥተኛ ባልሆኑ ወሳኝ ሁኔqዎች ምክንያት የሚኖሩትን ምቹ ሁኔqዎች ˆንድንጠቀም ይረዱናል::

በዚህ ስላይድ የIPOPCORM ፕሮጀክት ቡድን በፕሮጀክት ጣቢያዉ በከፍተኛ የውልደት መጠን ምክኒያት የተፈጠረውን ቀጥተኛ ስጋት ˆንዲሁም በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችና ዘዴዎች አለመኖር የተፈጠሩትን ቀጥተኛ ያልሁኑ ስጋቶች ለማስወገድ የመረጠው ስትራቴጂ ባለስድስት ጎን ሳጥን ዉስጥ ቀረቦአል::

በዚህ ተጨባጭ ሁኔq የተመረጠው ስትራቴጂ "አቅም ግንባq ለህብረተሰብ አቀፍ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት " የሚል ነው::

# ስትራቴጂ 2




ይኼኛው IPOPCORM ዓላማውን ለማሳ‹ትና ገደብ የለሽ ጎጂ የአሳ ማስገር ችግርን ለመቅረፍ የተጠቀመበትን ዘዴ ወይም ስትራቴጂ የሚገልፅ ሌላ ምሳሌ ነው::

በአጠቃላይ IPOPCORM በግንዛቤያዊ ሞዴሉ ዉስጥ የተቀመጠዉን ራዕይና ዓላማ ለማሳካት አራት መሠረqዊ ስትራቴጂዎችን መርጧል፡፡

- ህብረተሰብ አቀፍ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት
- ህብረተሰብ አቀፍ የባርጠረፍ ሃብት (ጥሪት) ክብካቤ
- የፖሊሲ አድቮካሲና የማሕበረሰብ መረጃ፣ ትምህርትና ተግባቦት (IEC) ሥራ
- አካባቢን የማይጎዳ የኢኮኖሚ ልማት

ስትራቴጂዎቹ በተጓዳኝ ተተግብረዋል፡፡ ሁሉም ስትራቴጂዎች ለሴክተር ተኮር ዓላማዎች ˆንዲሁም ለአጠቃላዩ ፕሮጀክት የጋራ ግብ አስተዋጽኦ ˆንዲያደርጉ ሆነዉ ተዘጋጅተ ”G ፡፡

## የፕሮጀክት ቡድን ተግባር:- ግብ-ዓላማ-ስትራቴጂዎች

1. የፒ.ኤች.ኢ. ፕሮጀክqችሁ በረጅም ጊዜ ሊያስገኘዉ ስላለመዉ ዋና ውጤት የሚገልጽ የጋራ ግብ ረቂቅ አዘጋጁ::

2. ፕሮጀክቱ የሚያከናዉናቸዉ ለሁሉም አብይ የፒ.ኤች.ኢ. ምሰሶዎች (ዘርፎች) የጋራ ግብ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ቢያንስ አንድ ዓላማ አዘጋጁ:: (ነባር የፕሮጀክት ዓላማዎች ከአዳዲሶቹ የፕሮጀክት ዓላማ(ዎች) አንፃር ሊጠናከሩ ይችላሉ)

## የፒ.ኤች.ኢ. ምሰሶዎች

ፒ(P) = ስነህዝብ/የቤተሰብ ምጣኔ (አራርቆ መውለድ፣ የልጆችን ቁጥር መወሰን፣ አስቸካይ የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም፣ የአዋቂዎች ስነተዋልዶና ቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች)

ኤች(H)= ጤና ለምሳሌ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ የመተንፈሻ አካላት በሽqዎችን መከላከል፣ ንጹህ ዉሃ አቅርቦትና ጤና አጠባበቅ፣የወባ በሽqን መከላከል፣ መሠረqዊ የጤና አገልግሎ፣ የሕፃናት ትርፈት::

ኢ(E) = የአካባቢ ክብካቤ፣ የተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ የአሳ ሀብት አያያዝ፣ የደን አያያዝና አስተዳደር፣ ሊጠፉ የተቃረቡ ዝርያዎች ክብካቤ ወዘተ.

3. ^ያንዳንዱ ዓላማ ላይ ለመድረስ የምትጠቀሙበትን ስትራቴጂ (ዘዴ) አስቀምጡ::

4. ስራዎቻችሁን በፍሊፕቻርት ለማዘጋጀትና ለማቅረብ በቀጣዩ ገጽ የቀረበውን ቅጽ (ፎረም) ተጠቀሙ:: በዋናዉ የዉይይት ጊዜ በቀላሉ ለማጣቀስ ^ንዲቻል ስራዎቻችሁን ግድግዳ ላይ አስቀምጡ::

**የተሰጠ ጊዜ: 60 ደቂቃ**

# የጋራ ግብ ማስቀመጥ

- የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክቶቻችሁን ግብ፣ ዓላማና ስትራቴጂ ቅደም ተከተል ማቅረቢያ ቅጽ/ፎርም



# ምሳሌ፡- በኔፓል የፒ.ኤች.ኢ. ፕሮጄክት



# የውጤት ሰንሰለቶች

- በሞዴሉ ውስጥ ባለ አንድ ሰንሰለት ላይ አትኩሩ



## የውጤት ሰንሰለት ምሳሌ

## የውጤት ሰንሰለት ቁጥር 1

### የአካባቢ ክብካቤ ውጤት ለማግኘት የሚከናወን የቤተሰብ ምጣኔ ሥራ




**ክንዉን፡-** የማሕበረሰብ አባላት በወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ላይ ስልጠና በመውሰድ የሚሳተፉበት በማህበራዊ ግብይት አማ‹ኝነት የሚከናወን ሕብረተሰብ አቀፍ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች ስርጭት(CBD)፡፡

**የውጤት ሰንሰለት ቁጥር 2**

**በአካባቢ ጥበቃ ውጤት ላይ ያተኮረ መሠረqዊ ጤና አገልግሎት**




**ክንዉን፡-** ቡድናችሁ በመንደሩ የሚከሰት አደጋን ሊቀንስ የሚችል የመሠረqዊ ጤና አገልግሎት መጥቀስ ይችላል?

## ውጤት ሰንሰለት ቁጥር 3

በአካባቢ ክብካቤና በሰዎች ጤና ላይ  ያተኮረ የመሠረተ ትምህርት ክንዉን




**ክንውን፡-** ስለማሕበረሰብ ደን አያያዝ፣ ቤተሰብ ምጣኔና ፒ.ኤች.ኢ. መረጃ ያካተተ ለሴቶችና ለልጃገረዶች የሚሰጥ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (NFC)

## የውጤት ሰንሰለት ቁጥር 4

## በአካባቢ ክብከቤ ውጤት ላይ ያተኮረ የንፁህ ኢነርጂ ክንውን




**ክንውን፡-** ጭስአልባና ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን አቅርቦት መጨመር

# የጥሩ ውጤት ሰንሰለቶች መመዘኛዎች

- ***ውጤት ተኮር፡-*** ሳጥኖች ውስጥ ማስፈር ያለብን ማየት የምንፈልገውን ውጤት ነዉ፡፡ ለምሳሌ "የውልደት መጠን መቀነስ"፡፡ በተቃራኒዉ "አቻ ትምህርት ማከናውን" የሚለዉ ድርጊት የሚያመለክት አቀራረብ በመሆኑ የጥሩ ውጤት መመዘኛን አያሟላም፡፡

- ***ምክንያታዊ ትስስር የሚያመለክቱ፡-*** በተከታታይ ሳጥኖች መሃከል ግልጽ የሆነ ምክንያታዊ ትስስር መኖር አለበት፡፡

- ***የተሟላ፡-*** በምክኒያቶች መሃከል ያለውን ሎጂካዊ ግኑኙነት ለማመልከት በቂ ሳጥኖችን መጠቀም፡፡

- ***ግልጽ***- በአንድ ሳጥን አንድ ውጤት ማመልከት፡፡

- ***ለውጥ አመልካች፡-*** ሳጥኖች ምክንያቶች/ወሳኝ ሁኔታዎች እንዴት እንደሚጨምሩ (እንደሚሻሻሉ)፣ እንደሚቀንሱ ወይም እንደሚለወጡ መግለጽ አለባቸው፡፡

## የፕሮጀክት ቡድን ተግባር፡- የውጤት ሰንሰለቶች ማዘጋጀት

1. ከወጠናችሁት ፕሮጀክት አንድ የአላማ ስብስብ (ግብ-አላማ-ስትራቴጂ) ምረጡ፡፡

2. ካዘጋጃችኋቸው አላማዎችና የግንዛቤያዊ ሞዴል በመነሳት 1 ወይም 2 ክንውኖችን አዘጋጁ፡፡ እነዚህ ክንውኖች የሚፈለገውን ውጤት እንዴት እንደሚያስገኙ የውጤት ሰንሰለት በማዘጋጀት ፈትሹአቸው፡፡ (*ጥቆማ፡ በዛያሉ ተጽእኖዎች* (Impacts) እና በእነዚህ ውጤቶች መሃከል ተደጋጋፊነት እንዲኖር እንደምትፈልጉ አስታውሱ)፡፡

3. የተሻለ ነው ብላችሁ የምታስቡትን ክንውን በመምረጥ የዚህን የውጤት ሰንሰለት በተሰጣችሁን ካርድ በመጠቀም ፍሊፕቻርት ላይ አስፍሩ፡፡

*ማስታወሻ፡- ሁለት ሰንሰለቶች ለማዘጋጀት ሞክሩ*

ሰንሰለት 1፡ የተፈጥሮ ሃብት ክብካቤ ውጤት ላይ ያተኮረ የስነ-ህዝብ ክንውን

ሰንሰለት 2፡ የተፈጥሮ ሃብት ክብካቤ ውጤት ላይ ያተኮረ የጤና ክንውን ወይም ምጣኔ ኑሮ ውጤት ለማግኘት የሚተገበር የተፈጥሮ ሃብት ክብካቤ ክንውን፡፡

**የተሰጠ ጊዜ፡ 45 ደቂቃ**

### ውጤት ሰንሰለት ማዘጋጀት ቅጽ/ፎርም



# ክፍለጊዜ 5፡ የፒ.ኤች.ኢ ክንውን (Intervention) መምረጥ

**የክፍለጊዜው ዓላማዎች፡-**

- በግንዛቤያዊ ሞዴሉ ላይ በመመስረት
  - የስነህዝብ፣ ጤናና የአካባቢ ተግባሮችን ተያያዥነትና ተደጋጋፊነት ያገናዘቡ ክንውኖች መለየት/መምረጥ

**ከክፍለጊዜው በፊት የሚነበቡ ጽሁፎች**

- መረጃ-ደገፍ የፒ.ኤች.ኢ ክንውኖች (በዚህ _____ (tab) ክፍል ቀርቦአል)

## የክንውን አይነቶች

ሶስት ዋና ዋና የፒ.ኤች.ኢ ክንውን አይነቶች አሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ፕሮጀክቶች ጥንድ ወይም ሶስቱን አይነቶች ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

1. **ነጠላ ሴክተር (Single Sector )፡-** በአንድ ሴክተር አላማ ላይ ተጽዕኖ/ውጤት ለማስገኘት ያነጣጠረ ክንውን፡፡

   ምሳሌ፡- በሕፃናት ትርፈት (Child Survival) ላይ ያነጣጠረ የኩፍኝ ክትባት፡፡

2. **እሴት ጨማሪ (value added)** ፡- ክንውኑ በአንድ ዘርፍ ላይ ያነጣጠረ ቢሆንም በሌላ ዘርፍ ላይ እሴት ሊጨምር (ዉጤት ሊኖረዉ) ይችላል፡፡

   ምሳሌ፡- የተሻሻሉ የማብሰያ ምድጃዎችን መጠቀም የደን ጭፍጨፋን ለመቆጣጠር ከመረዳታቸዉ በተጨማሪ ጊዜ-ስለሚቆጥቡ ለተጠቃሚዎቹ ማሕበራዊ ፋይዳ አላቸዉ፤ በተጨማሪም የመተንፈሻ አካላት በሽታን ስለሚከላከሉ የጤና ፋይዳ አላቸው፡፡

3. **የተሳሰሩ/የተያያዙ (Linked)**፡- ይኸኛው በተጨማሪም የተቀናጀ ክንውን በመባል ይታወቃል፡፡ እነዚህ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሴክተሮች ላይ በማተኮር የሚተገበሩ ክንውኖች ሲሆኑ በጽንሰሃሳብ እንዲሁም በገቢር የተቀናጁ ናቸው፡፡ የነዚህ ክንውኖች ውጤት ከሚጠበቀው አንድ ዉሱን ሴክተር ባሻገር ይታያል፡፡

   ምሳሌ፡- ከግብርና ክንውን (የኮምፖስት ዝግጅት) ጋር የተያያዘ የአካባቢ ንጽህና ክንውን (ኦርጋኒክ ቆሻሻ ማስወገድ ሥራ)፡፡ ይህ ክንውን በመንደሩ ንጽህና ላይ እንዲሁም በአዝርእት ምርት ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል (ሁለቱም በክንዉኑ መተግበር የሚጠበቁ ዉጤቶች ናቸዉ) ፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ በሕፃናት ስነ-ምግብ (Nutrition) ሁኔታ ላይ የማይጠበቅ ውጤት ይኖረዋል፡፡

በተቻለ መጠን እሴት የሚጨምሩና በቅንጅት የተሻለ ውጤት የሚያስገኙ ክንውኖችን መምረጥ አለባችሁ፡፡

## የክንውን ደረጃዎች

ክንውኖች በተለያየ ደረጃ ስለሚሠሩ በየደረጃው ያሉ ተጠቃሚዎችን (ታዳሚዎች) መለየት አስፈላጊ ነው፡፡

- **የግለሰብ ደረጃ ክንውኖች፡-** እነዚህ ክንውኖች በአንድ ግለሰብ ላይ ያተኮሩ ሲሆን እውቀትን፣ አመለካከትን፣ እምነትንና የራስን ብቃት ለመለወጥ/ በማሻሻል ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

- **የቡድን ደረጃ ክንውኖች፡-** በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦችን ባህርይ፣ እውቀት፣ አመለካከት፣ እምነትና ብቃት ለመለወጥ ያለሙ ክንውኖችን ይመለከታል፡፡

  እንደዚህ አይነት ክንውኖች በሰለጠነ አመቻች አማካይነት በሚቀርቡ መረጃዎችና ተግባሮች በቡድን አባላት አማካኝነት በሚደረግ ድጋፍና ጫና የግለሰቦችን ባህርይ ለመለወጥ ይጠቅማሉ፡፡

- **የማሕበረሰብ ደረጃ ክንውኖች፡-** የአንድን ማሕበረሰብ/ ተጠቃሚ ህዝብ አመለካከት፣ ልማድና እሴት ለመለወጥ፤ እንዲሁም ማሕበራዊና አካባቢያዊ የባሕርይ አዉዶችን (context) ለመለወጥ የሚተገበሩ ክንውኖች ናቸዉ፡፡

- **መዋቅራዊ ክንውኖች፡-** የምንገኝበትን ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መዋቅሮችና ስርዓቶች ለመለወጥ ያለሙ ክንውኖች ናቸው፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ክንውኖች በሕግ፣ በብዙሃን መገናኛና በገቢያ (በኢኮኖሚ) ሁኔታዎች ላይ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል፡፡ መዋቅራዊ ክንውኖች ሰዎች የሚኖሩበትን፣ የሚሠሩበትና፣ የሚዝናኑበትን ወዘተ. አካባቢዎች/ሁኔታዎች በቀጥታ ይለወጣሉ፡፡

## የክንውን ደረጃዎች ሰንጠረዥ

*በግል የሚከናወን ተግባር :- ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ክንውኖች ደረጃ በተገቢው የሰንጠረዥ ክፍል (ሳጥን) ምልክት በማድረግ ለዩ::*

| ክንውን | ግለሰብ | ቡድን | ማሕበረሰብ | መዋቅር |
|---|---|---|---|---|
| ፖሊሲ አድቮከሲ | | | | |
| የቤተሰብ ምጣኔ/የስነተዋልዶ ጤና የአቻ ትምህርት | | | | |
| ሕብረተሰብ አቀፍ የወሊድ መቆጣጠሪያ ስርጭት | | | | |
| የወጣቶች ስነምህዳር ካምፕ(Youth Ecology Camps) | | | | |
| ተሳትፎዓዊ የባርጠረፍ ሃብት ዳሰሳና ካርታ ዝግጅት | | | | |
| ጥብቅ የአሳዎች መናሃሪያ መከለል | | | | |
| ሳይናይድ (ኬሚካል ) በመጠቀም የሚከናወን የአሳ ማስገር ተግባርን የሚከለክል የአካባቢ ደንብ ማውጣት | | | | |

# መረጃ-ደገፍ ክንውኖች ምንድን ናቸው? ለምንስ ያስፈልጋሉ?

- መረጃ-ደገፍ ክንውኖች በሙከራ ጥናት ወይም በጥልቅ ግምገማ ውጤqማነqቸው የተረጋገጠ ተግባሮች ናቸዉ::
- የፒ.ኤች.ኢ. ፕሮጀክቶቻችሁ ውጤqማነት የተሻለ ^ንዲሆን ያደርጋሉ::
- የፕሮጀክት አመራር ከሌሎች ተሞክሮ በመውሰድ/በመማር የተሻለ ስራ ለማከናወን ያስችላሉ::

ቀጥሎ ባሉት ገፆች የተዘረዘሩትን የመረጃ-ደገፍ ክንውኖች ዝርዝር ሰንጠረዥ ተመልከቱ::

| ችግር/ሰጋት<br>ምቹ ሁኔq | ውሱን/ተጨባጭ ዓላማ | ክንውን/ስትራቴጂ | ተግባር | ውጤት<br>ተፈላጊ የባህሪ/ማሕበራዊ ልማድ ለውጥ |
|---|---|---|---|---|
| **ሰ.** ከስነህዝብ/ስነ ተዋልዶ ጤና ጋር የተያያዙ | | | | |
| በመዉለድ ዕድሜ ክልል ያሉ ሴቶች ከፍተኛ የዉልደት መጠን | የተጠቃሚዉን ማህበረሰብ ስነ ተዋልዶ ጤና ሁኔq ማሻሻል | ቤተሰብ ምጣኔ፣ አራርቆ መዉለድ | ሕብረተሰብ አቀፍ የወሊድ መቆጣጠሪያ ስርጭት ስርዓት መዘርጋት<br><br>ማህበረሰቡ ስለ ወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ያለዉን ሃሜትና ትክክለኛ ያልሆነ ግንዛቤ ለማስወገድ ለአቻ መምህራን ስልጠና መስጠት | ባለትዳሮች/ጥንዶች ከሕብረተሰብ አቀፍ የወሊድ መቆጣጠሪያ ሰራተኞች ድጋፍ ይሻሉ፤ የሚወልዱትነ ልጆች ቁጥር ለመወሰን ወይም ለማራራቅ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በመደበኛነት በትክክል ይጠቀማሉ |
| | | ጡት ብቻ የማጥባትን ባህል ማስፋፋት | በማህበረሰቡ ዉስጥ የጡት ማጥባት ድጋፍ ቡድኖችን ማ ም | ሕጻናት በተወለዱ ^ስከ ስድስት ወር ድረስ ጡት ብቻ የማጥባት ልማድ ይስፋፋል |
| | | ከወሊድ በኻላ የወሊድ መቆጣጠሪያ መረጃና አገልግሎት አቅርቦት | መዉለድ ለተቃረቡ ነፍሰጡር ^ናቶች ትምህርት መስጠት | ^መጫቶች በወለዱ በሶስት ወራቸዉ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች በትክክል ይጠቀማሉ |
| በጎልማሶችና በወጣቶች ላይ የሚከሰት የኤች.አይ.ቪና ሌሎች አባለዘር በሽqዎችን መከላከል | ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የተጠበቁ ሰዎችን ቁጥር በፍጥነት መጨመር | የኤች.አይ.ቪና ሌሎች አባለዘር በሽqዎች መከላከያ ትምህርት መስጠት | ለጥቃት ለተጋለጡ ቡድኖች ሕብረተሰብ አቀፍ የሆነ የአቻ ትምህርት መስጠት | ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎች ለአደጋ ተጋላጭ የሚያደርጉ ባህሪዎችን መቀነስ በተለይም እንደ በአንዴ ብዙ የግብረስጋ ጓደኛ መመስረት ፤ መከላከያ ሳይጠቀሙ ግብረስጋ ማድረግ፤ መርፌ ወይም ሲሪንጅ በጋራ መጠቀም እና የሴተኛ አዳሪነት ያሉ ባህሪዎችን መቀነስ |
| | | የኮንዶም አቀርቦትንና አጠቃቀም ማስፋፋት | ሕብረተሰብ አቀፍ የሆነ የኮንደም ስርጭት ማከሄድ | ትክክለኛና የማያቋርጥ የኮንደም አጠቃቀም ከሁሉም የግብረስጋ አጋር ጋር |
| | | በቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የደም ምርመራና የምክር አገልግሎት | በቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የደም ምርመራና የምክር አገልግሎት ጣቢያ ማቋቋም እና ፈቃደኞችን በምክር አገልግሎት እና በአደጋ ቅነሳ ዙሪያ ስልጠና መስጠት | ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎች የኤች.አይ.ቪና ሌሎች አባለዘር በሽqዎች ላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ማገኘት፤ የክትትል የምክር አገልግሎት ማግኘት እንዲሁም የህክምና ፕሮቶኮልና የአደጋ ቅነሳ ምክሮችን ተግባራዊነት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የኤች.አይ.ቪና ሌሎች አባለዘር በሽq ምልክቶች ያለባቸውን ሰዎች ለመለየትና ለመርዳት የሚያስችሉ አልጎሪዝምና የአደጋ አሰሳ ተክኒኮች ዙሪያ የጤና ሰራተኞችን ማሰልጠን | ለኤች.አይ.ቪና ሌሎች አባለዘር በሽqዎች ተጋላጭ የሆኑ ባህሪዎች ያሏቸው ሰዎች ስልጠና ከወሰዱ የጤና ሰራተኞች ተገቢ የሆነ እንክብንቤ መሻት እንዲሁም የኮንደም አጠቃቀምን ጨምሮ የህክምና ሂደቶችን ተግባራዊ ማድረግ፡፡ |

| ችግር/ስጋት<br>ምቹ ሁኔq | ውሱን/ተጨባጭ<br>ዓላማ | ክንውን/ስትራቴጂ | ተግባር | ውጤት<br>ተፈላጊ የባህሪ/ማሕበራዊ<br>ልማድ ለውጥ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| ለመጥፋት የተቃረቡ ዝርያዎች ህገወጥ ዝዉዉር | ለመጥፋት የተቃረቡ የ`ንስሳትና ዕጽዋት ዝርያዎች ጥበቃ | ጥብቅ አካባቢዎችን ማቋቋም፣ የብርቅዬ ዝርያዎችን ... ማገድ | ስጋት ላይ የወደቁ የእንስሳት ዝርያዎች መያዝ ማዘዋወር እን መሸጥን የሚያግድ የፖሊስ ማዕቀፍ እንዲወጣ መለፈፍ | ስጋት ላይ የወደቁ የእንስሳት ዝርያዎች ዝውውር እና ሽያጭ ማክተም |
| | | ደንብ/ህግ ማስፈጸም | ህገወጥ አደን እና ስርቆትን ለመከላከል የማህበረአቡ አባለት በማሰልጠን የወጡትን ህጎች በማስፈፀም ምዡላቸወን እገዛ እንዲያደርጉ ማስቻል | የአካባቢው ማህበረሰብ ስለ «ስጋት ላይ የወደቁ የእንስሳትዝርዎች» ነባርና አዲስ የሚወጡ ህጎችን በማስተግበር ሙሉ በሙሉ መተባበር |
| የደን ጭፍጨፋ | የመካነ-ህይዎት ማገገም | ህብረተሰብ አቀፍ የደን ክብካቤ | ደን ሀብት ተጠቃሚዎችን በማደራጀት እና ስልጠና በመስጠት የጥብቅ ደን ቦታ የአስተዳደር ስርዓት እንዲዘረጉ እና እንዲተገበሩ ማስቻል | የደን ሀብት ተጠቃሚ አባላት የጥብቅ ደን አስተዳደር ሥርዓት በሚያዘው መሠረት እንዳያገልና ቦታ ከንኪኪ ነፃ ማድረግ |
| የደን ብዝሃ-ህይወት መመናመን | የብዝሃ ህይወት ክብካቤ | ዘላቂ የደን ሃብት ክብካቤ/አያያዝ | ስለ ችግኝ አዘገጃጀት ለማህበረሰቡ አበላት ስልጠና በመስጠት የተለያዩ የእፅዋት ዝርያዎችን በማፍላት ለደን ልማት ስራ ማዋል | ጓቃደኛ የሆኑ የማህበረሰብ አባላት በችግኝ ተከላ ላይ መሳተፍ |
| | | የአማራጭ ሃይል አጠቃቀምን ማስፋፋት (የተሻሻሉ የማብሰያ ምድጃዎች፣በፀሃይ ሃይል የሚሰሩ መብራቶች፣ ባዮጋዝ ወዘተ.) | ለማብሰያና ለመብራት የሚሆኑ የተሻሻሉ የማብሰያ ምድጃዎች እና ባዮጋዝ ማስተዋወቅ፤ የፋይናነስ እገዛ ማድረግ | እያንዳንዱ አባዎራ በየበ ታቱ የተሸሻሉ ምድጃዎች ባዮጋዝ ወይም የጸሐይ ብርሐን የሐይል ምንጭ በመገንባትና በመጠቀም ከደን የሚገኝ ማገዶ መጠቀም መቀነስ |
| | | ከመጤ ዕጽዋት ብሪኬት ማምረት | ለመንደር ነዋሪዎች ከወራሪ አረሞችና በአከባቢ ከሚገኙ ሌሎች ቁሶች የተጋገሩ ማገዶ እንዲያመርቱና እንዲሸጡ ስልጠና መስጠት:: | አርሶ አደሮችና ድርጅቶቻቸው የተሻሻለ የመሬት አጠባበቅ ዘዴዎችን ስለሚተገብሩ ምርታማነት ይጨምራል፣ የአፈር መሸሸርሸር ይቀንሳል፣ የጨፌ መሬቶችን ለእርሻ ማፋሰስ ይቀንሳል:: |
| የረግረጋማ መሬት ዉድመት | የተቀናጀ የረግረጋማ መሬት ዉሃከል ክብካቤ | | በሸቲሸርና በመኖ ተክሎች የተደገፉ ቁ ላሳዊና ስነ ህይወታዊ የውሀና የአፈር ጥበቃ ስራዎች በእርሻና በተዳፋት መሬቶች ላይ ይሰራል፤ | አርሶአደሮችና ድርጅቶቻቸው የተሻሻለ የመሬት አጠባበቅ ዘዴዎችን ስለሚተገብሩ ምርታማነት ይጨምራል፣ የአፈር መሸሸርሸር ይቀንሳል፣ የጨፌ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | መሬቶችን ለእርሻ ማፋሰስ ይቀንሳል:: |

| ችግር/ሰጋት<br>ምቹ ሁኔq | ውሱን/ተጨባጭ<br>ዓላማ | ክንውን/ስትራቴጂ | ተግባር | ውጤት<br>ተፈላጊ የባህሪ/ማሕበራዊ<br>ልማድ ለውጥ |
|---|---|---|---|---|
| **ሐ. አከባቢ/ሃብት ጋር የተያያዙ** | | | | |
| ዘወትር ደን በመቁረጥና በመጨፍጨፍ የሚከናወን የግብርና ስራ | ዘላቂ ምጣኔ-ኑሮ | የጥብቅ አካባቢዎች አስተዳደር | የአካባቢውን የደን ሀብት ተጠቃሚዎች በማደራጀትና በማሰልጠን ከፍተኛ የብዝሐ ህይወት ሀብት ያላቸው ቦታዎች እንዳይመነጠሩ ወይም እንዳይጠፋ ማድረግ | የደን ሀብት ተጠቃሚ አባላት ከጥብቅ አካባቢዎች አስተዳደር ስርዓት ጋር ተጣጥሞ መስራት |
| የባህር ዳርቻ አሳ ሀብት መ ጠጥ | ከባህር በሚገኙ ሃብቶች የምግብ ዋስትናን ማሻሻል | አማራጭ የገቢ ማስገኛ | የባህር አረም የማምረት ልምድን ማምጣትና የገበያ ሁኔታ በማደራጀት መርዳት | አማራጭ የገቢ ምንጭ ላይ ማተኮር እና የዓሣ ማስገር ሥራ መቀነስ |
| | | የባርጠረፍ/ አሳ ሃብት አያያዝ | ከማህበረሰቡ ጋር በመተባበር የባህር ዳርቻዎች ጥብቅ ቦታ መከለል የአሣ እና የማንግሩቭ ጥብቅ ቦታዎችንም መከለል | የባህር ዳርቻ ቦታ ነዋሪዎች በጥብቅ የባህር ዳርቻዎች ላይ የሚያድጉት የዓሣ ማስገር እና የተፈጥሮ ሀብት መመናመን በመታቀብ ለጥበቅ ቦታው እንክብካቤና ጥብቃ እገዛ ማድረግ |
| የአፈር መሸርሸር | ዘላቂ ምጣኔ-ኑሮ<br><br>የአፈር ጥበቃ | ከኦርጋኒክ ቆሻሻ ማስወገድ ስራ ጋር የሚከናወን የኮምፖስት ዝግጅት<br><br>የመሬት ካርq ዝግጅት በዞን መሸንሸን<br><br>በግብርና ምክንያት የተጎዳን አፈር ለምነት ለመመለስ አግሮፎረስትሪ ማካሄድ | የበ ₂ት ውስጥ ጥራጊ እና ቆሻሻን እንዴት ወደ ኮሚፖስትነት እንደሚቀየር እያንዳነዱን የበ ₂ተሰብ አበላት ስልጠና መስጠት<br><br>ከመጠን በላይ በአንድ ቦታ ላይ ግጦሽ እንዳይከሄድ ከብቶችን መመጠን ወይም ወደ ሌላ የግፑሽ ቦታ ማዛወር | የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባላት ጥራጊንና ቆሻሻን ወደ ኮምፖስትነት በመቀየር ለእርሻ ግብአትነት በመጠቀም የአፈሩን ሁኔታ በማሻሻል ምርትን ማሳደግ<br><br>ማህበረሰቡ ከተቀመጠው የግጦሽ ክልከላ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ከብቶቻቸውን ማስጋጥና የማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶች የግጦሽ ቦታዎች ክለላ ተግባራዊ እንዲሆን እገዛ መስጠት :: |
| | | | በእርሻ ማሳዎች ውስጥ ከአዘርት ሰብል ጎን ለጎን የሞሪንጋ ዛፍን መትከልና በትንሽ ቦታ ላይ ከፍተኛ ምርት ማምረት | አርሶ አደሮች በማሳቸው ውስጥ የሞሪንጋ ዛፍን መትከል |

| ችግር/ሰጋት<br>ምቹ ሁኔq | ውሱን/ተጨባጭ<br>ዓላማ | ክንውን/ስትራቴጂ | ተግባር | ውጤት<br>ተፈላጊ የባህሪ/ማሕበራዊ<br>ልማድ ለውጥ |
|---|---|---|---|---|
| **መ. ኢኮኖሚያዊ** | | | | |
| ኑ[ቸዉ የተፈጥሮ ሃብት በማዉጣት ላይ የተመሰረተ ሰዎችና ማህበረሰቦች ድህነት | ዘላቂ ምጣኔ-ኑሮ ልማት | የፒ.ኤች.ኢ ቅንጅትን ^ንደ ዘላቂ ምጣኔ-ኑሮ ዘዴ ማስፋፋት | ፖሊሲ አውጪዎችን ያተኮረ የፖሊሲ በህዝብ በጤናና በተፈጥሮ ሀብት ትስስርና አስፈላጊነት ላይ ለፈፋ ማድረግ፤ | ፖሊሲ አውጭዎች የህዝብ የጤናና የተፈጥሮ ሀብት ትስስርን በአከባቢ ጥበቃ ፖሊስዎች ውስጥ ያካትታሉ፤ |
| | | | በህዝብ በጤናና በተፈጥሮ ሀብት ትስስር ችግሮችና መፍትሄዎች ዙሪያ ፤ባህላዊና ዘመናዊ መገናኛ ብዙሃኖች እንዲሁም የተፈተሸ መልእክቶችን በመጠቀም በአከባቢው ቋንቋ የኢንፎርሜሽን ዘመቻ ማከሄድ | ስለ ህዝብ ጤናና የተፈጥሮ ሀብት ትስስር እንዲሁም የቤተሰብ ብዛት ምጣኔ አስፈላጊነት እና በአከባቢ ጥበቃ የተፈጥሮ ሀብቶችና ስርአተ ምህዳር ዘለቂታዊነት መረጋገጥና ለመጭው ትውልድ ግልጋሎት መዋል እንደሚቻል፤ የኑሮ እና የገቢ ምንጫቸው በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጥገኛ የሆነ የህብረተሰቡ አባላት የተሸለ ግንዛቤ ማግኘት |
| | የተሻሻለ የቤተሰብ አስተዳደር | ^ንደ ቤተሰብ በጀት ዝግጅት ያሉ የተቀናጁ የመማር ዘዴዎችን/ መሳሪያዎችን መጠቀም | ይህ ስራ ጥንዶች ዝቅተኛ የተመጣጠነ ምግብ ፍላጎት የሚዳስሱበትና ቀስ በቀስ የምግብ ፍጆታን ፣ወጭውንና የህንን ለቤተሰብ አባላት የሚያስተምሩበት ተግባርት ነው | የጥንዶች ግንዛቤ በቤተሰብ ብዛትና ተያያ ዥ የስራ ጫና ላይ ይዳብራል፡ ስለዚህም በቤተሰብ ምጣኔ ላይ የአስተሳሰብ ለውጥ ያመጣሉ፣ ዘዴዎችንም ይተገብራሉ፡፡ |
| | የምጣኔ-ኑሮ አማራጮችን ማስፋፋት | አ‹ባቢን የማይጎዳ ኢንተርፕራይዝ ልማት፣ አነስተኛ ብድር አቅርቦትና ገበያ ማመቻቸት | አማራጭ የኑሮ ሁኔታ ማሳደጊያ የስራ ዘዴዎችን መፍጠር፡፡ ለምሳሌ፡ ንብ እርባታ፡ የባህር አረም ልማት፡ አግሮ ፎረስተሪሪና የመሳሰሉት | ተፈጥሮ ሀብት ላይ ተመክተው የሚኖሩት ቤተሰቦች በአለምና በአከባቢ ገበያ ተፈላገ ፡አማራጭ የኑሮ ሁኔታ ማሳደጊያ ተግባራት ላይ ተሰማርተው ገቢያቸውን ያሳድጋሉ፡ በተፈጥሮ ሀብት ላይም ጫና ይቀንሳል፡፡ |

**የፕሮጀክት ቡድን ተግባር: ክንውኖችን መመረጥ**

1. በቀጣይ ገፅ ላይ የቀረበውን ቅጽ/ምርክሽት በመጠቀም ለፕሮጀክቶቻችሁ ተስማሚ የሆኑ ክንውኖችን ለመምረጥ  እንድትችሉ ቀጥሎ የተዘረዘሩ ተግባሮችን አከናወኑ፡፡
    - ያዘጋጃችሁትን ግንዛቤያዊ  ሞዴል፣ የውጤት ሰንሰለቶችና የዓላማዎች ቅደም ተከተል (Hierarchy of Objectives) እንዲሁም ሞዴሎች እንደገና በመፈተሽ ለያንድአንዱ ሴክተር እጅግ አስፈላጊ ናቸው የምትሉአቸውን ለዉጦች (የመካከለኛ ጊዜ ዉጤቶች- outcomes) ለዩ፡፡  የመረጣችኋቸውን ለዉጦች (የመካከለኛ ጊዜ ዉጤቶች) ቅጹ/ወርክሽቱ ላይ አስፍሩ::

    - ከመረጃ-ደገፍ (Evidence-based) ክንውኖች ዝርዝር ውስጥ ለመረጣችኋቸው ለዉጦች (የመካከለኛ ጊዜ ዉጤቶች) ተስማሚ ናቸው የምትሉአቸውን ለዩ:: ካስፈለገ የራሳችሁን መረጃ-ደገፍ ክንውኖች ዝርዝር ማስቀመጥ ትችላላችሁ:: ይህንንም ቅጹ/ወርክሽቱ ላይ አስፍሩ፡፡  (አስታውሱ፡- ለአንድ ዓላማ አንድ ምርክሽት፤ ለአንድ ዓላማ አንድ እሴት ጨማሪ ክንውን ተጠቀሙ::)

    - ለያንድአንዱ ክንውን የክንውኑን ደረጃና አይነት ለዩ (አስቀምጡ)፡፡  ይህንን መረጃ በተገቢው የሰንጠረዥ አምድ ዉስጥ አስፍሩ፡፡

2. ያዘጋጃችሁትን ቅጽ አጠገባችሁ  ካሉ የሌሎች ፕሮጀክት ቡድኖች ጋር በመለዋወጥ አስተያየታቸዉንና ጥቆማዎቻቸውን ተቀበሉ፡፡  እኩል  ወይም የተሻለ ውጤት ሊያስገኙ ይችላሉ የሚሏቸው አማራጭ ክንውኖችን ካላቸው አስተያየት (ሃሳብ) ተቀበሉ፡፡

**የተሰጠ ጊዜ፡ 50 ደቂቃ**

# የክንውን መምረጫ ቅጽ (ወርክሽት) (1)

| ዓላማ | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት (ተፈላጊ ለዉጥ) | ክንውን | የክንውን ^ርከን (ደረጃ) | የክንውን አይነት |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

# የክንውን መምረጫ ቅጽ (ወርክሽት) (2)

| ዓላማ | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት (ተፈላጊ ለዉጥ) | ክንውን | የክንውን ˆርከን (ደረጃ) | የክንውን አይነት |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

# የክንውን መምረጫ ቅጽ (ወርክሽት) (3)

| ዓላማ | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት (ተፈላጊ ለዉጥ) | ክንውን | የክንውን ˆርከን (ደረጃ) | የክንውን አይነት |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

# የክንውን መምረጫ ቅጽ (ወርክሽት) ምሳሌዎች

| ዓላማ | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት (ተፈላጊ ለዉጥ) | ክንውን | የክንውን እርከን (ደረጃ) | የክንውን አይነት |
|---|---|---|---|---|
| የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት ይሻሻላል | የቤተሰብ ምጣኔ መረጃና ቁሳቁስ አቅርቦት ይጨምራል | የወሊድ መቆጣጠሪያዎች ማሕበራዊ ግብይትና ህብረተሰብ አቀፍ ስርጭት ስርዓት መዘርጋት | መዋቅራዊ | እሴት ጨማሪ (ቤተሰብ ምጣኔ፣ ምጣኔ- ኑሮ) |
| | | ዘላቂ የወሊደ መቆጣጠሪያ ዘዴ (Sterlization) ለሚፈልጉ ተጠቃሚዎች የሪፈራል ስርዓት መዘርጋት | ግለሰብ | ነጠላ ሴክተር |
| | የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተቀባይነትና አጠቃቀም ይሻሻላል | በመውለድ እድሜ ክልል ላሉ ባለትዳር ሴቶች አቻ ትምህርት ይሰጣል | ግለሰብ | ነጠላ ሴክተር |
| | | ሰዎች የቤተሰቦቻቸውን ቁጥር እንዲመጥኑና የባር ጠረፍ ሃብታቸውን በመንከባከብ የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያበረታቱ የጎዳና ድራማዎች | ማሕበረሰብ | የተቀናጀ (የተያያዘ) (ቤተሰብ ምጣኔ + የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ = ምግብ ዋስትና) |
| | በወጣቶች ላይ የሚከሰት ያልተፈለገ እርግዝና ይቀንሳል | ልቅ የሆነ የግብረሥጋ ግንኙነት ለሚፈጽሙ ወጣቶች ትምህርት ይሰጣል | ግለሰብ | እሴት ተጨማሪ (ቤተሰብ ምጣኔ፣ ጤና) |
| | | ወጣቶች የወሲብ ባህሪያቸውን እንዲቆጣጠሩና አካባቢያቸውን እንዲንከባከቡ የሚያበረታቱ መልዕክቶችን ያካተቱ አሳታፊ የገበጣ ጨዋታዎች | ቡድን | እሴት ጨማሪ (ስነተዋልዶጤና፣ አካባቢ) |

| ዓላማ | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት (ተፈላጊ ለዉጥ) | ክንውን | ደረጃ ^ርከን | አይነት |
|---|---|---|---|---|
| ህብረተሰብ አቀፍ የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ (CB-CRM) | ማሕበረሰቡ ጠቃሚ መካነ ህይወቶችን (Habitats) ይንከባከባል | ተሳትፎአዊ የባርጠረፍ ሃብት ዳሰሳ (Participatory Costal Resource Assessment (PCRA) | ቡድን | እሴት ተጨማሪ (የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ፣ አስተዳደር) |
| | | የባህርማ ሃብት ባለቤትነት ማረጋገጫ ውል (Marine Tenural Agreement) መፈጸም | መዋቅራዊ | ነጠላ ሴክተር |
| | | ጥብቅ የባህርማ ክልሎች (Marine Protected Areas-MPA) አያያዝ ኮሚቴና እቅድ | ቡድን | እሴትጨማሪ |
| | | የባሕርማ ጥብቅ ክልሎችን ማቋቋም (ማለትም የአሳ ጥብቅ ክልሎች ፣ የማንግሩብ ጥብቅ ክልለች- Mangroove Reserve ) | ማሕበረሰብ | ነጠላ ሴክተር |
| | በማሕበረሰቡ ተሳትፎ ሕገወጥ አሳ የማጥመድ ተግባር ይቆማል | የባህርማ ጥብቅ ክልሎች ቅኝት /ፓትሮል | ማሕበረሰብ | ነጠላ ሴክተር |
| | | በአሳ ጠባቂዎች ሕግ/ደንብ ማስከበር | ቡድን | ነጠላ ሴክተር |
| | | በሕገወጥ አሳ አስጋሪዎች ላይ ያተኮረ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት | ግለሰብ | ነጠላ ሴክተር |
| | አሳማስገር ይቀንሳል | አካባቢን የማይጎዳ የኢንተርፐራይዝ ልማት | ቡድን | እሴት ጨማሪ (የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ፣, ኢኮኖሚያዊ) |
| | | አካባቢን ለማይጎዳ ኢንተርፐራይዝ ልማት አነስተኛ ብድር አቅርቦት | ግለሰብ | እሴት ጨማሪ ((የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ፣ኢኮኖሚያዊ) |
| | በባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ የተገኙ ውጤቶች በቀጣይነት ይጠበቃሉ | የቤተሰብ ምጣኔ በባርጠረፍ ሃብቶች ክብካቤና ተግባሮች እንዲሁም በመንደር የልማት እቅዶች ውስጥ ይካተታሉ | መዋቅራዊ | የተቀናጀ ((የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ ፣ስነተዋልዶ ጤና፣ አካባቢን የማይጎዳ የኢንተርፐራይዝ ልማት) |

# ክፍለጊዜ 6፡ አመላካቾችን መለየት

## የክፍለጊዜው ዓላማ

- ለአንድ የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት ወጥ የክትትልና ግምገማ አመለካቾችን ለመምረጥ ነባር የፒ.ኤች.ኢ መሣሪያ (ማቀላጠፊያ) መጠቀም
- ከፕሮጀክት ጣቢያዉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ፣ ፕሮጀክት-ተኮር አመላካቾችን ማዘጋጀት

## ከክፍለጊዜው በፊት የሚነበቡ ጽሁፎች

- የፒ.ኤች.ኢ ፕሮግራም ዝግጅት ማኑዋል ገጽ 48-49
- የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ መመሪያ ከገጽ 7-9 እና ከገጽ 14-21

## ሁነኛ/ጥሩ አመላካቾችን መምረጥ

**የጥሩ አመላካቾች መለያ ባህሪዎች፡**

- ወጥ (Precise) ምሳሌ፡- ሁሉም ሰው በተመሳሳይ ሊገልጸው የሚችል
- የተባ (Sensitive) ምሳሌ፡- የሚለካው ነገር/ሁኔታ በተለወጠ ቁጥር ተመጣጣኝ የሆ ለውጥ የሚታይበት፡፡
- ስምም /ተመሳሳይ (consistent) ምሳሌ፡- ከጊዜ በኃላ የማይለወጥ ሁሌም አንድ አይነት ነገር የሚለካ ፡፡
- ተለኪ /ሊለካ የሚችል(Measurable)ምሳሌ፡- በቁጥርም ሆነ በአይነት ሊለካና ለተነተን የሚችል

**አመላካቾች ሲመረጡ መታየት ያለባቸው ቁልፍ ነጥቦች**

- የሚተገበረው ክንውን
- ግብ (ማለትም በቁጥር ሊለካ  የሚችል የሚጠበቅ ውጤት)
- የውጤት ሰንሰለት ምክንያት፡፡ ባዘጋጃችሁት ፕሮጀክት ንድፍ ዉስጥ ያመለከታችሁት #እንዲህ ቢሆን;... ይሆናል; የሚል የነገሮችን/የሁኔታዎችን ትስስር የሚያሳይ ሰንሰለት፡፡ ለምሳሌ ክንዉኑ ስለሚኖረዉ ተጽዕኖዎች ወይም ዉጤት ታሳቢ ያደረጋችሁት፡፡

## የውጤት ሰንሰለት ፡- የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚከናወን የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ




| | |
|---|---|
| ተግባር/ክንውን | በማሕበረሰቡ የሚቋቋሙና የሚተዳደሩ ባህርማ ጥብቅ ክልሎች (MPA) |
| የውጤት ሰንሰለት ምክንያት | የባርጠረፍ መካነ ሕይወቶች ይጠበቃሉ |
| ተጨማሪ ምክንያቶች | የዛጎልማተሬና አሳ ሃብት ማገገም፤ የተሻለ የስነምህድር ቁሳቁሶችና አገልግሎቶች ፍሰት |

# የፕሮጀክቶች ውጤት መዳረሻ መንገድ

| ግብዓት(Input) → | ሂደት(Process) → | ውጤት → (Output) | ለዉጥ → (Outcome) | ተጽእኖ (Impact) |
|---|---|---|---|---|
| ሰብዓዊ፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ሃብቶች (አጋሮችና ምቹ የሥራ አካባቢዎችን ጨምሮ)<br><br>ምሳሌ፡- ለድጋፍ ፈቃደኛ የሆነ ሕዝብና ምቹ የአካባቢ ፖሊሲ | ዓላማን ለማሳካት በፕሮጀክቱ የሚከናወኑ ደርጊቶች ፣ ስነ-ተግባሮችና (Procedures) ፣ ተግባሮች<br><br>ምሳሌ፡- በታችኛው የሕብረሰብ ክፍል ደረጃ የሚቋቋሙ ሕብረተሰብ አቀፍ የስርጭት አገልግሎቶች | ፕሮጀክቱ ለማሕበረሰቡ የሚያቀርበው ምርቶች፣ አገልግሎቶች (የተግባሮች ውጤት )<br><br>ምሳሌ ፡- የተሻለ የቤተሰብ ምጣኔ መረጃ/ዘዴዎች አቅርቦት | በውጤቶች አማካኝነት የሚፈጠር የስነሕዝብ፣ የአካባቢ ወይም የጤና ለውጥ<br><br>ምሳሌ፡- የባለትዳሮች ዘመናዊ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎች አጠቃቀም መጨመር | የመጨረሻ ውጤት ወይም የረዥም ጊዜ የሚታይ ለዉጥ<br><br>ምሳሌ፡- በመውለድ እድሜ ክልል ዉስጥ ያሉ ሴቶች (15-49 ዓመት) የውልደት መጠን መቀነስ |

**የልኬት ዓይነቶች**




*ከ Foundations for Success (2005). "WWF Standards of Conservation Projec and Program Management* ***የተወሰደ***"

**ፕሮግራም-ተኮር አመላካቾች ብዙውን ጊዜ ሂደቶችን ለመለካት ያገለግላሉ፡፡** ለምሳሌ ግብአቶችን፣ ተግባሮችንና ውጤቶችን፡፡ ፕሮግራም-ተኮር መረጃ የፕሮግራሙን ውጤታማነት ለመለካት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲህ አይነት መረጃ ለምሳሌ የተሰጡ ስልጠናዎችንና የተተከሉ ዛፎችን ቁጥር ከሚያመለክቱ የፕሮጀክት መዛግብቶች (ሪፖርቶች) ማግኘት ይቻላል፡፡

**ስነ -ህዝብ ተኮርና መካነ ህይወት-ተኮር አመላካቾች ባብዛኛው የፕጀሮጀክት ውጤቶችን ለመለካት ያገለግላሉ፡፡** (ለምሳሌ ለዉጦችንና ተጽእኖዎችን) ፡፡ ስነሕዝብ-ተኮር መፍትሔዎች በአጠቃላዩ ማህበረሰብ ላይ የሚኖረዉን ዉጤት ያመለክታሉ፡፡ ይህ ቃል በተጨማሪም አንድን ዉሱን ጂኦግራፊያዊ ክልል ለምሳሌ የፕሮጀክቱን የትኩረት ቦታ ሊያመለክት ይችላል፡፡

# የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

| የልኬት ደረጃ | ዘዴ | የመረጃ ምንጭ | የጊዜ ሰሌዳ |
|---|---|---|---|
| **ግብአቶች**<br><br>ፕሮግራም-ተኮር መፍትሄዎች | 1. የአዝማሚያ ትንታኔ (Trend Analysis) | 1. የአገልግሎት ስታቲስቲክስ መዝገቦች<br>2. የፕሮጄክት መዝገቦች | ፕሮጀክቱ በጀመረ በስድስት ወር ውስጥ የታየ ለውጥ ። በፕሮጄክቱ ዕድሜ ከ 1-3 ወራት የጊዜ ልዩነት በመደበኛነት የሚሰበሰብ። |
| **ሂደት**<br><br>ፕሮግራም-ተኮር መፍትሄዎች | 1. የአዝማሚያ ትንተና<br>2. ፈጣን ግምገማ (Rapid Appraisal) (የአይነት) | 1. የቡድን ዉይይት (Focus Group)<br>2. ከቁልፍ የመረጃ ምንጮች ጋር የሚደረግ ቃለመጠይቅ (Key informal interview)<br>3. የድርጅት ሁኔታ ቅኝት (facility survey) | ፕሮግራሙ መተግበር በጀመረ ከመጀመሪያው 6 ወር እስከ 1 ዓመት |
| **ውጤት**<br><br>ፕሮግራም-ተኮር መፍትሄዎች | 1. የአዝማሚያ ትንተና<br>2. ትራንሴኬት ጥናት | 1. የአገልግሎት ስታቲስቲክስ<br>2. የፕሮጄክት መዛግብት<br>3. ቀጥታ ምልከታ | ከአንድ እስከ ሁለት ዓመት |
| **ለዉጥ**<br><br>(የአጭር ጊዜ/የረዥም ጊዜ)<br><br>ስነህዝብ -ተኮር ወይም መካነ ህይወት-ተኮር መፍትሄዎች | 1. ስነህዝብ ተኮር ጥናት/ቅኝት<br>2. ትራንሴክት ጥናት<br>3. ካርታ ዝግጅት | 1. ቃለመጠይቆች<br>2. የጥናት ቅጾች<br>3. ጂ.ፒ.ኤስ (GPS)<br>4. ህጋዊ መዝገቦች<br>5. የዕለት-ሁኔታ መዝገቦች | ከሁለት እስከ ሶስት ዓመት (ለአጭር ጊዜ) እና ከሶስት እስከ አምስት ዓመት (ለረዥም ጊዜ) |

# የ IPOPCORM ፕሮጄክት አመላካቾች

| ዓላማ | ክንውን | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት | አመላካቾች ሊሆኑ የሚችሉ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሂደት | ውጤት | ለዉጥ |
| በ2004 (እ.ኤ.አ) በባር ጠረፍ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የስነተዋልዶ ጤና ሁኔታ ይሻሻላል | ሕብረተሰብ-አቀፍ የወሊድ መቆጣጠሪያ ስርጭት (CBD) | የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት አቅርቦትና አጠቃቀም መጨመር | ስልጠና የወሰዱ ሕብረተሰብ-አቀፍ የወሊድ መቆጣጠሪያ ስርጭት ሰራተኞች ቁጥር | በሥራ ላይ ያሉ የሕብረተሰብ-አቀፍ የወሊድ መቆጣጠሪያ ስርጭት ሰራተኞች (መቶኛ) | ዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ጥቅም አምነዉ በመቀበል እየተጠቀሙ ያሉ ሰዎች ቁጥር (ገጽ 55) |
| በ 2006 (እ.ኤ.አ) የማሕበረሰቡ ባርጠረፍ ሃብቶችን የመንከባከብ አቅም ይዳብራል | ጥብቅ ባህርማ ክልሎች (MPA) በማህበረሰቡ ተሳትፎ ይቋቋማሉ፣ ይተዳደራሉ | መካነ ህይወቶች ይጠበቃሉ | ደንብ/ሕግ በማስከበር የሰለጠኑ የማሕበረሰቡ አባላት ቁጥር | የተከናወኑ የቅኝት/የፓትሮል መዝገብ | የተሻለ ጥበቃ የተደረገላቸው ጥብቅ ባህርማ ክልሎች ብዛት (ቁጥር) እንዲሁም ስፋት (በኪ.ሜ.ስ.) (ገጽ 95) |

## የተቀናጁ አመላካቾች

**(የፒ.ኤች.ኢ አሰራሮችን ወይም ክንዉኖችን ቅንጅት ለመለካት)**

| ሂደት /ውጤት(*ፕሮግራም-ተኮር*) | ለዉጥ/ተጽእኖ *(ስነሕዝብ-ተኮር)* |
|---|---|
| 1. ትስስር ያላቸዉ የተዘጋጁ መልዕክቶች/ቁሳቁሶች ቁጥር<br>2. የተጠቃሚ ማሕበረሰቡን አባላት ያሳተፉ ትምህርታዊ ውይይቶች ብዛትና/ድግግሞሽ<br>3. ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ተፈጠሩ/የተከናወኑ አዳዲስ የፒ.ኤች.ኢ ትብብሮች (ቁጥር) | 1. በተወሰኑ  የፒ.ኤች.ኢ ጭብጦች ዙሪያ ዕውቀት ያላቸው ቤተሰቦች መጠን (በመቶኛ)<br>2. በፕሮጀክቱ አካባቢ በሶስቱም የፒ.ኤች.ኢ ዘርፎች አገልግሎት እያገኙ ያሉ ማህበረሰቦች መጠን (በመቶኛ)<br>3. ፒ.ኤች.ኢን የሚደግፉ በፕሮጀክቱ አካባቢ ያሉ ፖሊሲዎች ቁጥር |

# እሴት ጨማሪ አመላካቾች

| ሂደት / ውጤቶች (ፕሮግራም-ተኮር) | ለዉጦች/ተጽእኖ (ስነ-ህዝብ ተኮር) |
|---|---|
| 1. በሕብረተሰብ-አቀፍ የተፈጥሮሃብት ክብካቤ ኮሚቴዎች ውስጥ የመሪነት ቦታ የያዙ ሴቶች ብዛት (መቶኛ) | 1. ከሞሪንጋ ፍሬ የተዘጋጀ የማብሰያ ዘይት በመሸጥ ገቢ የሚያገኙ ቤተሰቦች መጠን (በመቶኛ) |
| 2. በሕብረተሰብ-አቀፍ የወሊድ መቆጣጠሪያ ስርጭት ሰራተኞች ማሕበራዊ ግብይት አማካይነት የተሸጡ የቤተሰብ ምጣኔ ቁሳቁሶች ዋጋ (በዶላር) | 2. እድሜአቸው ከአምስት ዓመት በታች በሆኑ ልጆች ላይ የተከሰተ የመተንፈሻ አካላት በሽታዎች (ARI) ሁኔታ |
| 3. የተሻሻለ የማበሰያ ምድጃ በሚጠቀሙ ቤተሰቦች በየወሩ የተቀጠበ የማገዶ ወጪ መጠን፡፡ | 3. በቅርብ (በዚህ ሰሞን) የግብረ ስጋ ግኑኝነት ጊዜ ኮንዶም የተጠቀሙ እድሜአቸው ከ15-24 ዓመት የሆኑ ወጣቶች በዛት (መቶኛ) |

## <u>የፕሮጀክት ቡድን ተግባር ፡- አመላካቾችን መለየት</u>

1. የ MEASURE መምሪያን እንዲሁም የቀረበውን ቅጽ (ወርክሽት)በመጠቀም ለወጠናችሁዋቸዉ የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት ዘርፍ ዓላማዎች (sector objectives) አመላካቾችን ምረጡ፡፡
   ሀ. የዘርፉን ስም አስፍሩ በተሠጠዉ ባዶ ቦታ አስፍሩ(በተቀናጁ አመላካቾች ወይም እሴት ጨማሪ አመላካቾች ላይ ለመስራት ካሰባችሁ ይህንኑ በተሰጠው ቦታ አስፍሩ)
   ለ. በክፍለ ጊዜ 4 ተግባራችሁ ያዘጋጃችሁትን ዓላማ አስፍሩ፡፡

   ሐ. አንድ ወይም ከዚያ በላይ ክንውኖችንና ተያያዥ የውጤት ሰንሰለት ምክንያቶችን በተገቢው የሰንጠረዡ ክፍል አስፍሩ፡፡ (በ4ኛውና 5ኛው ክፍለ ጊዜ ያዘጋጃችሁትን መረጃ ተጠቀሙ)፡፡

   መ. ለያንዳንዱ ክንውን/የውጤት ሰንሰለት ምክንያት (RCF) ቢያንስ አንድ መደበኛ አመላካች (በ MEASURE መምሪያ ውስጥ ከተዘረዘሩት ) ምረጡ፡፡ ከመምሪያው ተስማሚ አመላካች ማግኘት ካልቻላችሁ ተገቢ አመላካች ነው የምትሉትን ራሳችሁ አዘጋጁ፡፡ በዚህ ሂደት የጥሩ/ሁነኛ አመላካቾች መገለጫ ባህሪዎች ተብለዉ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች አስታውሱ፡፡

2. ጊዜ የሚኖራቸው ከሆነ በሌላ የዘርፍ ዓላማ ስር ለተቀመጠ ክንውን ተጨማሪ አመላካች (ቾች) አዘጋጁ፡፡ እንደአማራጭ የተቀናጁ አመላካቾችን ወይም እሴት ጨማሪ አመላካቾችን መውሰድ ትችላላችሁ፡፡ የተቀናጁ አመላካቾችን ወይም እሴት ጨማሪ አመላካቾችን የምትጠቀሙ ከሆነ " ሴክተር/ዘርፍ" በሚለዉ ባዶ ቦታ ይህንኑ አስፈሩ፡፡

**የተሰጠ ጊዜ፡ 45 ደቂቃ**

## የአመላካች መምረጫ ቅጽ (ምርክሽት) (1)

ዘርፍ/ሴክተር________________________________

| ዓላማ | ክንውን | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት | አመላካቾች ሊሆኑ የሚችሉ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሂደት (ፕሮግራም-ተኮር) | ዉጤት (ፕሮግራም-ተኮር) | ለዉጥ (ስነ ሕዝብ/መካነ ሕይወት-ተኮር) |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

## የአመላካች መምረጫ ቅጽ (ምርክሽት) (2)

________________________________ ዘርፍ/ሴክተር

| ዓላማ | ክንውን | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት | አመላካቾች ሊሆኑ የሚችሉ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሂደት (ፕሮግራም-ተኮር) | ውጤት (ፕሮግራም-ተኮር) | ለዉጥ (ስነ ሕዝብ/መካነ ሕይወት-ተኮር) |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

## ምሳሌ፡ እሴት ጨማሪ ክንውን

ዘርፍ ፡ አካባቢ

| ዓላማ | ክንውን | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት | አመላካቾች (ሊሆኑ የሚችሉ) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሂደት | ውጤት | ለዉጥ |
| የደን ሃብቶች ዘለቄታዊ ክብካቤ የማሕበረሰቡ አቅም ይገነባል | የተሻሻሉ የማብሰያ ምድጃዎች ማቅረብ | የማገዶ ፍጆታ መቀነስ | የተሻሻሉ የማብሰያ ምድጃዎችን አስገብተው በመደበኛነት የሚገለገሉ ቤተሰቦች ቁጥር | የተሻሻሉ ምድጃዎቸችን በመጠቀም የሚቆጠበው ማገዶ መጠን (በወር) | የደን ሽፋን (በሄክታር) |
| | | የቤት ውስጥ አየር ብክለት መቀነስ | የተሻሻሉ የማብሰያ ምድጃ አስገብተው በመደበኛነት የሚገለገሉ እድሜአቸው ከ5 በታች የሆኑ ልጆች የሚገኙባቸዉ ቤተሰቦች ቁጥር | ባለፈው ስድስት ወር ለመተንፈሻ አካላት በሽታ ህክምና የተደረገላቸው ዕድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ቁጥር | በፕሮጀክቱ አካባቢ ባሉ ቤተሰቦች ዉስጥ በኢነርጂ አጠቃቀም ምክንያት በሕፃናት ላይ የተከሰተ የመተንፈሻ አካላት በሽታ ችግር |
| | | ለሁከት ተጋላጭነትን መቀነስ | ሴቶችና ልጃገረዶች ማገዶ በመልቀም የሚያባክኑት አማካይ ጊዜ (በሰዓት) | ባላፈው ስድስት ወር ማገዶ ሲለቅሙ ሁከት እንደተፈፀመባቸው ያመለከቱ/የተናገሩ ሴቶች/ልጃገረዶች ቁጥር | ማገዶ በሚለቅሙ ሴቶች/ልጃገረዶች ላይ የተከሰተ ሁከት |

# ክፍለጊዜ 7: የፒ.ኤች.ኢ አፈፃጸም ሞዴሎችና ዘዴዎች

የክፍለ ጊዜው ዓላማዎች ፡-

- የተለያዩ የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክቶች አፈፃጸም ሞዴሎችንና የቅንጅት ዘዴዎችን ማብራራት፡፡ በዚህ ላይ በመንተራስ ለአንድ ፕሮጀክት የትኞቹ ሞዴሎችና ስትራቴጂዎች የበለጠ ተስማሚ እንደሆኑ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ምርጫ ማድረግ፡፡

- ተስማሚ የሆኑ ሞዴሎችን/ስተራቴጂዎችን ለመምረጥ አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ መረጃዎችን መሰብሰብ (ለምሳሌ ስለ ቡድን አወቃቀር፣ የፕሮጀክት ማከናወኛ ሃብት/ገንዘብ ምንጭ ማፈላለግ፣ ከሌሎች ጋር እንዴት በትብብር መስራት እንደሚቻል መወሰን ወዘተ.)

ከክፍለ ጊዜው በፊት የሚነበቡ ጽሁፎች

- የፒ.ኤች.ኢ ፕሮግራም ዝግጅት ማንዋል ገጽ 10፣31-40፣ እና ገጽ 54-64

## የማቀናጀት ዓላማ

በስነሕዝብ ፣ ጤናና አካባቢ ዘርፎች ማሃከል ትስስር በመፍጠር እነኚህ ዘርፎች በተናጥል ከሚያስገኙት ውጤት ይልቅ በቅንጅት ሊሰጡ የሚችሉትን የተሸለ ውጤት ዕዉን ማድረግ።

**የቅንጅት ሁለት ደረጃዎች (እርከኖች)**

*የመጀመሪያ ደረጃ (ቀዳማይ)* ቅንጅት ፦ በፖሊሲና አስተዳደር (ማኔጅመንት) ደረጃ የሚከናወን ቅንጅት።

*ሁለተኛ ደረጃ* ቅንጅት ፦ በክንውን (ስልጠና ፣ አገልግሎት መስጠት፣ መረጃ/ትምህርትና/ተግባቦት -IEC፣ በክትትልና ግምገማ ) ሂደት የሚደረግ ቅንጅት።

**የመጀመሪያ ደረጃ (ቀዳማይ) ቅንጅት**

- ሚዛናዊና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ የስነህዝብና ጤና ጉዳዮችን ከአካባቢ ጉዳዮች ጋር (እንዲሁም የአካባቢን ጉዳዮች ከጤናና ስነህዝብ ጉዳዮች ጋር ) በማቀናጀት ላይ ያተኮረ ነው።
- የፕሮጀክቶቻችሁ ፒ.ኤች.ኢ ጽንሰሃሳቦች ከሴክተር -አቀፍ/ተሸጋጋሪ ጉዳዮች ጋር የተገናዘቡ እንዲሆኑ አድርጉ።

**ለምሳሌ**

- ከድህነት ቅነሳ ፖሊሲ
- ከአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች
- ከምግብ ዋስትና ፖሊሲ
- ከምርታማነት ሴፍቲኔት (Productive Safety Net) ጉዳዮች
- ከድህረ-ግጭት ልማትና ዲሞክራሲ ግንባታ ጉዳዮች ጋር።

**የመጀመሪያ ደረጃ  ቅንጅት ጥቅሞች**

- ለስራችን ማከናወኛ  ሃብት/ጥሪት ለማቅረብ
- የፒ.ኤች.ኢን ዘዴ ዘላቂነት የተሻለ ያደርጋል
- ውጤታማ ተሞክሮዎችን/ተግባሮችን ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል
- ለአጠቃላይ ልማት አስተዋፅኦ ያደርጋል

**የመጀመሪያ ደረጃ  ቅንጅቶችን እውን ለማድረግ የምንጠቀምባቸዉ ዘዴዎች ፡፡**

- በቅድሚያ የፒ.ኤች.ኢን ውጤታማነት በፕሮጄክት አካባቢው ካሉ 'ደጋፊዎች' ጋር በመስራት ማሳየት
- ይህን ሂደት ለማበረታታት ስብሰባ፣ እቅድ/በጀት በጋራ ማዘጋጀት
- ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ተቋሞች/ክፍሎች ተወካዮችን ማሳተፍ
  - ✓ መንግስታዊ ተቋማት፡- የአካባቢ ፣ ጤና ፣ ግብርና ዘርፍ ተቋማት
  - ✓ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የማህበረሰብ ድርጅቶች (CBOs) ፡- (በጤና ፣ አካባቢ፣  ገጠር ልማት ላይ የሚሰሩ )
  - ✓ የሃብት ተጠቃሚ ቡድኖች፣ የሴቶች/ወጣቶች ክለቦች ወዘተ.

ምሳሌ

- ፍሊፒንስ - የIPOPCORM ፕሮጄክት የስነህዝብና የስነተዋልዶ ጤና ስትራቴጂዎችን ለማቀናጀት ከነባር የማዘጋጃ ባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ ፖሊሲ ጋር ትስስር ፈጥሯል፡፡
- ኔፓል -  ጤናንና የንፁህ ኢነርጂን ጉዳዮችን ለማቀናጀት ከነባር የወረዳ ደን ክብካቤ አጀንዳ ጋር በማያያዝ ተስርቷል፡፡
- ማዳጋስካር - የስነተዋልዶ ጤናና የአግሮ-ኢኮሎጂ ክንውኖች ከማሕበረሰብ ልማት ጉዳዮች ጋር ተቀናጅተዋል፡፡

**ሁለተኛ ደረጃ ቅንጅት** (Secondary Integration)

- **ስልጠና** - የስነህዝብን፣ ጤናና  የአካባቢን የመማር ዓላማዎች በማጣመር ቅንጅት ለመፍጠር የሚከናወን፡፡  በተጨማሪም የነዚህን ዘርፍ ግቦች ከሌሎች ዘርፍ ጉዳዮች ጋር ማጣመር፡፡ (ለምሳሌ ከድህነት፣ ምግብ ዋስትና ወዘተ.)
- **አገልግሎት** - የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሃብት ክብካቤን የሚደግፉ የስነህዝብ/ጤና አገልግሎቶችና መረጃዎች ለማህበረሰቡ አማካይ ቦታዎች ላይ ማቅረብ፡፡
- **መረጃ/ትምህርት/ተግባቦት** (IEC) - በፕሮጄክቱ የጋራ ግብ ወይም ማዕከላዊ  ጭብጥ (ለምሳሌ በምግብ ዋስትና፣ በዘላቂ ምጣኔ-ኑሮ ልማት) ላይ ያተኮሩ በተጠቃሚ ቡድኖች ተሳትፎ የሚዘጋጁና የሚሰራጩ መልዕክቶችና ቁሳቁሶች፡፡
- **ክትትልና ግምገማ** - እሴት ጨማሪና የተቀናጁ አመላካቾችን ያካተቱ፡፡  እንዲሁም በተቻለ መጠን የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን የሚያመለክቱ፡፡

# የመስክ ተግባር አፈጻፃም ሞዴሎች

### *ማሕበረሰብ አሳታፊ ዘዴዎች*

ህብረተሰብ አቀፍ የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ (CB-CRM) ወይም ህብረተሰብ አቀፍ የተፈጥሮ ሃብት ክብካቤ (CB-NRM) የመሳሰሉ የማህበረሰቡን ነባር የተፈጥሮ ሃብት ክብካቤ ዘዴዎች የሚያጠናክሩ አሳታፊ የሃብት ክብካቤ ሞዴሎች የአሳታፊ ዘዴዎች ምሳሌዎች ናቸዉ፡፡ እንደዚህ ያሉ ሞዴሎች በተለያዩ ዘርፎች መሃከል ቅንጅት ለማረጋገጥ የቤተሰብ ምጣኔና የምጣኔ-ኑሮ ተግባሮችን የሚያካትቱ ሲሆን በማህበረሰቡ ዉስጥ ያሉ ነባር የማኔጅመንት ኮሚቴዎችንና መዋቅሮችን ይጠቀማሉ፡፡ አሳታፊ ሞዴል አንድ የፕሮጀክት ሰራተኛ (ለምሳሌ ማህበረሰብ አደራጅ ባለሙያ) በፕሮጀክት ቦታዉ ላሉ የማህበረሰብ ድርጅቶች በመልካም አስተዳደር ወይም በሌሎች የተቋም ማጠናከሪያ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ ለመስጠት በፕሮጀክት ጣቢያዉ በቋሚነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ የሚኖር ከሆነ የበለጠ ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡

### *ማሕበረሰብ ማነሳሻ (ማነቃቂያ) ሞዴሎች (Social Mobilization Models)*

አፕሪሼት የማሕበረሰብ ማነቃቃት (Appreicate Community Mobilization-ACM)፣ Champion Community (ማሕበረሰቡ ዓላማዎችን በማስቀመጥና በመከታተል እንዲሁም የተገኘውን ውጤት በማክበር የሚሳተፍባቸው ሞዴል)፣ እንዲሁም የ Champion Commune ዘዴዎች፡፡ እነዚህ ሞዴሎች በአጠቃላይ የማሕበረሰቡ መሪዎች የቤተሰቦችን ኑሮ ለማሻሻል የሚረዱ "ትናንሽና በቀላሉ ሊሰሩ የሚችሉ ተግባሮችን" በማመቻቸት፣ በማቀድ፣ በመፈፀምና ክትትል በማድረግ የመሪነት ሚና በሚጫወቱባቸው አሠራሮች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

### *የማሕበረሰብ ዉሉገብ አቻ ትምህርት (Community Outreach Peer Education-COPE) ሞዴል*

ለኢክስቴሽን ሰራተኞች ክፍያ በመክፈል የፒ.ኤች.ኢ አገልግሎት ስርዓት የሚዘረጋበት ሞዴል ነው፡፡

የኤክስቴሽን ሰራተኞቹ በተጨማሪም ለአቻዎቻቸው ብሎም በፕሮጀክት አካባቢው ለሚገኘው ማሕበረሰብ  የቤተሰብ ምጣኔና የተፈጥሮ ሃብት ክብካቤ ትምህርት የሚሰጡ በጎፍቃደኞችን ያስለጥናሉ፣ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

***የአርሶ አደር -ለአርሶ አደር (Farmer-to-Farmer) ሞዴል***

በዚህ ሞዴል አርሶአደሮች ግብርናን በተመለከተ ቴክኒካዊ ምክር እንዲሁም የጤናና የአካባቢ ክብካቤ መረጃዎችን ለአቻዎቻቸው (ለሌሎች አርሶአደሮች) ይሰጣሉ፡፡

## ማህበረሰቡን በማሳተፍ ቅንጅትን ማረጋጋጥ

ፒ.ኤች.ኢ ከማሕበረሰቡ ጋር የሚከናወን ተግባራዊ (እውነተኛ) ትብብር ስለሆነ ማህበረሰቡ ስለ ቅንጅት ምንነት  እንዲገነዘብ ማድረግ ለፕሮጀክቱ ውጤታማነት ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም ሕብረተሰብ አሳታፊ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡  ቀጥሎ የተዘረዘሩት ጥቅሞችን/አገልግሎቶችን ለማህበረሰቡ ማቅረብ የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክቶች የማሕበረሰብ ተሳትፎን ከሚያረጋግጡባቸዉ መንገዶች ውስጥ ይካተታሉ፡፡

- **ማሕበራዊ ጥቅሞች፡-** ለምሳሌ የተሻሉ የማህበረሰብ ድርጅቶች (መዋቅሮች) መፈጠር፣ እውቅና (ለበጎፈቃደኛ አቻ መምህራን የምስክር ወረቀት መስጠት)፣ ለራስ ያለን ክብር መጨመር (ፕሮጀክቱ በሚያቀርባቸዉ አገልገሎቶች በመጠቀም ልጆቻቸውን በተሟላ ሁኔታ ላስከተቡ ቤተሰቦች እውቅና መስጠት)፡፡

- **የማህበረሰብ ፕሮጀክቶች** በፕሮጀክቱ/ በኢንተርፕራይዙ የሚደገፉ ለምሳሌ አስቸኳይ የመጀመሪያ ሕክምና አገልግለቶች የሚሰጡ የጤና ኬላዎችን መገንባት፡፡

- **አካባቢያዊ ጠቀሜታ** የአፈር መሸርሸር ቁጥጥር ወይም የውሃከል (watershed) ክብካቤ
- **ስነውበታዊ ጠቀሜታ** (መንፈሳዊ ፋይዳ ያላቸው ቦታዎች መጠበቅ ለምሳሌ የሂማሊያ ተራራዎች)

## የፒ.ኤች.ኢ. ትብብር ዓይነቶች/ምሳሌዎች

| | ጥቅም | ጉዳት |
|---|---|---|
| ባንድ ድርጅት ዉስጥ ያሉ የተለያዩ ዓይነት ሙያተኞችን ያካተቱ ቡድኖች (Multidisciplinary Teams) | • ቅንጅትና ተግባቦት ቀላል ነው፡፡<br>• የመስክ ተግባሮችን በተሻለ ቅንጅት ማከናወን ይቻላል፡፡<br>• በሌሎች ዘርፎች የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት ይቻላል፡፡ | • ሁሉንም ክህሎቶች ያሏቸው ሙያተኞች ማግኘት (መቅጠር) ከፍተኛ ወጪ ሊያስከትል ይችላል፡፡<br>• በሁሉም የአካባቢ ጉዳዮች ላይ የሰለጠነ ሙያተኛ ማግኘት (እንዲኖር ማድረግ) አስቸጋሪ ነው፡፡<br>• አላማ መሳት/ትኩረት ማጣት ተደርጎ ሊታይ ይችላል (Mission Drift) |
| በአንድ ድርጅት ውስጥ ያሉ ሴክተር-ተኮር የሙያተኞች ቡድን (Sector-specific Teams) | • አንድ ድርጅት የተለያዩ ቡድኖች በአንድ ላይ እንዲሰሩና ሥራቸዉን እንዲያቀናጁ ማድረግ ስለሚችል አሁንም በመስክ ደረጃ ቅንጅት መፍጠር ይቻላል፡፡ | • በተለያየ ድርጅቶች መሃከል ቅንጅትን ለማሽጋገር አዳጋች ነው፡፡<br>• በተለያዩ ሴክተሮች መሃከል ተግባቦትንና መማማርን ለማከናወን ተጨማሪ ወጪ ይጠይቃል፡፡<br>• የሌሎች ዘርፎች ሰራተኞች አቅም አይገነባም፡፡ |
| ከሌሎች ጋር በሚፈጠር ትብብር የሚገኝ ቴክኒካዊ ብቃት | • አንድ ድርጅት ሁሉንም ሙያቶኞች/ክህሎቶች እንዲኖሩት አይጠበቅበትም<br>• በትብብሩ አማካኝነት በሚፈጠሩ ቅንጅቶችና መረቦች መጠቀም  ይቻላል፡፡<br>• የተለያዩ አይነት በአካባቢ ላይ ያተኮሩ ሙያተኞች (ክህሎቶች) ማግኘት ይቻላል፡፡<br>• አላማ መሳት/ትኩረት ማጣት አዝማሚያ አይኖርም | • ተግባቦትና ቅንጅት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ እነኚህን ችግሮች መቅረፍ ተጨማሪ ወጪ ያስከትላል፡፡<br>• በእቅድ ዝግጅትና አፈጻፀም ጊዜ የሚኖረው ቅንጅት ያነሰ ነው፡፡<br>• በመስክ ደረጃ ቅንጅትን ለማሽጋገር ያለው እድል ያነሰ ነው፡፡<br>• የሌሎች ዘርፎች ሰራተኞች አቅም አይገነባም<br>• እንደየሁኔታው እየታየ የሚከናወን (adaptive) ማኔጅመንት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ |

## የትብብር ጥቅሞች

- የሚደረገዉ ጥረት የተሻለ ዉጤት እንዲኖረዉ
- የሚደጋገፉ ክህሎቶችን በማጣመር የተሻለ ስራ ለመስራት
- ገንዘብ ወይም ሃብትን ለማቀናጀት/ምንጭ ለማሥፋት
- የሥራ ድግግሞሽ ለማስወገድ
- ነባር ፕሮግራሞችንና ማሕበራዊ እሴቶችን ለማዳበር
- ተቀባይነት ለመጨመር
- የአገልግሎት ክፍተትን ለመሙላት
- አቅም ለመገንባት
- ዘላቂነትን ለማረጋገጥ
- ፕሮጄክቱ ሰፋ ያለ ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘብ እንዲሆን ለማስቻል፡፡

# የፕሮጀክት ማከናወኛ ሃብት ማሰባሰብ

**በማሕበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሃብቶች፡-** ፕሮጀክቱ ፒ.ኤች.ኢን ለማከናወን ሊጠቀምባቸው የሚችል በማሕበረሰቡ ውስጥ ነባር ተቋሞች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ IPOPCORM ፕሮጀክት በተመለከተ ራቅ ባሉ የፊሊፒንስ ጠረፋማ አካባቢዎች የነበሩ ተቋሞች አነስተኛ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብሮች (ሳሪ-ሳሪ በመባል ይታወቃሉ) ናቸው፡፡ በመሆኑም ፕሮጀክቱ የቤተሰብ ምጣኔ መረጃዎችንና ቁሳቁሶችን ለማሰራጨት የነዚህን መደብሮች ባለቤቶች በማሰልጠን መደብሮቹን እንደማሰራጫ ጣቢያ ተጠቅሞባቸዋል፡፡

**የአካባቢ መስተዳድር ተቋሞች፡-** እነዚህ ተቋሞች አገልግሎቶችንና ገንዘብ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ፕሮጀክቱ ለምሳሌ ማሕበረሰቡ የድጋፍ ጥያቄ፣ እቅድና በጀት እንዲያዘጋጅ በመርዳት በነዚህ የድጋፍ ምንጮች እንዲጠቀም ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይችላል፡፡

**ፕሮጀክት በማከናወን ላይ ያሉ የማሕበረሰብ ድርጅቶች፡-** የፒ.ኤች.ኢ ተግባሮችን ለማቀናጀት እንደ መነሻ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በኔፓል የቤተሰብ ምጣኔንና የንፁህ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ከደን ጥበቃ ተግባሮችና እቅዶች ጋር ለማቀናጀት የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት ከነባር የማህበረሰብ ደን ተጠቃሚ ቡድኖች (Community Forest Users Groups-CFUGs) ጋር ሰርቷል፡፡

**ክለቦችና ማሕበራት፡-** እንደ ላየንስ ክለብ፣ ሮታሪ ክለብ ያሉ አነስተኛ የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጡ ድርጀቶች (ማሕበራት)፡፡ እነዚህ ቡድኖች በተለይ በወጣቶች ጉዳዮች ላይ ላተኮሩ ሥራዎች የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጡ ሲሆን የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክቶቻችሁም በወጣቶች (ለምሳሌ የሥነተዋልዶ ጤና መረጃና አገለግሎት) እንዲያካትቱ በማድረግ እነኚህን የድጋፍ ምንጮች መጠቀም መቻል አለባቸው፡፡

**አገር በቀል ትረስቶችን ፈንዶች፡-** እነዚህ የድጋፍ ምንጮች በግል ኩባኒያዎች የሚተዳደሩ ትረስቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በታይላንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአገሬው ባንኮች ከተቋቋሙ የአካባቢ ክብካቤን ከሚደግፉ ፋውንዴሽኖች የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ፡፡

**ዓለም አቀፍ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ምንጮች ዉስጥ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡-**

- የተባበሩት መንግሥታት ተቋማት ለምሳሌ UNFPA
- የክሊንተን ፋውንዴሽን (በኤች.አይ.ቪ/ኤድስና በአየር ለውጥ ላይ)
- የፓካርድ ፋውንዴሽን (በቤተሰብ ምጣኔ፣ ስነተዋልዶ ጤና፣ ፒ.ኤች.ኢ ላይ)
- ኢንጀንደር ሄልዝ (በቤተሰብ ምጣኔ፣ ስነተዋልዶ ጤና )
- ዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ (PBR, MEASURE EVALUATION, BALANCED)

## የፕሮጀክት ቡደን ተግባር፡ የአገልግሎት "ክፍተት ካርታ" ማዘጋጀት

1. ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች የሚያሳይ ካርታ አዘጋጁ፡-

   - ከትኩረት ዘርፎቻችሁ (ማለትም ከስነህዝብ፣ ጤናና አካባቢ) ጋር በፕሮጀክት አካባቢው ተያያዥነት ያላቸዉ የመንግስት ተቋማት ክፍሎችን፤ በነዚህ ዘርፎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን፤ እንዲሁም የነዚህን ተቋሞች/አገልግሎቶች ሽፋን በተመለከተ፤
   - የአገልግሎት ክፍተት የሚስተዋልባቸውን ቦታዎች፡፡ ለምሳሌ በነዚህ ተቋማት/አገልግሎቶች ታችኛው የህበረተሰብ ክፍል ይገለገላል?
   - ፕሮጅክት በመተግበር በተባባሪነት ሊያገለግሉ የሚችሉ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ነባር ተቋሞችና መደበኛ ያልሆኑ ቡድኖችን በተመለከተ፤

2. እነዚህን የአገልግሎት ክፍተቶች በመሙላት አገልግሎቶቹን ወደ ሕዝቡ እንዴት ለማድረስ እንደሚቻል አብረዋችሁ ከተቀመጡ ተሳታፊዎች ጋር ውይይት(Brain Storm) አድርጉ፡፡
3. ክፍተቶቹን ለመሙላት መከናወን ያለባቸውን ተግባሮች /እርምጃዎች ዝርዝር አዘጋጁ፡፡ ለምሳሌ በነባር መደበኛ ያልሆኑ ተቋሞች መሃከል በመንደር ደረጃ ፤ ብሎም ቀጥሎ ባለዉ ደረጃ በመንግስት አካላት መሃከል ትስስር ስለመፍጠር ፡፡

**የተሰጠ ጊዜ፡ 70 ደቂቃ**

# IPOPCORM ሁኔታ ካርታ




**አብዛኛዎች የባርጠረፍ ነዋሪዎች የሚገኙበት ቦታ**

ይህ ካርታ አብዛኛዎች የባርጠረፍ ነዋሪዎች የሚገኙት በጎጥ ወይም በንዑስ-መንደር ደረጃ እንደሆነ፤ የመንግሥት ጤና አገልግሎት ግን ያለዉ በመንደር ደረጃ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ያም ቢሆን ያለው አንድ የጤና ሰራተኛ ለ5 ወይም 6 መንደሮች አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የጤና ሰራተኛ የሚባለውም በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ደረጃ ብቻ የሰለጠ (ሙያተኛ ያልሆነ) ሰው ነው፡፡ ከበርካታ የጤና ሰራተኞች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ለማወቅ እንደተቻለዉ አብዛኛዎቹ ከእምነታቸው የተነሳ (ብዙዎቹ ካቶሊኮች ናቸው) የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ከመስጠት እንደሚቆጠቡ ለማወቅ ተችሎአል፡፡ በተጨማሪም ካለባቸው የሥራ ጫና የተነሳ እነዚህ የጤና ሰራተኞች መንደሮች ዉስጥ በመግባት አገልግሎት ከመስጠት ይልቅ ተገልጋዮች እነሱ ወዳሉበት ጤና ኬላዎች በመምጣት እንዲገለገሉ ይጠብቃሉ፡፡ ለአብዛኛዎቹ ነዋሪዎች በመኖሪያዎቻቸውና በጤና ኬላዎች መሃከል ያለው ርቀት ከፍተኛ ስለሆነ የቤተሰብ ምጣኔንና

የጤና አገልግሎት ለማግኘት የትራንስፖርት ወጪውን ወይም የሥራ ጊዜአቸውን መስዋዕት ማድረግ አይደፍሩም (አይችሉም)፡፡ ስለሆነም በነዚህ የባርጠረፍ አካባቢዎች (ጎጦች) ከፍተኛ የውልደት መጠን፣ የምግብ እጥረትና ተላላፊ በሽታዎች ተንሰራፍተው ይገኛሉ፡፡

በብዛኛዎቹ የከተማ መስተዳድሮች የአካባቢ ጉዳዮች መምሪያ/ሙያተኛ ስለሌላቸው የተፈጥሮ ሃብት ክብካቤን በተመለከተ ያለባቸው ክፍተት የከፋ ነው፡፡ አንደንዶቹ የግብርና ሙያተኛና ኢንጂነር አሉአቸው፡፡ እነዚህ ሙያተኞች አቅራቢያቸዉ ወደሚገኙ መንደሮች በመሄድ የኢክስቴንሽን ሥራ የሚሰሩ ቢሆንም የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤን በተመለከተ በቂ እውቀትና ክህሎት የላቸዉም፡፡

በዚህ ምክንያት ማሕበረሰቡ ስለአሳና ሌሎች የባርጠረፍ ሃብቶቹ ፋይዳና አጠባበቅ ያለው እውቀት አነስተኛ ነው፡፡ በነዚህ አካባቢዎች በሕዝብ ብዛት ጫናና በምጣኔ-ኑሮ አማራጮች እጦት ምክንያት ጎጂ የአሳ ማጥመድ ተግባሮችና ሌሎች የሃብት መራቆት ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላሉ፡፡

በጎጥ ደረጃ ያሉ ተቋሞች ገጀራ፣ ሳሙናና መሠል የእለት መጠቀሚያ ቁሳቁሶችን የሚሸጡ ሱቆች (ኪዮስኮች)፣ የአሳ አጥማጆች ማህበራት፣ የወጣቶችና የሴቶች ቡድኖች ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህም ቢሆኑ በአግባቡ ያልተደራጁና የአስተዳደር አወቃቀራቸውም ያልዳበረ ነዉ፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ በመንደርና በከተሞች አገልግሎቶችን ለማሕበረሰቡ በማድረስ ረገድ እነዚህ ተቋሞች መልካም (ምቹ) አጋጣሚዎችን ፈጥረዋል፡፡ በመሆኑም ፕሮጀክቱ የእቅድ አፈጻፀም መርሃግብሩን በሚያዘጋጅበት ጊዜ የመንግሥትን አገልግሎቶች ተደራሽነት ለማረጋገጥ ለኪዮስክ ባለቤቶችና ለሕዝብ ድርጅቶች (Peoples Organizations) አቅም ግንባታ ትኩረት ስጥቷል፡፡

## የIPOPCORM ፕሮጀክትን በተመለከተ ክፍተቱን ለመዝጋት የነበሩ አማራጮች

- የአገልግሎት ክፍተቱን የመብት ጥያቄ ጉዳይ ማድረግ - መንግሥት አገልግሎቱን እንዲያስፋፋ ጫና መፍጠር (በታችኛው የመንግሥት እርከን የአቅም ችግር ስላለ ዘዴውን ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ነዉ)፡፡
- አገልግሎቶቹን (ያለመንግስት ድጋፍ) ማቅረብ - መንግሥትን ወደጎን በመተው የስነህዝብ፣ ጤናና አካባቢ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ተጓዳኝ ሥርዓት መዘርጋት (ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ ዘላቂነት ላይኖረው ይችላል) ፡፡
- ከመንግሥት ጋር ትብብር በመፍጠር እነዚህን አገልግሎቶች ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ወጪ መጋራት ለምሳሌ የሥልጠና የቁሳቁሶች ድጋፍ ማቅረብ፡፡ (ይህ ዘዴ ጥሩ አማራጭ ቢሆንም ሁሉም አካላት የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ የመግባቢያ ሰነድ(MoU) መኖር አለበት)

## IPOPCORM ሁኔታ ካርታ (2)



ይህ ካርታ ፕሮጀክቱ የነበረውን የአገልግሎት ክፍተት ለመዝጋት የተጠቀመባቸውን ዘዴዎች ያሳያል። የተወሰዱ ዋና ዋና እርምጃዎች፡-

1. ከመንግሥት የገጠር ጤና፣ እቅድና ልማት ክፍሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ውይይት ማድረግ፣ ዕቅድ በጋራ ማዘጋጀት ።

2. የሁሉንም ወገን ተግባርና ሃላፊነት በግልፅ ያስቀመጠ የመግባቢያ ሰነድ (MoU) ከነዚህ መንግሥታዊ ክፍል ሰራተኞች ጋር በማዘጋጀት ከንቲባው እንዲያፀድቀው መጠየቅ።

3. የሳራ-ሳሪ መደብሮች ባለቤቶች የቤተሰብ ምጣኔ መረጃና ቁሳቁሶች ማሰራጨት እንዲችሉ አቅማቸውን መገንባት። እነዚሁ የመደብር ባለቤቶች ከመንደሩ ጤና ሰራተኛ አንድአንድ ቁሳቁሶችን እንዲያገኙ፤ ከገጠር ጤና አገልግሎት ክፍል ጋር በመሆን ደግሞ የሪፈራል ሥራ (ለምሳሌ ለአባለዘር በሽታ ህክምና፣ ለዘለቄታዊ የወሊድ መቆጣጠሪያ አገልግሎቶች ወዘተ) እንዲሰሩ ማገናኘት/ማስተሣሰር።

   በተጨማሪም የሪፈራል አገልግሎቱን እንዲያመቻቹና የፒ.ኤች.ኢ መረጃዎችን እንዲያሰራጩ ለመንግሥት የጤና አገለግሎት ክፍል ሠራተኞችና ለገጠር ጤና ሰራተኞች በቤተሰብ ምጣኔ/ስነተዋልዶ ጤናና በፒ.ኤች.ኢ ቅንጅት ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። የመንግስታዊው ጤና አገልግሎት ክፍል ሠራተኞች በበኩላቸው የስነተዋልዶ ጤናና ሃላፊነት የተሞላበት አሳ ማስገር እንዲኖር የሚሠሩ በለውጥ አመቻችነት የሚያገለግሉ የሳሪ ሳሪ ሱቅ ባለቤቶችንና የማሕበረሰብ በጎ ፈቃደኛ አቻ መምህራንን አሠልጥነዋል።

4. የህዝብ ድርጅቶች ጥብቅ ባህርማ አካባቢዎችን ከመንደር ልማት ምክር ቤቶች ጋር እንዲያስተዳድሩ ከመንግሥት አካላት ጋር በመሆን አቅማቸውን መገንባት። አስተዳደሩ ጥብቅ አካባቢዎችን ለማቋቋምና ለአሣ ጥበቃ ሠራተኞች ሥልጠና ከሚያስፈልገው ገንዘብ/ቁሳቁስ የበኩሉን ድርሻ እንዲያዋጣ መጠየቅ።

5. በጥብቅ አካባቢዎች መቋቋም ምክንያት ከመደበኛው የዓሣ ማስገሪያ አካባቢያቸው ለሚፈናቀሉ አሥጋሪዎች አማራጭ መተዳደሪያ የሚሆን የብድር አገልግሎት ማቅረብ እንዲችሉ ለህዝብ ድርጅቶች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፡፡

በማሕበረሰቡ ውስጥ እነዚህን አቅሞች ለመፍጠር 3 ዓመት ወስዷል፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ ክንውኖችና የጥብቅ ሃብቶች አያያዝ ሥርዓት ከተዘረጋ በኋላ ማሕበረሰቡ በራሱ እነዚህን ተግባሮች ያለ አካባቢዉ አስተዳደር ድጋፍ ለማከናወን አስፈላጊወን አቅም አዳብሯል፡፡

የ IPOPCORM ፕሮጀክት ያለውን አገልግሎት ክፍተት በአግባቡ መለየት በመቻሉ በማህበረሰቡና በመንግስት አገልግሎት ሰጪዎች መሃከል አስፈላጊውን ትሥሥር ለማወቅና ለማመቻቸት ችሏል፡፡

## በኔፓል የፒ.ኤች.ኢ ክፍተት ማጥበብ




በኔፓል ፕሮጀክት ከወረዳ ደን ጽ/ቤት የቴክኒክ ድጋፍ በሚያገኙ የማሕበረሰብ ደን ተጠቃሚ ቡድኖች (CFUGs) የሚተዳደሩ ጥብቅ የደን አካባቢዎች አሉ፡፡ (በአረንጓዴ ሣጥን የተመለከተው)

ነጫጮቹ ሳጥኖች ደግሞ በአንድ መንደር ዉስጥ ያሉትን የመንግሥት ጤና መዋቅሮችና አገልግሎቶች ያመለክታሉ፡፡ በንዑስ ጤና ኬላ ያሉ ሠራተኞች (እነኚህ ኬላዎች በመደበኛዉ የጤና አገልግሎት አወቃቀር የመጨረሻው ታችኛው የአገልግሎት ተቋሞች ናቸው) የክትባት፣ ቤተሰብ ምጣኔና የነፍስጡር እናቶች ጤና አገልግሎት ለማቅረብ በየወሩ የውሎገብ ክሊኒክ አገልግሎት (Outreach Clinic-ORC) እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ባለፉት አስር ዓመታት በነበረው የሽማቂዎች ውጊያ/ግጭት ምክንያት እነዚህ የውሎገብ ክሊኒኮች አገልግሎት አቁመዋል፡፡ ግጭቱ ምንም እንኳ አሁን የቆመ ቢሆንም የመንግሥት ጤና ሰራተኞች የውሎገብ ክሊኒክ አገልግሎቱን እንደገና ለማንቀሳቀስ ጥረት አላደረጉም፡፡ በየጤና ኬላዎቻቸውና ንዑስ ጤና ኬላዎቻቸው በመቀመጥ ተጠቃሚዎች ወደነሱ እንዲመጡ ይጠብቃሉ፡፡

የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ሴት የማሕበረሰብ ጤና በጎፍቃደኞች (FCHU) በመባል የሚታወቁ መሠረታዊ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ከማሕበረሰቡ የወጡ የተወሰኑ ቁጥር ያላቸዉ ሴቶችን አሠልጥኗል፡፡ እነዚህ በጎፍቃደኞች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት እንዲያስፋፉና የወሊድ መቆጣጠሪያዎችን እንዲያሠራጩ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ብዙዎች ካለባቸው የሥራ ጫና ይህን ሃላፊነት አይወጡም፡፡

የኔፓል የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት የማሕበረሰብ ደን ተጠቃሚዎች ቡድኖችን ስለ ወረዳው ጤና ጽ/ቤት ፖሊሲ እንዲሁም በውሎገብ ክሊኒክ የጤና አገልግሎት ስለማግኘት መብት በማስተማር ያለውን የጤና አገልግሎት ክፍተት ለመሙላት በማለም የተነሳ ፕሮጀክት ነው፡፡ ቡድኖቹ ስለጤና አስፈላጊነትና የጤና አገልግሎት የማግኘት ህጋዊ መብታቸው ግንዛቤ ማግኘት ሲጀምሩ የወረዳው ጤና ጽ/ቤት የተዘጉትን የውሎ ገብ ክሊኒኮች እንዲከፍት መወትወት ጀመሩ፡፡ ፕሮጀክቱ በበኩሉ የማሕበረሰብ ደን ተጠቃሚዎች ቡድኖች የቤተሰብ ምጣኔን እንዲያሳፋፉ፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ እንዲያሰራጩ፣ የተሸሻሉ የማብሰያ ምድጃዎችን እንዲያስገቡና ባህላዊ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የፒ.ኤች.ኢ መልዕእክቶችን (መረጃ) እንዲያሰራጩ አቅማቸዉን ገንብቷል፡፡ አቻ መምህራን ለሴት የማሕበረሰብ በጎፍቃደኛ ጤና አገልግሎት ሰራተኞችና ለንዑስ ጤና ኬላዎች ረዳት በመሆን እያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የውሎገብ ክሊኒኮችን የሚያደራጁና የሚያንቀሳቅሱት እነሱ ናቸው፡፡

# ክፍለጊዜ 8፡ የክትትልና ግምገማ እቅድ

**የክፍለጊዜው ዓላማ፡**

- ለ የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክት/ተግባር ቀላል የክትትል ዕቅድ ማዘጋጀት

**ከክፍለ ጊዜው በፊት የሚነበቡ ጽሁፎች**

- የፒ.ኤች.ኢ ፕሮግራም ዝግጅት ማኑዋል ገጽ 54-64
- "የፒ.ኤች.ኢ. ፕሮግራሞች ክትትልና ግምገማ መምሪያ" - MEASURE ገጽ 23-39

## ክትትልና ግምገማን ማነጻጸር

| | ክትትል | ግምገማ |
|---|---|---|
| ድግግሞሽ | መደበኛ፤ ተከታታይ | ወቅታዊ |
| ዋና ተግባር | መከታተል/ቁጥጥር | መፈተሽ |
| መሠረታዊ ዓላማ | የአፈፃጸም ብቃትን መሻሻል፤ የሥራ ዕቅድን ማስተካከል | ውጤታማነትን፣ ተጽእኖንና የወደፊት ፕሮግራም ዝግጅትን ማሻሻል |
| ትኩረት | ግብዓት/ ውጤት ፣ ሂደት ፣ ለዉጥ፣ የሥራ ዕቅድ | ውጤታማነት፣ አግባብነት፣ ብቃት፣ ኢምፓክት፣ ዘላቂነት |
| የመረጃ ምንጭ | መደበኛ ሥርዓቶች ፣ የመስክ ጉብኝት፣ የባለድርሻ አካላት ስብሰባ፣. የውጤት ሪፖርቶች ፣ ፈጣን ፍተሻ (Rapid Assessment) | ከተጠቀሱት በተጨማሪ የቅድመ-ፕሮጀክትና ድህረ-ፕሮጀክት ቅኝቶች (Survey) ፣ ልዩ ጥናቶች |
| ፈጻሚ | የፕሮጀክት/ፕሮግራም ሃላፊዎች፣ የማህበረሰብ ሠራተኞች፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ማሕበረሰቡ (ተጠቃሚዎች)፣ የፕሮጀክት ማከናወኛ ገንዘብ ለጋሾች ሌሎች ባለድርሻ አካላት | የውጭ ገምጋሚዎች ፣ ማህበረሰቡ (ተጠቃሚዎች)፣ የፕሮጀክት/ የፕሮግራም ሃላፊዎች ፣ ሱፐርቫይዘሮች የፕሮጀክት ማከናወኛ ገንዘብ ለጋሾች |

ከዩኒሴፍ *"A UNICEF Guide for Monitoring and Evaluation: Making and Difference?"* ኒውዮርክ 1991፣ ገጽ 3 የተወሰደ

## የክትትል ሥርዓት ዕቅድ ማዉጣት

1. ክትትል ሊደረግበት የሚገባው ነገር ምንድን ነው?
   - አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ብቻ ያዙ
   - ተጠቃሚዎች ሊገለገሉበት የሚችሉትን መረጃ ብቻ አሰባስቡ

2. እንዴት ?

- አመላካቾችን ለመከታተል እንዲሁም ለዉጥን ሪፖርት ለማድረግ ተገቢውን ዘዴ ምረጡ
  - ቅኝት፣ ቃለመጠይቅ ፣ መደበኛ ሪፖርቶች የክትትል ቦታዎች (Sentinel Sites)
  - ባሉት መረጃዎች ላያ ሆኖ ሌሎችን ተጨማሪ መረጃዎችን ማጠናከር ( piggyback on existing data collection)
  - መደበኛ /መደበኛ ያልሆኑ ዘዴዎች፣ በቁጥር/አይነት መረጃ የሚገልጹ የጥናት ዘዴዎች
  - መረጃ እንዴት ስርዓት ባለው መንገድ እንደሚሰበስብና እንደሚቀርብ ወስኑ
  - መረጃውን የሚሰበስቡ ሰዎችን ጊዜና ክህሎት አገናዝቡ
  - አዳዲስ አሠራሮችን በቅድሚያ ፈትሹ (ሞክሩ)

3. ማን መቼ መካተት አለበት
   - አመላካቾችን በተመለከተ ማን መረጃ እንደሚሰበስብ፣ መቼ እንደሚሰበስብና የተሰበሰበው መረጃ ለማን እንደሚቀርብ በግልጽ መታወቅ አለበት
   - የክትትል እቅዱ በተጨማሪም ለውጥ በመገምገምና ውጤትን በማሳወቅ ማን መካተት እንዳለበት በግልፅ ማስቀመጥ አለበት
4. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ምንድን ናቸው? የትኞቹስ በእጃችን አሉ?
   - መረጃውን የማሰባሰብ፣ የመተንተንና ሪፖርት ማድረግ የሚያስፈልገዉ የሰው ሃይልና የገንዘብ ወጪ መታወቅ አለበት

- ለዚህ ተግባር የሚሆን ገንዘብና ጊዜ መያዝ አለበት

5. **ውይይትና ሥልጠና**
    - የክትትል ፕሮግራም ወደተግባር ከመተርጎሙ በፊት በየደረጃው ካሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ አካላት ጋር ተወያዩበት
    - የክትትል ሥርዓቱን ለሚጠቀሙ ክፍሎች ሁሉ ስልጠና መሰጠት አለበት
6. **የሥራ ዕቅድ ዝግጅት**
    - ለያንዳአንዱ ዓመት የሚከናወኑ ዋና ዋና ቁልፍ ተግባራት፣ የሚጠበቀውን ዉጤት፣ የጊዜ ሰሌዳና በክንውኑ የሚሳተፉ አካላትን በመዘርዝር የዓመቱን የስራ ዕቅድ ማዘጋጀት ይጠበቅባችል፡፡

# ሰንጠረዥ 1፡ የIPOPCORM ውጤት ለመከታተል የተዘጋጀ ዕቅድ

## የፕሮጀክት ተግባሮች ቅጽበታዊ ውጤት (Immediate Result)

| | የክትትል አመላካች | የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ (እንዴት) | ድግግሞሽ (መቼ) | ሃላፊነት ድርጅት/ግለሰብ (ማን) |
|---|---|---|---|---|
| ፖሊሲ | 1. በአካባቢ መስተዳደሮች የፀደቁ የስነተዋልዶ ጤናን ያካተቱ የማዘጋጃ ባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ እቅዶች ብዛት (ቁጥር) | የማዘጋጃ እቅድና ልማት ጽ/ቤት | ዓመታዊ | ተባባሪ የአካባቢ መስተዳደር አካል |
| ዕቅድ ዝግጅትና ማኔጅመንት | 1. በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ የጥብቅ አካባቢዎች ማኔጅመንት ኮሚቴዎች ያሉባቸው ባራንጌዮች (Barangays) መጠን (መቶኛ) | የባራንገይ ምክር ቤት መዛግብት + የድርጅቱ ውጤት ሪፖርት | በየሶስት ወሩ | የድርጅቱ ሱፐርቫይዘር |
| ሥልጠና | 1. በፒ.ኤች.ኢ ቅንጅት/የውሎገብ አገልግሎት አሰጣጥ የሰለጠኑ የመያድ ሰራተኞች ብዛት<br>2. በሰለጠኑ የመያድ ሰራተኞች ላይ ስለ ፒ.ኤች.ኢ ፣ ቤተሰብ ምጣኔ፣ ስነተዋልዶ ጤና፣ የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ በተመለከተ የተስተዋለ | የስልጠና ሪፖርቶች<br><br>የቅድመ/ድህረ ስልጠና ሙከራ ፈተና ውጤቶች/የስልጠና ሪፖርቶች | በመንፈቅ<br><br>በመንፈቅ | የፓዝ ፋውንዴሽን አሰልጣኝ<br><br>የፓዝ ፋውንዴሽን አሰልጣኝ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የዕውቀት መጨመር<br>3. ስለአማራጭ ምጣኔ ኑሮ ለአሳ አጥማጆች የተሰጠ የትምህርት ፕሮግራም (ቁጥር) | • የድርጅት ውጤት ሪፖርቶች | በየሶስት ወሩ | የድርጅቱ ሱፐርቫይዘር |
| አገልግሎቶች | 1. የማህበረሰብ ስርጭት ጣቢያዎች (CBD) ያሏቸው ህዝባዊ ድርጅቶች ቁጥር<br>2. በማሕበረሰብ ስርጭት ጣቢያዎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ያገኙ ተጠቃሚዎች ቁጥር<br>3. በማሕበራዊ ግብይት የተሸጡ ቁሳቁሶች ዋጋ | • የድርጅት ውጤት ሪፖርት<br>• የማሕበረሰብ ስርጭት አገልግሎት ስታትስቲክስ<br>• የማሕበረሰብ ስርጭት አገልግሎት ስታትስቲክስ | በየሶስት ወሩ<br>በየወሩ<br>በየወሩ | የድርጅቱ ውሎገብ ሰራተኛ (ለሁሉም አመላካቾች) |
| የተቀናጀ የመረጃ ፣ ትምህርትና ተግባቦት (IEC) | 1. ተያያዥነት ያላቸው የስነተዋልዶ፣ ጤናና የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ ጉዳዮች ዙሪያ የተዘጋጁ መልዕክቶችና መሣሪያዎች ቁጥር<br>2. በበዓላት ወቅት የተከናወኑ የፒ.ኤች.ኢ ዘመቻዎች ቁጥር<br>3. የፒ.ኤች.ኢ ዘመቻውንና ስነተዋልዶ ጤና/ባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ መልዕክቶችን በተመለከተ የተደራስያን አቀባበል ሁኔታ | • የድርጅቱ ውጤት ሪፖርት የIEC ቁሳቁሶች ዶሴ/ፋይል<br>• የድርጅቱ ውጤት ሪፖርት<br>• FDG | በሶስት ወሩ<br>በየሶስት ወሩ<br>በዓመት | ውሎገብ ሰራተኛ<br>ውሎገብ ሰራተኛ<br>የድርጅቱ ሱፐርቫይዘሮች |

## ሰንጠረዥ 2፡ ወደ IPOPCORM ዓላማዎችና ውጤቶች የሚደረገውን እርምጃ መከታተያ እቅድ

| ዓላማ | አመላካች | የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ | ድግሞሽ | ከዋኝ ድርጅት/ግለሰበ |
|---|---|---|---|---|
| ዓላማ 1፡<br>የባርጠረፍ ማሕበረሰብ ነዋሪዎችን የስነተዋልዶ ጤና ማሻሻል | 2. በመዉለድ እድሜ ክልል ያሉ ሴቶች የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም<br>3. በመዉለድ እድሜ ክልል ያሉ ሴቶች ስለድንገተኛ እርግዘና መቆጣጠሪያ ዘዴ (Emergency Contraception ) ያላቸው ዕውቀት<br>4. በመጀመሪያ የግብረስጋ ግኑንነት ወቅት ማንኛውንም አይነት የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ የተጠቀሙ ወጣቶች መቶኛ | የባህሪ ክትትል ጥናት (BMS) | በየ24 ወራት<br>በየ24 ወራት<br>በየ24 ወራት | የድርጅቱ ሱፐርቫይዘር<br>የውሎገብ ጤና ሰራተኞች<br>የድርጅቱ ሱፐርቫይዘር |
| ዓላማ 2፡<br>በማህበረሰብ ደረጃ የባሕርማ እንዲሁም ባርጠረፍ ሃብቶችን ክብካቤ ማሻሻል | <u>ባዮፊዚካዊ አመላካቾች</u><br>1. ሕያዉ ዛጎል (Live Coral) ሽፋን መቶኛ<br>2. የማንግሩቭ ተክል ሽፋን በሄክታር<br><u>የማኔጅመንት አመላካቶች</u> | የጥብቅ ባህራዊ ሃብት አካባቢዎች የክትትል ጥናት (Monitoring Survey) | በዓመት | ሕዝባዊ ድርጅቶች |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 1. የተሻለ ክብካቤ እየተደረገላቸው ያሉ ጥብቅ ባህርማ አካባቢዎች ብዛት (ቁጥርና) ስፋት (በኪ.ሜ)<br>2. ተቋቁመዉ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ የጥብቅ ባህራዊ ሃብት አካባቢዎች ማኔጅመንት ኮሚቴዎች ቁጥር<br>3. ሪፖርት የተደረጉና የተረጋገጡ ጥሰቶች ቁጥር | የማዘጋጃ ባርጠረፍ ሃብት ዳታቤዝ<br>የመያድ ውጤት ሪፖርት<br>የማጅመነት ኮሚቴ የዕለት ሁኔታ መዝገብ | በዓመት<br><br>በየ3 ወር<br><br>በየ3 ወር | ተባባሪ የአካባቢ መሥተዳደር አካላት<br>የውሉገብ ሠራተኛ<br><br>የ ውሉገብ ሠራተኛ |
| ዓላማ 3፡<br>ሕዝቡና ፖሊሲ አውጪዎች ስለ ፒ.ኤች.ኢ ያላቸውን ግንዛቤና ድጋፍ ማሣደግ | 4. በስነሕዝብ፣ አካባቢና ጤና ጉዳዮች ማሃከል ስላለው መስተጋብር ዕውቀት ያላቸው ፖሊሲ አውጪዎች ቁጥር<br>5. ለፒ.ኤች.ኢ ተግባሮች ማስፈጸሚያ ከአካባቢ መስተዳደሮችና ማህበረሰቦች የቀረበ ሃብት ዋጋ | የፖሊሰ አውጪዎች ጥናት<br><br>የድርጅቱ የፋይናንስ መዛግብትና የፋይናንስ መግለጫ ኦዲት | በዓመት<br><br>በየ24 ወራት | የድርጅቱ ፕሮጄክት ዳይሬክተር<br><br>በፊሊፒንስ የፓዝ ፋውንዴሽን ኦዲተር |

## የፕሮጀክት ቡድን ተግባር ፡- የክትትል ዕቅድ ማዘጋጀት

1. ቀጥሎ የቀረበውን ቅፅ (ምርክሽት ) በመጠቀም ቀደም ላዘጋጃችኋቸው አንድ/ሁለት ዓላማዎች - ክንውኖች የክትትል ዕቅድ አዘጋጁ፡-

   - በመጀመሪያው አምድ- በጊዜ የተገደበ ውሱን ዓላማችሁን አስፍሩ
   - በ2ኛው አምድ- ክንውኖችንና ተያያዥ የውጤት ሰንሰለት ምክንያቶችን አስፍሩ
   - በ3ኛው አምድ- ለክንውኖች - የውጤት ሰንሰለት ምክንያቶች የመረጣችኋቸውን 2 ወይም ከዚያ በላይ አመላካቾችን አስፍሩ
   - በ4ኛው አምድ- ለያንዳአንዱ አመላካች የክንውን ግብ (Performance Indicator) አስገቡ
   - 5ኛ አምድ፡- የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴውን (እንዴት ይሰራል) አስፍሩ
   - በ6ኛ አምድ የመረጃ አሰባሰብ ድግግም (Frequency of Data Collection) ይግባ
   - በ7ኛው አምድ፡- በዋናነት መረጃን የመሰብሰብ/ሪፖርት የማድረግ ሃላፊነት ያለበት ወገን/ድርጅት/ግለሰብ ስም አስገቡ፡፡

2. ቢያንስ ለአንድ ዓላማ/ክንውን እና አብሮት ላለ አመላካች 'የተሟላ' ዕቅድ ለማዘጋጀት በሚያስችላችሁ መልኩ ጊዜችሁን አብቃቁ (ይህን ማድረግ እንድትችሉ ቅፁን አግድም ሙሉት )
3. ያዘጋጃችሁትን ዕቅድ አጠገባችሁ ላሉ ሌሎች ሠልጣኞች ለመግለጽ ወይም አሠልጣኙ በሚነግራችሁ መሠረት ለማብራራት ተዘጋጁ፡፡

**የተሰጠ ጊዜ 60 ደቂቃ**

## የፒ.ኤች.ኢ ክትትል ዕቅድ ቅፅ (የወርክሽት ) - 1

| ዓላማ | ክንውን/የውጤት ሰንሰለት ምክንያት | አመላካች | ግብ (በፕሮጀክቱ መጨረሻ አመት የሚገኝ ዉጤት) | የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ | ድግግሞሽ | ከዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

# የፒ.ኤች.ኢ ክትትል ዕቅድ ቅፅ (የወርክሽት ) — 2

| ዓላማ | ክንውን/የውጤት ሰንሰለት ምክንያት | አመላካች | ግብ (በፕሮጀክቱ መጨረሻ አመት የሚገኝ ዉጤት) | የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ | ድግግሞሽ | ከዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

# የዘርፍ ክንውን ናሙና ቅጽ (ምርክሽት)

| ዓላማ | ክንውን/የውጤት ሰንሰለት ምክንያት | አመላካች | ግብ (በፕሮጄክቱ መጨረሻ አመት የሚጠበቅ ዉጤት) | የመረጃ አሠባሰብ ዘዴ | ድግግሞሽ | ከዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በ2004 (እ.ኤ.አ) በባርጠረፍ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች የስነተዋልዶ ጤና ሁኔታ ይሻሻላል | ሕብረተሰብ አቀፍ ማሰራጫ አገልግሎት ማስፋፋት፣ ጣቢያዎችን መመሥረት | የተቋቋሙ የማሕበረሰብ ማሠራጫ ጣቢያዎች ብዛት | በ2001 ከነበረው 0 በ2004 ወደ 500 ማሳደግ | የድርጅቱ ውጤት ሪፖርት | በየ3ወሩ | የድርጅቱ ውሎገብ ሰራተኛ |
| | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት 1<br>የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተደራሽነት ማሻሻል | በማሕበረሰብ ማሠራጫ ጣቢያዎች አገልግሎት ያገኙ ተጠቃሚዎች ቁጥርት | በ2001 ከነበረው 0 በ2004 ወደ 8000 ማሳደግ | የማሕበረሰብ ማሠራጫ ጣቢያዎች መዛግብትና የሽያጭ መረጃ | በየወሩ | የድርጅቱ ውሎገብ ሰራተኛ |
| | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት 2<br>በመውለድ እድሜ ክልል ያሉ ሴቶችንና ለአቅመ | በመውለድ እድሜ ክልል ያሉ ሴቶች CPR | እ.ኤ.አ በ2001 ከነበረው 20 % በ2004 ወደ 35% ማሳደግ | የባህሪ ለውጥ ክትትል ጥናት | በየዓመቱ | የድርጅቱ ውሎገብ ሰራተኛ እና ሱፐርቫይዘር |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አቅመ አዳም/ሔዋን የደረሱ ወጣቶችን የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት አጠቃቀም መጨመር | በመጀመሪያ የወሲብ ግኑኝነት ጊዜ የወሊድ መከላከያ የተጠቀሙ ወጣቶች (ዕድሜአቸዉ 15-24 ዓመት ) | እ.ኤ.አ በ2001 ከነበረው 5% በ2004 ወደ 20% ማሳደግ | የባህሪ ለውጥ ክትትል ጥናት | በየዓመቱ | የድርጅቱ ውሎገብ ሰራተኛ እና ሱፐርቫይዘር |

## የተቀናጀ መረጃ፣ ትምህርትና ተግባቦት (IEC) ክንውን ናሙና ቅጽ/ምርክሽት

| ዓላማ | ክንውን | አመላካች | ግብ (በፕሮጀክቱ መጨረሻ አመት የሚጠበቅ ዉጤት) | የመረጃ አሠባሰብ ዘዴ | ከዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|
| በፊሊፒንስ ባርጠረፍ አካባቢዎች በስነህዝብ፣ በአካባቢ፣ በሃብት ፍጆታ/ አጠቃቀምንና በምግብ ዋስት መሃከል ስላለው ትስስር የፖሊሲ አውጭዎችንና የሕዝቡን ግንዛቤ መጨመር | በፒ.ኤች.ኢ ዘርፎች ማሃከል ስላለው ትስስርና ስለባርጠረፍ ሐብት ክብካቤ/የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎች መረጃ ያዘለ የመረጃ፣ ትምሕርትና ተግባቦት (IEC) /አድቮከሲ ማከናወን | የአድቮካሲና የተግባቦት መልዕክቶች የደረሱአቸው ክንቲባዎች ቁጥር | 50 ክንቲባዎች (በፕሮጀክቱ መጨረሻ አመት) | የጋራ ስብሰባ ቃለጉባኤዎች | የፒ.ኤች.ኢ መስክ ሱፐርቫይዘር |
| | <u>የውጤት ሰንሰለት ምክኒያት 1</u> በፕሮጀክት አካባቢው የቤተሰብ ምጣኔ ጉዳዮችን ከባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ ተግባሮች ጋር ለማቀናጀት ለሚደረገው ጥረት ድጋፍ | የቤተሰብ ምጣኔን እንዲሁም ለቤተሰብ ምጣኔ የሚሆን በጀት ያካተቱ የማዘጋጃ ባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ እቅዶች ቁጥር | 25 እቅዶች (በፕሮጀክቱ መጨረሻ አመት) | የማዘጋጃ ባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ ዕቅዶች + የድርጅቱ ውጤት ሪፖርቶች | የፒ.ኤች.ኢ መስክ ሱፐርቫይዘር |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ማሰባሰብ/ማሳደግ | | | | |
| | <u>ውጤት ሰንለሰት ምክንያት 2</u><br>ማሕበረሰቡ ስለባርጠረፍ ሃብት ክብካቤና ስለቤተሰብ ምጣኔ ያለውን ግንዛቤና ተሳትፎ ማሳደግ | የተከናወኑ የፒ.ኤች.ኢ ትምህርት ዘመቻዎች ቁጥር | 20 (በፕጀክቱ ማጠናቀቂያ) | የድርጅቱ ውጤት ሪፖርት | የፒ.ኤች.ኢ ውሎገብ ሰራተኛ |
| | | የተቀናጁ የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ - ቤተሰብ ምጣኔ የድርጊት መርሃግብሮችንና ተግባሮችን በማዘጋጀት ያከናወኑ መንደሮች ቁጥር | 100 መንደሮች (በፕሮጀክቱ መጨረሻ አመት) | የመንደር የልማት መርሃግብሮች | የፒ.ኤች.ኢ ውሎ ገብ ሰራተኛ |

# የእሴት ጨማሪ ክንውን ናሙና ቅጽ/ምርክሽት

| ዓላማ | ክንውን | አመላካች | ግብ<br>(በፕሮጄክቱ መጨረሻ አመት የሚጠበቅ ዉጤት) | የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ | ድግግም | ከዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የማሕበረሰቡ ዘላቂ የደን ሃብት ክብካቤ አቅም ይገነባል | የተሻሻሉ የማብሰያ ምድጃዎችን ማስፋፋት | የተሰራጩ ምድጃዎች ቁጥር | በዓመት 100 ምድጃዎች/በ4 ዓመት 400 (በፕሮጄክቱ ማጠናቀቂያ ) | የድርጅቱ አገልግሎት ስታትስቲክስ | በየ6 ወሩ | የፒ.ኤች.ኢ የመስክ ሱፐርቫይዘር |
| | <u>የውጤት ሰንሰለት ምክንያት 1</u><br>የማገዶ ፍጆታ መቀነስ | የተቆጠበ ማገዶ መጠን | መጀመሪያ ዓመት= 100 ሜ.ቶ<br>ሁለተኛ ዓመት = 200 ሜ.ቶ<br>ሶስተኛ ዓማት = 300 ሜ.ቶ<br><u>አራተኛ ዓመት = 400 ሜ.ቶ</u><br>አጠቃላይ 1000 ሜ.ቶ | ስሌት፡<br>1 የተሻሻለ ምድጃ በዓመት 1 ቶን ማገዶ ይቆጥራል | በየ6 ወሩ | የፒ.ኤች.ኢ የመስክ ሱፐርቫይዘር |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | <u>ውጤት ሰንሰለት ምክንያት 2</u><br>ማገዶ ለመልቀም የሚባክነወን ጊዜ መቀነስ | ማገዶ ለመሰብሰብ የሚባክነው አማካይ ሰዓት/ ቀን | የመቀነስ አዝማሚያ | በቤተሰብ ደረጃ የሚከናወን ጥናት | በዓመት | የማሕበረሰብ ደን ተጠቃሚዎች ቡድን አለቃ |
| | <u>ውጤት ሰንሰለት ምክንያት 3</u><br>ማገዶ የሚለቅሙ ሴቶች/ልጃገረዶችን ለሁከት ተጋላጭነት መቀነስ | ሪፖርት የተደረጉ ማገዶ በሚለቅሙ ሴቶች ላይ የተፈጸሙ ሁከቶች ቁጥር | የመቀነስ አዝማሚያ | የፖሊስ መዛግብት፣ የማሕበረሰብ ደን ተጠቃሚዎች ቡድኖች መዛግብት | በዓመት | የፒ.ኤች.ኢ መስክ ሱፐርቫይዘር |

# የተቀናጁ ክንውኖች ናሙና ቅጽ/ምርክሽት

| ዓላማ | ክንውን | አመላካች | ግብ (በፕሮጀክቱ መጨረሻ አመት የሚጠበቅ ዉጤት) | መረጃ አሰባሰብ ዘዴ | ድግግምሽ | ከዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማሕበረሰቡ የተቀናጁ የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ ተግባሮችን እንዲሁም የቤተሰብ ምጤኔ ስትራቴጂዎቸን የማከናወን አቅም ይኖረዋል | በንዑስ መንደር ደረጃ የተቀናጀ የባርጠረፍ ሃብት ክብካቤና የቤተሰብ ምጣኔ ሥራዎችን ለማከናወን ኣቅም ግንባታ | በባርጠረፍ ሃብት ክብካቤና በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት የሰለጠኑ የሕዝብ ድርጅቶች ቁጥር | 50 ህዝብ ድርጀቶ (በፕሮጀክቱ መጨረሻ አመት) | የመያድ ሪፖርት እና ከመንደር አለቃዎች ጋር የሚደረግ ቃለመጠይቅ | በዓመት | የፒ.ኤች.ኢ የመስክ ሱፐርቫይዘር |
| | የውጤት ሰንሰለት ምክንያት 1 የሕዝብ ድርጅት አባሎችን የቤተሰብ ምጣኔ ተጠቃሚነት መጨመር | የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎችን የሚጠቀሙ ባለትዳሮች መቶኛ | በፕሮጀክቱ ከታቀፉ ተጠቃሚዎች 50% ባለትዳሮች( በፕሮጀክቱ መጨረሻ አመት) | በሕዝብ ድርጅቶች የሚከናወን ጥናት | በዓመት | የሕዝብ ድርጅቶች ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ |
| | ውጤት ሰንለሰት ምክንያት 2 በባርጠረፍ ሃብት ክብካቤ የሕዝባዊ ድርጅቶችን ተሳትፎ መጨመር | በሕዝብ ድርጅቶች የተቋቋሙ ጥብቅ ባህርማ ክልሎች ቁጥርና ስፋት | እያንድአንዳቸው 10 ሄክታር ስፋት ያላቸውን ጥብቅ የአሳ ክልሎች በሕዝብ ድርጅቶች ይቋቋማሉ ፣ ይተዳደራሉ | የማዘጋጃ ጥብቅ ባህርማ ሃብት ክልሎች ዳታ ቤዝ | በዓመት | የፒ.ኤች.ኢ መስክ ሱፐርቫይዘር |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ውጤት ሰንለሰት ምክንያት 3<br>የቤተሰብ ምግብ ዋስትና ማሻሻል | አልፎአልፎ የምግብ ችግር እንደሚያጋጥማቸዉ የተናገሩ ቤተሰቦች መቶኛ | የመቀነስ አዝማሚያ | በቤተሰብ ደረጃ የሚደረግ ጥናት | ቢያንስ 3 ጥናቶች (በየ 18 ወር ልዩነት) | የፓዝ ፋዉንዴሽን የክትትልና ግምገማ ባለሙያ እና የፒ.ኤች.ኢ መስክ ሱፐርቫይዘር 5 |

# ክፍለ ጊዜ 9፡ግብረ-መልስ (Back-Home Application)

**የክፍለጊዜው ዓላማ**

- ሰልጣኞች ከአዉደጥናቱ ያገኙትን እውቀት በተግባር ለመተርጎም ዕቅድ ያዘጋጃሉ፤ በቡድናቸዉ የተዘጋጀውን የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጄክት ሃሳብ/ንድፍ ያከናዉናሉ፡፡

## የፕሮጀክት ቡድን ተግባር ፡- የተዘጋጀዉን ፕሮጀክት ማደራጀትና /መፈተሽ

1. በፕሮጀክት ዝግጅት ሂደት ያዘጋጃችኋቸዉን ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የፕሮጀክት ክፍሎች (ቅጾች) አሰባስቡ፡-

    - ግንዛቤያዊ ሞዴል (ክፍለ ጊዜ 3)
    - የፕሮጀክት ግብ፣ ዓላማዎች፣ ስትራቴጂዎች (ክፍለ ጊዜ 4)
    - የውጤት ሰንሰለቶች (ክፍለ ጊዜ 4)
    - መረጃ -ደገፍ ክንውኖች (ክፍለ ጊዜ 5)
    - አመላካቾች (ክፍለ ጊዜ 6)
    - የአፈፃፀም ካርታዎች (ክፍለ ጊዜ 7)
    - የክትትል እቅድ (ክፍለ ጊዜ 8)

2. እነዚህን ንድፎች/ዉጥኖች እንደገና በማየት በዝግጅት ሂደቱ ላይ ያሉአችሁን ጥያቄዎች/ግልፅ ያልሆኑ ነገሮች መዝግቡ፡፡ (ይህን ተግባር በምታከናዉኑበት ጊዜ እነዚህ የተለያዩ የፕሮጀክት ክፍሎች እንዴት እንደሚያያዙ፣ በተወሰነ ሞዴል ወይም መሣሪያ ላይ ያሉአችሁን ጥያቄዎች፣ እነዚህ ሞዴሎች/መሣሪያዎች ለየአካባቢያችሁ ተጨባጭ የልማት ሁኔታዎች ስላሏቸው አግባብነት መመልከት አትዘንጉ፡፡)

3. ጥያቄዎቻችሁን/ግልጽ ያልሆኑላችሁን ነገሮች ፍሊፕ ቻርት ላይ አስፍሩ

**የተሰጠ ጊዜ፡ 25 ደቂቃ**

## የፕሮጀክት ቡድን/የድርጅት ቡድን ተግባር፡-

## ግብረ-መልስ እቅድ

1. በአዉደጥናቱ ሂደት ያዘጋጃችኋቸዉን የፒ.ኤች.ኢ ፕሮጀክቶች/አሰራሮች እንዲሁም የዲዛይን ሂደቱን እንደገና ፈትሹ፡፡ በመቀጠል ወደየቢሮአችሁ/ወደየአካባቢያችሁ ስትመለሱ በቀጣይ 3-6 ወራት በምታከናዉኗቸዉ ዋና ዋና ተግባሮች ላይ ተስማሙ፡፡

2. በእቅዶቻችሁ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ማካተት እንዳትዘነጉ፤
   - ፕሮጀክቶቻችሁን የተሟላ በማድረግ ወደተግባር ለመግባት መሟለት ያለባቸውን የመረጃ ክፍተቶች፤ መረጃዎቹን እንዴት እንደምታገኙ
   - በቀጣይ የዕቅድ ዝግጀት ሂደት መካተት ስላለባቸው ባለድርሻ አካላት (አጋሮች፣ የፕሮጀክት ተሳታፊዎች፣ የማህበረሰብ መሪዎች ወዘተ.) ፤ እነዚህን አካላት እንዴት ለማሳተፍ እንደምታስቡ
   - ለቀጣይ የፕሮጀክት ዝግጅትንና ዕቅድ የሚያስፈልጉ የቴክኒካዊ ሙያተኞች
   - የፕሮጀክት ቦታ ለመምረጥ መሟላት ስላለባቸው ነገሮች እንዲሁም ለዚሁ ተግባር ስለሚደረግ ጥናት
   - በክፍለ ጊዜ 7 የተለዩትን የአገልግሎት ክፍተቶች ለማሟላት/ለመቅረፍ ስለሚያስፈልግ ጥናትና የዕቅድ ዝግጅት ስብሰባ (የክፍተት ካርታ ዝግጅት)
   - ለታሰበው የቅንጅት ፕሮጀክት ድጋፍ ለማሰባሰብና አቅም ለመፍጠር የሚያስፈልጉ የውስጥና የውጪ ግኑኝነቶች
   - ከሌሎች የአውደጥናቱ ተሳታፊዎች ጋር ሊደረግ ስለሚችል ትስስር (Networking)

3. ቀጥሎ የተቀመጡትን ነጥቦች ያካተተ ተጨባጭና በተግባር ሊተረጎም የሚችል የድርጊት መርሃግብር አዘጋጁ
   - መወሰድ ያለበት እርምጃ/ተግባር
   - አስፈጻሚ/ ሃላፊ ሰዎችን መለየት
   - ለማስፈጸሚያ የሚያስፈልግ ሃብት
   - የጊዜ ሰሌዳ

የቀረበውን የዕቅድ ዝግጅት ቅጽ ተጠቀሙ

**የተሠጠ ጊዜ፡ 50 ደቂቃ**

# የፒ.ኤች.ኢ ግብረ-መልስ ዕቅድ (1)

| ተግባር | አስፈጻሚ/ ሃላፊ | የሚያስፈልግ ሃብት | ጊዜ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

# የፒ.ኤች.ኢ ግብረ-መልስ ዕቅድ (2)

| ተግባር | አስፈጻሚ/ ሃላፊ | የሚያስፈልግ ሃብት | ጊዜ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

# የአውደጥናቱ ግምገማ

**ነጥብ አሰጣጥ**

1. = አልረካሁም
2. = እንደነገሩ ረክቻለሁ
3. = ረክቻለሁ
4. = በጣም ረክቻለሁ

**1. አጠቃላይ ግምገማ**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በአጠቃላይ ይህን አዉደጥናት እንዴት ይመዝኑታል? | 1 | 2 | 3 | 4 |
| አስተያየት፡- | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ስለስልጠናው ዘዴ ምን ይላሉ? (አሳታፊ ገለፃዎች፣ የቡድን ውይይቶችና ተግባሮች የተመጣተኑ ነበሩ?) | 1 | 2 | 3 | 4 |
| አስተያየት፡- | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የስልጠና ቁሳቁሶችን ጥራት በተመለከተ ምን ይላሉ? | 1 | 2 | 3 | 4 |
| አስተያየት፡- | | | | |

2. የዚህ አውደጥናት ዋና ጠቃሚ ክፍል/ገፅታ ምን ነበር ብለዉ ያምናሉ?

3. በዚህ አውደጥናት ብዙም ጠቃሚ ሆኖ ያላገኙት ክፍል/ገጽታ ምንድን ነበር?

4. የአሰልጣኞቹን  ብቃት በተመለከተ ምን ይላሉ?

5. ሌላ ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት?

**እናመሰግናለን!**